# የሉቃስ ወንጌል

የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል
ከሰባ ሁለቱ አርድእት አንዱ ቅዱስ ሉቃስ እንደ ጻፈው።

---

## ምዕራፍ ፩

### ወንጌልን ስለ መጻፍ

፩በእኛ ዘንድ የተፈጸመውንና የታመነውን
የሥራውን ዜና በሥርዐት ሊጽፉ የጀመሩ ብዙ
ዎች ናቸው። ፪ከእኛ አስቀድሞ በዐይን ያዩትና
የቃሉ አገልጋዮች የነበሩ እንደ አስተላለፉልን፤
፫የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ከመጀመሪያው ተከ
ትዬ፥ ሁሉንም በየተራው እውነተኛውን እጽ
ፍልህ ዘንድ መልካም ሁኖ ታየኝ። ፬የተማ
ርኸውን የነገሩን እውነት ጠንቅቀህ ታውቅ
ዘንድ።

### ስለ ዘካርያስና ስለ ኤልሳቤጥ

፭በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ
ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን
ነበረ፤ ሚስቱም ከአሮን ልጆች ወገን ነበረች፤
ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበረ። ፮ሁለቱም በእግዚ
አብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ፤ በእግዚአብሔር
ሥርዐትና በትእዛዙም ሁሉ ያለ ነውር የሚ
ሄዱ ነበሩ። ፯ልጅም አልነበራቸውም፤ ኤል
ሳቤጥ መካን ነበረችና፤ ሁለቱም አርጅተው
ነበር፤ ዘመናቸውም አልፎ ነበር።
፰እርሱም በእግዚአብሔር ፊት በተራው የክህ
ነትን ሥራ በሚሠራበት ጊዜ፥ ፱ካህናት እንደሚ
ያደርጉት የሚያጥንበት ጊዜ ደረሰ፤[፩] ወደ እግ
ዚአብሔር ቤተ መቅደስም ገባ። ፲ዕጣን በሚ
ያጥንበት ጊዜም ሕዝቡ በሙሉ በውጭ ይጸ
ልዩ ነበር። ፲፩የእግዚአብሔር መልአክም በዕ
ጣን መሠውያው በስተቀኝ ቆሞ ታየው። ፲፪ዘካ
ርያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ፤ ፍርሀትም ረዓ
ድም ወረደበት። ፲፫መልአኩም እንዲህ አለው፥
"ዘካርያስ ሆይ፥ አትፍራ፤ ጸሎትህ በእግዚአ
ብሔር ፊት ተሰምቶአልና፤ ሚስትህ ኤልሣቤ
ጥም ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅንም ትወልድል
ሃለች፤ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ። ፲፬ደስታና
ሐሤትም ይሆንልሃል፤ በመወለዱም ብዙዎች
ደስ ይላቸዋል። ፲፭እርሱ በእግዚአብሔር ፊት
ታላቅ ይሆናልና የወይን ጠጅና የሚያሰክርም
መጠጥ ሁሉ አይጠጣም፤ ከእናቱ ማሕፀን ጀም
ሮም መንፈስ ቅዱስ ይመላበታል። ፲፮ከእስራኤ
ልም ልጆች ብዙዎችን ወደ አምላካቸው ወደ
እግዚአብሔር ይመልሳቸዋል። ፲፯እርሱም የአባ
ቶችን ልብ ወደ ልጆች፥ የከሓድያንንም ዐሳብ
ወደ ጻድቃን ዕውቀት ይመልስ ዘንድ፥ ሕዝ
ብንም ለእግዚአብሔር የተዘጋጀ ያደርግ ዘንድ
በኤልያስ መንፈስና ኀይል በፊቱ ይሄዳል።"
፲፰ዘካርያስም የእግዚአብሔርን መልአክ እን
ዲህ አለው፥ "ይህ እንደሚሆን በምን አውቃ
ለሁ? እነሆ፥ እኔ አርጅቻለሁ፤ የሚስቴም
ዘመንዋ አልፏል።" ፲፱መልአኩም መልሶ እን
ዲህ አለው፥ "እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆ
መው ገብርኤል ነኝ፤ ይህንም እነግርህና አበ
ሥርህ ዘንድ ወደ አንተ ተልኬአለሁ። ፳አሁ
ንም በጊዜው የሚሆነውንና የሚፈጸመውን ነገ
ሬን አላመንኸኝምና ይህ እስኪሆን ድረስ ዲዳ
ትሆናለህ፤ መናገርም ይሳንሃል።" ፳፩ሕዝቡ ግን
ዘካርያስን ይጠብቁት ነበር፤ በቤተ መቅደስ
ውስጥ ዘግይቶ ነበርና እጅግ ተደነቁ። ፳፪ወደ
እነርሱ ወደ ውጭ በወጣ ጊዜም እነርሱን ማነ
ጋገር ተሳነው፤ በቤተ መቅደስም የተገለጠለት

---

፩ በግሪኩ "ዕጣ ደረሰው" ይላል።

፩፥፭ ፩ ዜ.መ. ፳፬፥፲።  ፩፥፲፭ ዘኍ. ፮፥፫።  ፩፥፲፯ ሚል. ፬፥፭-፮።  ፩፥፲፱ ዳን. ፰፥፲፮፤ ፱፥፳፩።

እንዳለ ዐወቁ፤ እንዲሁም ዲዳ ሆኖ በእጁ እያ
መለከታቸው ኖረ። ፳፫ ከዚህም በኋላ የማገልገሉ
ወራት በተፈጸመ ጊዜ ወደ ቤቱ ገባ።
፳፬ ከእነዚያም ቀኖች በኋላ[፩] ሚስቱ ኤልሳቤጥ
ፀነሰች፤ ፅንስዋንም ለአምስት ወር ሸሸገች፤
እንዲህ ስትል፦ ፳፭ "እግዚአብሔር በዚህ ወራት
ከሰው ስድቤን ያርቅ ዘንድ በጐበኘኝ ጊዜ እን
ዲህ አደረገልኝ።"

## ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን እንደ አበሠራት

፳፮ በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል
ከእግዚአብሔር ዘንድ ስሟ ናዝሬት ወደምትባ
ለው ወደ አንዲት የገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን
ለሚሆን ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨችው
ወደ አንዲት ድንግል ተላከ፤ ፳፯ የዚያችም ድን
ግል ስምዋ ማርያም ይባል ነበረ። ፳፰ መልአ
ኩም ወደ እርስዋ ገብቶ፥ "ደስ ያለሽ፥[፪] ጸጋ
ንም የተመላሽ ሆይ፥ ደስ ይበልሽ፤ እግዚአብ
ሔር ካንቺ ጋር ነው፤ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ
የተባረክሽ ነሽ" አላት። ፳፱ እርስዋም በአየችው
ጊዜ ከአነጋገሩ የተነሣ ደነገጠችና "ይህ እንዴት
ያለ ሰላምታ ነው?" ብላ ዐሰበች። ፴ መልአኩም
እንዲህ አላት፥ "ማርያም ሆይ፥ በእግዚአብ
ሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና አትፍሪ።
፴፩ እነሆ፥ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅንም ትወልጃ
ለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ። ፴፪ እርሱም
ታላቅ ነው፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጅም ይባ
ላል፤ እግዚአብሔር አምላክም የአባቱን የዳዊ
ትን ዙፋን ይሰጠዋል። ፴፫ ለያዕቆብ ወገንም ለዘ
ለዓለሙ ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለ
ውም።" ፴፬ ማርያምም መልአኩን፥ "ወንድ ስለ
ማላውቅ ይህ እንዴት ይሆንልኛል?" አለችው።
፴፭ መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፥ "መንፈስ
ቅዱስ ያድርብሻል፤ የልዑል ኀይልም ይጋርድ
ሻል፤ ከአንቺ የሚወለደውም ቅዱስ ነው፤ የል
ዑል እግዚአብሔር ልጅም ይባላል። ፴፮ እነሆ፥
ከዘመዶችሽ ወገን የምትሆን ኤልሣቤጥም እር
ስዋ እንኳ በእርጅናዋ ወንድ ልጅን ፀንሳለች፤
መካን ትባል የነበረችው ከፀነሰች እነሆ፥ ይህ
ስድስተኛ ወር ነው። ፴፯ ለእግዚአብሔር የሚሳ
ነው ነገር የለምና"። ፴፰ ማርያምም መልአኩን፥
"እነሆኝ፥ የእግዚአብሔር ባሪያው አለሁ፤
እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" አለችው፤ ከዚህ በኋ
ላም መልአኩ ከእርስዋ ዘንድ ሄደ።

## ማርያም ወደ ኤልሣቤጥ ስለ መሄድዋ

፴፱ በዚያም ወራት ማርያም ፈጥና ተነሣች፤
ወደ ተራራማው ሀገር[፫] ወደ ይሁዳ ከተማም
ደረሰች። ፵ ወደ ዘካርያስ ቤትም ገብታ ለኤል
ሣቤጥ ሰላምታ ሰጠቻት። ፵፩ ኤልሳቤጥም የማር
ያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ
ዘለለ፤ በኤልሣቤጥም መንፈስ ቅዱስ መላባት።
፵፪ በታላቅ ቃልም ጮሃ እንዲህ አለች፥ "ከሴ
ቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ፤ የማኅፀ
ንሽም ፍሬ ቡሩክ ነው። ፵፫ የጌታዬ እናት ወደ
እኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ምንድን ነኝ? ፵፬ እነሆ፥
ሰላምታ ስትሰጭኝ ቃልሽን በሰማሁ ጊዜ፥
ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሎአልና። ፵፭ ከእግዚአ
ብሔር ዘንድ የነገሩሽ ቃል እንደሚሆን የምታ
ምኚ አንቺ ብፅዕት ነሽ።"[፬]
፵፮ ማርያምም እንዲህ አለች፥ "ሰውነቴ እግ
ዚአብሔርን ታከብረዋለች። ፵፯ ልቡናዬም በአም
ላኬ በመድኀኒቴ ሐሤት ታደርጋለች። ፵፰ የባር
ያውን ትሕትና ተመልክቶአልና። እነሆ፥ ከዛሬ
ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል።
፵፱ ታላቅ ሥራን ሠርቶልኛልና፤[፭] ስሙም ቅዱስ
ነው። ፶ ይቅርታውም ለሚፈሩት ለልጅ ልጅ
ነው። ፶፩ በክንዱ ኀይልን አደረገ፤ በልባቸው
ዐሳብ የሚታበዩትንም በተናቸው። ፶፪ ኀያላኑን
ከዙፋናቸው አዋረዳቸው፤ ትሑታኑንም ከፍ
ከፍ አደረጋቸው። ፶፫ የተራቡትን ከበረከቱ አጠ
ገባቸው፤ ባለጠጎችንም ባዶ እጃቸውን ሰደዳ
ቸው። ፶፬ ብላቴናውን እስራኤልን ተቀበለው፤
ይቅርታውንም ዐሰበ። ፶፭ ለአባቶቻችን ለአብርሃ
ምና ለዘሩ እስከ ዘለዓለም እንደ ተናገረው።"

፩ አንዳንድ የግእዝ ትርጉም "ከሁለት ቀኖች በኋላ" ይላል።
፪ "ደስ ያለሽ" የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።
፫ ግእዙ "ደወለ ዐይነ ከርም" ይላል።
፬ በግሪኩ "ከእግዚአብሔር የተነገረላት ይፈጸማልና የምታምን ብፅዕት ናት" ይላል።
፭ በግሪኩ "ብርቱ የሆነ እርሱ ለእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና" ይላል።
፩፥፳፯ ማቴ. ፩፥፲፰። ፩፥፴፩ ማቴ. ፩፥፳፩። ፩፥፴፪-፴፫ ፪ሳሙ. ፯፥፲፪-፲፫፤ ፲፮፤ ኢሳ. ፱፥፯።
፩፥፵፯ ዘፍ. ፲፰፥፲፬። ፩፥፵፮-፶፭ ፩ሳሙ. ፪፥፩-፲። ፩፥፵፰ ፩ሳሙ. ፩፥፲፩። ፩፥፶፪ ኢዮብ ፭፥፲፩፤ ፲፪፥፲፱።
፩፥፶፭ ዘፍ. ፲፯፥፯።

፶፮ማርያምም ሦስት ወር ያህል በእርስዋ
ዘንድ ተቀመጠች፤ ከዚህ በኋላም ወደ ቤቷ
ተመለሰች።

### ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ልደት

፶፯የኤልሣቤጥም የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ፤
ወንድ ልጅም ወለደች። ፶፰ዘመዶችዋና ጎረቤ
ቶችዋም እግዚአብሔር ቸርነቱን እንዳበዛላት
በሰሙ ጊዜ ከእርስዋ ጋር ደስ አላቸው። ፶፱ከዚ
ህም በኋላ በስምንተኛው ቀን ሕፃኑን ሊገዝሩት
መጡ፤ በአባቱም ስም ዘካርያስ ብለው ጠሩት።
፷እናቱ ግን መልሳ፥ "አይሆንም፥ ዮሐንስ
ይባል እንጂ" አለች። ፷፩እነርሱም፥ "ከዘመዶ
ችሽ ስሙ እንደዚህ የሚባል የለም" አሉአት።
፷፪አባቱንም ጠቅሰው፥ "ማን ሊሉት ትወዳ
ለህ?" አሉት። ፷፫ብራናም ለመነና "ስሙ ዮሐ
ንስ ይባል" ብሎ ጻፈ፤ ሁሉም አደነቁ። ፷፬ያን
ጊዜም አፉ ተከፈተ፤ አንደበቱም ተናገረ፤ እግ
ዚአብሔርንም አመሰገነ። ፷፭በዚያም ሀገር ሰው
ሁሉ ላይ ፍርሀት ሆነ፤ ይህም ነገር ሁሉ በይ
ሁዳ በተራራማው ሀገር ሁሉ ተወራ። ፷፮የሰ
ሙትም ሁሉ፥ "እንግዲህ ይህ ሕፃን ምን
ይሆን?" እያሉ በልባቸው አኖሩት፤ የእግዚአ
ብሔር እጅ በእርሱ ላይ ነበረችና።
፷፯በአባቱ በዘካርያስም መንፈስ ቅዱስ
መላበት፤ እንዲህም ብሎ ትንቢት ተናገረ፡-
፷፰"ይቅር ያለን፥ ለወገኖቹም ድኅነትን ያደረገ
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን፤
፷፱ከባርያው ከዳዊት ቤት የምንድንበትን ቀንድ
አስነሣልን፤ ፸ከጥንት ጀምሮ በነበሩ በቅዱሳን
በነቢያት አፍ እንደ ተናገረ። ፸፩ከጠላቶቻችን
እጅ፥ ከሚጠሉንም ሁሉ እጅ ያድነን ዘንድ።
፸፪ቸርነቱን ከአባቶቻችን ጋር ያደርግ ዘንድ፥
ቅዱስ ኪዳኑንም ያስብ ዘንድ። ፸፫ለአባታችን
ለአብርሃም የማለውን መሐላ ያስብ ዘንድ።
፸፬ከጠላቶቻችን እጅ ድነን ያለ ፍርሀት፥ ፸፭በቅ
ድስናና በጽድቅ በፊቱ በዘመናችን ሁሉ እንድ
ናመልከው ይሰጠን ዘንድ። ፸፮አንተም ሕፃን፥
የልዑል ነቢይ ትባላለህ፤ መንገዱን ትጠርግ
ዘንድ በፊቱ ትሄዳለህና። ፸፯ኀጢአታቸው ይሰ
ረይላቸው ዘንድ መድኀኒታቸውን እንዲያውቁ
ለአሕዛብ ትሰጣቸው ዘንድ። ፸፰ከአርያም በጐ
በኛን በአምላካችን በይቅርታውና በቸርነቱ።
፸፱በጨለማና በሞት ጥላ ለነበሩት ብርሃኑን ያሳ
ያቸው ዘንድ፥ እግሮቻችንንም ወደ ሰላም ጎዳና
ያቀና ዘንድ ወጣ።" ፹ሕፃኑም አደገ፤ በመን
ፈስ ቅዱስም ጸና፤ ለእስራኤልም እስከታየበት
ቀን ድረስ በምድረ በዳ ኖረ።

## ምዕራፍ ፪

### ስለ ሕዝብ ቈጠራ

፩በዚያም ወራት እንዲህ ሆነ፤ ሰው ሁሉ
ይቈጠር ዘንድ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ
ወጣ። ፪ቄሬኔዎስ ለሶርያ መስፍን በነበረ ጊዜ
ይህ የመጀመርያ ቈጠራ ሆነ። ፫ሰው ሁሉ ሊቈ
ጠር ወደየከተማው ሄደ። ፬ዮሴፍም ከገሊላ
አውራጃ ከናዝሬት ከተማ ወደ ይሁዳ፥ ቤተ
ልሔም ወደምትባለው ወደ ዳዊት ከተማ ወጣ፤
እርሱም ከዳዊት ሀገርና፩ ከዘመዶቹ ወገን ነበ
ርና። ፭ፀንሳ ሳለች ከእጮኛው ከማርያም ጋር
ይቈጠር ዘንድ ሄደ።

### ስለ ጌታችን መወለድ

(ማቴ. ፩፥፲፰-፳፭)

፮በዚያ ሳሉም የምትወልድበት ቀን ደረሰ።
፯የበኵር ልጅዋንም ወለደች፤ አውራ ጣቱንም
አሰረችው፤፪ በጨርቅም ጠቀለለችው፤ በበረ
ትም አስተኛችው፤ በማደርያቸው ቦታ አልነበ
ራቸውምና። ፰በዚያ ሀገር እረኞች ነበሩ፤ ሌሊ
ቱንም ተግተው መንጋቸውን ይጠብቁ ነበር።
፱እነሆም፥ የእግዚአብሔር መልአክ በአጠገባ
ቸው ቆመ፤ የእግዚአብሔርም ብርሃን በዙሪያ
ቸው አበራ፤ ታላቅ ፍርሀትንም ፈሩ። ፲መል
አኩም እንዲህ አላቸው፥ "እነሆ፥ ለእናንተና
ለሕዝቡ ሁሉ ደስታ የሚሆን ታላቅ የምሥራች
እነግራችኋለሁና አትፍሩ። ፲፩እነሆ፥ ዛሬ በዳ
ዊት ከተማ መድኀን ተወልዶላችኋል፤ ይኸ
ውም ቡሩክ ጌታ ክርስቶስ ነው። ፲፪ለእናንተም
ምልክቱ እንዲህ ነው፡- ሕፃን አውራ ጣቱን
ታስሮ፥፫ በጨርቅም ተጠቅልሎ በበረት ውስጥ
ተኝቶ ታገኛላችሁ።" ፲፫ድንገትም ከዚያ መል
አክ ጋር ብዙ የሰማይ ሠራዊት እግዚአብሔርን
እያመሰገኑ መጡ። ፲፬"ክብር ለእግዚአብሔር

፩ በግሪኩ "ከዳዊት ቤትና" ይላል።
፪ "አውራ ጣቱንም አሰረችው" የሚለው በግሪኩ የለም።
፫ "አውራ ጣቱን ታስሮ" የሚለው በግሪኩ የለም።
፩፥፶፱ ዘሌ. ፲፪፥፫። ፩፥፸፮ ሚል. ፫፥፩።

በሰማያት፥ ሰላምም በምድር፥ ለሰው ልጅም
በጎ ፈቃድ ሆነ” ይሉ ነበር።
፲፭ከዚህም በኋላ መላእክት ከእነርሱ ዘንድ
ወደ ሰማይ በዐረጉ ጊዜ እነዚያ እረኞች ሰዎች
እርስ በርሳቸው፥ “እስከ ቤተ ልሔም እን
ሂድ፤ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን ነገር
እንወቅ” አሉ። ፲፮ፈጥነውም ሄዱ፤ ማርያምንና
ዮሴፍን አገኙአቸው፤ ሕፃኑንም በበረት ውስጥ
ተኝቶ አገኙት። ፲፯በአዩም ጊዜ የነገሩአቸው
ስለዚህ ሕፃን እንደ ሆነ ዐውቀው አወሩ። ፲፰የሰ
ሙትም ሁሉ እረኞቹ የነገሩአቸውን አደነቁ።
፲፱ማርያም ግን ይህን ሁሉ ትጠብቀው፥ በል
ብዋም ታኖረው ነበር። ፳እረኞችም እንደ ነገሩ
አቸው ባዩትና በሰሙት ሁሉ እግዚአብሔርን
እያከበሩና እያመሰገኑ ተመለሱ።

## ስለ ሕፃኑ መገዘርና ወደ ቤተ መቅደስ መግባት

፳፩ስምንት ቀን በተፈጸመ ጊዜም ሕፃኑን ሊገ
ዝሩት ወሰዱት፤ በማኅፀንዋ ሳትፀንሰው መል
አኩ እንዳወጣለትም ስሙን ኢየሱስ አሉት።
፳፪የመንጻታቸውም ወራት በተፈጸመ ጊዜ እንደ
ሙሴ ሕግ በእግዚአብሔር ፊት ያቆሙት ዘንድ
ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት። ፳፫“በኵር ሆኖ የሚ
ወለድ ወንድ ልጅ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተ
ቀደሰ ይባላል” ተብሎ በእግዚአብሔር ሕግ
እንደ ተጻፈ፥ ፳፬በእግዚአብሔርም ሕግ እንደ
ታዘዘ ሁለት ዋኖስ ወይም ሁለት የርግብ ግል
ገሎች ስለ እርሱ መሥዋዕት አድርገው ያቀር
ቡለት ዘንድ።

## ስለ አረጋዊው ስምዖን

፳፭በኢየሩሳሌምም ስሙ ስምዖን የሚባል
አንድ ሰው ነበር፤ እርሱም ጻድቅና ደግ ሰው
ነበር፤ እርሱም የእስራኤልን ደስታቸውን ያይ
ዘንድ ተስፋ ያደርግ ነበር፤ መንፈስ ቅዱስም
ያደረበት ነበር። ፳፮የእግዚአብሔርንም መሲሕ
ሳያይ እንደማይሞት መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት
ነበር። ፳፯መንፈስም ወደ ቤተ መቅደስ ወሰ
ደው፤ ዘመዶቹም በሕግ የተጻፈውን ያደርጉ
ለት ዘንድ ሕፃኑን ጌታችን ኢየሱስን ወደ ቤተ
መቅደስ በአገቡት ጊዜ፥ ፳፰እርሱ ደግሞ ተቀ
ብሎ በክንዱ ታቀፈው፤ እግዚአብሔርንም
አመሰገነው። ፳፱እንዲህም አለ፤ “አቤቱ፥ እንደ
አዘዝህ ዛሬ ባርያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ።
፴ዐይኖቼ ትድግናህን አይተዋልና። ፴፩በወገንህ
ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን፥ ፴፪ለአሕዛብ ብርሃ
ንን፥ ለወገንህ ለእስራኤልም ክብርን ትገልጥ
ዘንድ።” ፴፫ዮሴፍና እናቱ ግን በእርሱ ላይ
ስለሚናገረው ያደንቁ ነበር። ፴፬ስምዖንም ባረ
ካቸው፤ እናቱን ማርያምንም እንዲህ አላት፤
“እነሆ፥ ይህ ሕፃን ከእስራኤል መካከል ለብ
ዙዎች ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው፥ ለሚ
ቃወሙትም ምልክት ይሆን ዘንድ የተሠየመ
ነው፤ ፴፭ባንቺ ግን በልብሽ ፍላጻ ይገባል፤ የብ
ዙዎቹን ዐሳብ ይገልጥ ዘንድ።”

## ስለ ነቢይቱ ሐና

፴፮ከአሴር ወገን የምትሆን የፋኑኤል ልጅ
ሐና የምትባል ነቢይት ነበረች፤ አርጅታም
ነበር፤ ከድንግልናዋም በኋላ ከባል ጋር ሰባት
ዓመት ኖረች። ፴፯ሰማንያ አራት ዓመትም መበ
ለት ሆና ኖረች፤ በጾምና በጸሎትም እያገለገ
ለች፥ ቀንም ሆነ ሌሊት ከቤተ መቅደስ አት
ወጣም ነበር። ፴፰ያንጊዜም ተነሥታ እግዚአብ
ሔርን አመሰገነች፤ የኢየሩሳሌምንም ድኅነት
ተስፋ ለሚያደርጉ ሁሉ ስለ እርሱ ተናገረች።
፴፱በእግዚአብሔርም ሕግ የተጻፈውን ሁሉ
ከፈጸሙ በኋላ ወደ ገሊላ ወደ ከተማቸው ወደ
ናዝሬት ተመለሱ። ፵ሕፃኑም አደገ፤ በመንፈ
ስም ጠነከረ፤ ጥበብንም የተመላ ነበር፤ የእግዚ
አብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረች።

## በሊቃውንት መካከል ስለ መገኘቱ

፵፩ዘመዶቹም በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል ወደ
ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር። ፵፪ዐሥራ ሁለት ዓመ
ትም በሞላው ጊዜ እንደ አስለመዱ ወደ ኢየ
ሩሳሌም ለበዓል ወጡ። ፵፫፩ሥራቸውንም ጨር
ሰው ተመለሱ፤ ሕፃኑ ጌታችን ኢየሱስ ግን
በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር፤ ዮሴፍና እናቱም
አላወቁም ነበር። ፵፬በመንገድም ከሰዎች ጋር
ያለ መስሎአቸው ነበር፤ ያንድ ቀን መንገድ
ንም ከሄዱ በኋላ ዕለቱን ከዘመዶቹ፥ ከሚያው
ቁትም ዘንድ ፈለጉት። ፵፭ባላገኙትም ጊዜ እየ
ፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። ፵፮ከዚህም
በኋላ በሦስተኛው ቀን በቤተ መቅደስ በሊቃ

፩ ግሪኩ “ቀኖቹንም ከፈጸሙ በኋላ” ይላል።

፪፥፳፩ ዘሌ. ፲፪፥፫፤ ሉቃ. ፩፥፴፩። ፪፥፳፪-፳፬ ዘሌ. ፲፪፥፮-፰። ፪፥፳፫ ዘፀ. ፲፫፥፪፤ ፲፪።

፪፥፴፱ ማቴ. ፪፥፳፫። ፪፥፵፩ ዘፀ. ፲፪፥፩-፳፯፤ ዘዳ. ፲፮፥፩-፰።

ውንት መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውና ሲጠይ
ቃቸው አገኙት። ፵፯የሰሙትም ሁሉ አስተዋይ
ነቱንና አመላለሱን ያደንቁ ነበር። ፵፰በአዩትም
ጊዜ ደነገጡ፤ እናቱም፥ "ልጄ፥ ለምን እንዲህ
አደረግኸን? እነሆ አባትህም፥፩ እኔም ስንፈል
ግህ ደከምን" አለችው። ፵፱እርሱም፥ "ለምን
ትፈልጉኛላችሁ? በአባቴ ቤት ልኖር እንደሚገ
ባኝ አላወቃችሁምን?" አላቸው። ፶እነርሱ ግን
የነገራቸውን ቃል አላስተዋሉም። ፶፩ከእነርሱም
ጋር ሂዶ ወደ ናዝሬት ወረደ፤ ይታዘዝላቸውም
ነበር፤ እናቱ ግን ይህን ሁሉ ነገር ትጠብቀው፥
በልብዋም ታኖረው፪ ነበር። ፶፪ጌታችን ኢየሱ
ስም በእግዚአብሔር ዘንድ፥ በሰውም ዘንድ፥
በጥበብና በአካል በሞገስም አደገ።

## ምዕራፍ ፫

### ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ስብከት

(ማቴ. ፫፥፩-፲፪፤ ማር. ፩፥፩-፰)

፩ጢባርዮስ ቄሣር በነገሠ በዐሥራ አምስት
ዓመት ጴንጤናዊው ጲላጦስ የይሁዳ ገገር ሆኖ
ሳለ፥ ሄሮድስም በገሊላ የአራተኛው ክፍል ገገር
ሳለ፥ ወንድሙ ፊልጶስም የኢጡርያስና የጥራኮ
ኒዶስ አራተኛ ክፍል ገዢ፥ ሊሳንዮስም የሳብ
ላኒስ አራተኛ ክፍል ገገር ሆነው ሳሉ፥ ፪ሐናና
ቀያፋም ሊቃነ ካህናት በነበሩበት ወራት የእ
ግዚአብሔር ቃል በምድረ በዳ ወደ ዘካርያስ
ልጅ ወደ ዮሐንስ መጣ። ፫ስለ ኀጢአት ስር
የት ለንስሓ የሚያበቃ ጥምቀትን እየሰበከ በዮ
ርዳኖስ አውራጃ ዞረ። ፬በምድረ በዳ የሚጮኽ
የአዋጅ ነጋሪ ድምፅ በነቢዩ በኢሳይያስ መጽ
ሐፍ ቃል እንደ ተጻፈ፥ እንዲህ ሲል፥ "የእ
ግዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ፤ ጥርጊያውንም
አስተካክሉ። ፭ጐድጓዳው ሁሉ ይምላ፤ ተራራ
ውም፥ ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይበል፤ ሰንከ
ልካላውም የቀና ጥርጊያ ይሁን፤ ወጣ ገባው
መንገድም ይስተካከል። ፮ሰውም ሁሉ የእግዚ
አብሔርን ትድግና ይይ።"

፯ዮሐንስም ሊያጠምቃቸው የመጡትን ሰዎች
እንዲህ አላቸው፥ "እናንት የእፉኝት ልጆች፥
ከሚመጣው መቅሠፍት ታመልጡ ዘንድ ማን
ነገራችሁ? ፰እንግዲህ ለንስሓ የሚያበቃችሁን
ሥራ ሥሩ፤ አብርሃም አባታችን አለን በማ
ለት የምታመልጡ አይምሰላችሁ፤ እግዚአብ
ሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆችን
ማስነሣት እንደሚችል እነግራችኋለሁ። ፱እነሆ፥
ምሳር በዛፎች ላይ ተቃጥቶአል፤ መልካም ፍሬ
የማያፈራውንም ዛፍ ሁሉ ይቈርጡታል፤ ወደ
እሳትም ይጥሉታል።"

፲ሕዝቡም፥ "እንግዲህ ምን እናድርግ?"
ብለው ጠየቁት። ፲፩እርሱም መልሶ እንዲህ
አላቸው፥ "ሁለት ልብስ ያለው አንዱን ለሌ
ለው ይስጥ፤ ምግብ ያለውም እንዲሁ ያድ
ርግ።" ፲፪ቀራጮችም ሊያጠምቃቸው መጡና፥
"መምህር፥ ምን እናድርግ?" ብለው ጠየቁት።
፲፫እርሱም፥ "ከታዘዛችሁት አትርፋችሁ አት
ውሰዱ" አላቸው። ፲፬ጭፍሮችም መጥተው፥
"እኛሳ ምን እናድርግ?" አሉት፤ "በደመወዛ
ችሁ ኑሩ እንጂ በማንም ግፍ አትሥሩ፤ ማን
ንም አትቀሙ፤ አትበድሉም" አላቸው።

፲፭ሕዝቡም ሁሉ በልባቸው ዐሰቡ፤ ዮሐንስም
ክርስቶስ እንደ ሆነ መሰላቸው። ፲፮ዮሐንስም መልሶ
ሁሉንም እንዲህ አላቸው፥ "እኔ በውኃ አጠም
ቃችኋለሁ፤ ግን የሚበልጠኝ የጫማውን ማሰሪያ
እንኳ ልፈታለት የማይገባኝ ይመጣል፤ እርሱ በመ
ንፈስ ቅዱስ፥ በእሳትም ያጠምቃችኋል። ፲፯መንሹ
በእጁ ነው፤ የዐውድማውንም እህል ያጠራል፤
ስንዴውንም በጎተራው ይሰበስባል፤ ገለባውን ግን
በማይጠፋ እሳት ያቃጥላል።"

፲፰ሕዝቡንም ይገሥጻቸውና በሌላም በብዙ
ነገር የምሥራች ይነግራቸው ነበር።

### ስለ ዮሐንስ መጥምቅ መታሰር

፲፱ዮሐንስም የአራተኛው ክፍል ገዢ ሄሮድ
ስን የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ሄሮድያዳን
ስለማግባቱና ሄሮድስ ያደርገው ስለነበረው ክፉ
ነገር ሁሉ ይገሥጸው ነበር። ፳ደግሞም ከዚህ
ሁሉ በላይ ጨምሮ ዮሐንስን ተቀየመውና በግ
ዞት ቤት አስገባው።

### ጌታችን ስለ መጠመቁ

(ማቴ. ፫፥፲፫-፲፯፤ ማር. ፩፥፱-፲፩)

፳፩ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ጌታ
ችን ኢየሱስም ተጠመቀ፤ ሲጸልይም

፩ "አባት" የተባለ አሳዳጊው ስለሆነ ነው።

፪ "ታኖረው ነበር" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪፥፶፪ ፩ሳሙ. ፪፥፳፮፤ ምሳ. ፫፥፬። ፫፥፬-፮ ኢሳ. ፵፥፫-፭። ፫፥፯ ማቴ. ፲፪፥፴፬፤ ፳፫፥፴፫።
፫፥፰ ዮሐ. ፰፥፴፫። ፫፥፱ ማቴ. ፯፥፲፱። ፫፥፲፪ ሉቃ. ፯፥፳፱። ፫፥፲፱-፳ ማቴ. ፲፬፥፫-፬።

ሰማይ ተከፈተ። ፳፪መንፈስ ቅዱስም የር
ግብ መልክ ባለው አካል አምሳል በእርሱ
ላይ ወረደ፤ ከሰማይም፥ “የምወድህ፥ በአን
ተም ደስ የሚለኝ ልጄ አንተ ነህ” የሚል
ቃል መጣ።

## ስለ ጌታችን ትውልድ መጽሐፍ

(ማቴ. ፩፥፩-፲፯)

፳፫የጌታችን ኢየሱስም[፩] ዕድሜዉ ሠላሳ
ዓመት ያህል ነበር፤ የዮሴፍ ልጅም ይመስ
ላቸው ነበር። ፳፬የኤሊ ልጅ፥ የማቲ ልጅ፥
የሌዊ ልጅ፥ የሚልኪ ልጅ፥ የዮና ልጅ፥
የዮሴፍ ልጅ፥ ፳፭የማታትዩ ልጅ፥ የአሞጽ
ልጅ፥ የናሆም ልጅ፥ የኤስሎም ልጅ፥
የናጌ ልጅ፥ ፳፮የማአት ልጅ፥ የማታትዩ
ልጅ፥ የሴሜይ ልጅ፥ የዮሴፍ ልጅ፥ የዮዳ
ልጅ፥ ፳፯የዮናን ልጅ፥ የሬስ ልጅ፥ የዘ
ሩባቤል ልጅ፥ የሰላትያል ልጅ፥ የኔሪ
ልጅ፥ ፳፰የሚልኪ ልጅ፥ የሐዲ ልጅ፥
የዮሳ ልጅ፥ የቆሳም ልጅ፥ የኤልሞዳም
ልጅ፥ የኤር ልጅ፥ ፳፱የዮሴዕ ልጅ፥ የአ
ልዓዛር ልጅ፥ የዮራም ልጅ፥ የማጣት
ልጅ፥ የሌዊ ልጅ፥ ፴የስምዖን ልጅ፥ የይ
ሁዳ ልጅ፥ የዮሴፍ ልጅ፥ የዮናን ልጅ፥
የኤልያቄም ልጅ፥ ፴፩የሜልያ ልጅ፥ የማይ
ናን ልጅ፥ የማጣት ልጅ፥ የናታን ልጅ፥
የዳዊት ልጅ፥ ፴፪የዕሤይ ልጅ፥ የኢዮቤድ
ልጅ፥ የቦዔዝ ልጅ፥ የሰልሞን ልጅ፥ የነ
ዓሶን ልጅ፥ ፴፫የአሚናዳብ ልጅ፥ የአራም
ልጅ፥ የአርኒ ልጅ፥ የኤስሮም ልጅ፥ የፋ
ሬስ ልጅ፤ የይሁዳ ልጅ፥ ፴፬የያዕቆብ ልጅ፥
የይስሐቅ ልጅ፥ የአብርሃም ልጅ፥ የታራ
ልጅ፥ የናኮር ልጅ፥ ፴፭የሴሩኅ ልጅ፥ የራ
ግው ልጅ፥ የፋሌቅ ልጅ፥ የኤቦር ልጅ፥
የሳላ ልጅ፥ ፴፮የቃይናን ልጅ፥ የአርፋክስድ
ልጅ፥ የሴም ልጅ፥ የኖኅ ልጅ፥ የላሜሕ
ልጅ፥ ፴፯የማቱሳላ ልጅ፥ የሄኖክ ልጅ፥ የያ
ሬድ ልጅ፥ የመላልኤል ልጅ፥ የቃይናን
ልጅ፥ ፴፰የሄኖስ ልጅ፥ የሴት ልጅ፥ የአ
ዳም ልጅ፥ የእግዚአብሔር ልጅ።

## ምዕራፍ ፬

## በዲያብሎስ ስለ መፈተኑ

(ማቴ. ፬፥፩--፲፩፤ ማር. ፩፥፲፪፡፲፫)

፩ጌታችን ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስን ተመ
ልቶ ከዮርዳኖስ ተመለሰ፤ መንፈስም ወደ
ምድረ በዳ ወሰደው። ፪አርባ መዓልትና አርባ
ሌሊት ከዲያብሎስ ተፈተነ፥ በእነዚያም ቀኖች
ምንም አልበላም፤ እነዚያም ቀኖች ከተፈጸሙ
በኋላ ተራበ። ፫ዲያብሎስም፥ “አንተ የእግ
ዚአብሔር ልጅ ከሆንህስ ይህ ድንጋይ እን
ጀራ ይሁን በል” አለው። ፬ጌታችን ኢየሱስም
መልሶ፥ “ሰው የሚኖረው ከእግዚአብሔር አፍ
በሚወጣው ቃል ነው እንጂ በእንጀራ ብቻ አይ
ደለም የሚል ተጽፎአል” አለው። ፭ዲያብሎ
ስም ወደ ረዥም ተራራ አወጣው፤ የዓለምን
መንግሥታትም ሁሉ በቅፅበት አሳየው። ፮ዲያ
ብሎስም እንዲህ አለው፥ “ይህን ሁሉ ግዛት፥
ይህንም ክብር ለአንተ እሰጥሃለሁ፤ ለእኔ ተሰ
ጥቶአልና፤ ለወደድሁትም እሰጠዋለሁና። ፯ስለ
ዚህ አንተ በፊቴ ብትሰግድልኝ ይህ ሁሉ ለአ
ንተ ይሁንልህ።” ፰ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥
“ሰይጣን ከኋላዬ ሂድ[፪] ለእግዚአብሔር ለአም
ላክህ ልትሰግድ፥ እርሱንም ብቻ ልታመልክ
ተጽፎአል” አለው። ፱ወደ ኢየሩሳሌምም ወስዶ
በቤተ መቅደሱ የማዕዘን ጫፍ ላይ አቆመው፤
እንዲህም አለው፥ “የእግዚአብሔር ልጅ ከሆን
ህስ አንተ ራስህ ወደ ታች መር ብለህ ውረድ።
፲በመንገድህ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክትን ስለ
አንተ ያዝዛቸዋል፤ ፲፩እግርህም በድንጋይ እንዳ
ትሰነካከል በእጃቸው ያነሡሃል” ተብሎ ተጽ
ፎአልና። ፲፪ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ “ፈጣ
ሪህ እግዚአብሔርን አትፈታተነው” ተብሎ
አል አለው። ፲፫ዲያብሎስም በዚህ ሁሉ እር
ሱን መፈታተኑን ከፈጸመ በኋላ እስከ ጊዜው
ከእርሱ ተለየ።

## ስለ መጀመሪያ ትምህርቱ

(ማቴ. ፬፥፲፪-፲፯፤ ማር. ፩፥፲፬-፲፭)

፲፬ጌታችን ኢየሱስም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል
ተመልሶ ወደ ገሊላ ሄደ፤ ዝናውም በሀገሩ

---

፩ ግሪኩ “ማስተማር ሲጀምር” የሚል ይጨምራል።

፪ በግሪኩና በአንዳንድ የግእዝ ትርጉም “ሰይጣን ከኋላዬ ሂድ” የሚለውን የሚጽፍም የማይጽፍም አለ።

፫፥፳፪ ዘፍ. ፳፪፥፪፤ መዝ. ፪፥፯፤ ኢሳ. ፵፪፥፩፤ ማቴ. ፫፥፲፯፤ ማር. ፩፥፲፩፤ ሉቃ. ፱፥፴፭   ፬፥፬ ዘዳ. ፰፥፫።
፬፥፰ ዘዳ. ፮፥፲፫።   ፬፥፲ መዝ. ፺፥፲፩።   ፬፥፲፩ መዝ. ፺፥፲፪።   ፬፥፲፪ ዘዳ. ፮፥፲፮።

ሁሉ ተሰማ። ፲፭በየምኵራባቸውም ሁሉ ያስተ
ምራቸው ነበር፤ ትምህርቱንም ያደንቁ ነበር፤
ሁሉም ያመሰግኑት ነበር።

### በናዝሬት ስለ ማስተማሩ
(ማቴ. ፲፫፥፶፫-፶፰፤ ማር. ፮፥፩-፮)

፲፮ወደ አደገበት ወደ ናዝሬትም ሄደ፤ በሰን
በት ቀንም እንዳስለመደ ወደ ምኵራብ ገባ፤
ሊያነብም ተነሣ። ፲፯የነቢዩን የኢሳይያስንም
መጽሐፍ ሰጡት፤ መጽሐፉንም በገለጠ ጊዜ እን
ዲህ የሚል የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ። ፲፰"የእግ
ዚአብሔር መንፈስ በላዬ ነው፤ ስለዚህ ቀብቶ
ለድሆች የምሥራችን እነግራቸው ዘንድ፥ ለተ
ማረኩትም ነጻነትን እሰብክላቸው ዘንድ፥ ያዘኑ
ትንም ደስ አሰኛቸው ዘንድ፥ ዕውሮችም ያዩ
ዘንድ፥ የተገፉትንም አድናቸው ዘንድ፥ የታ
ሰሩትንም እፈታቸው ዘንድ፥ የቈሰሉትንም
እፈውሳቸው ዘንድ፥ ፲፱የተመረጠችውንም የእ
ግዚአብሔርን ዓመት እሰብክ ዘንድ ላከኝ።"
፳መጽሐፉንም አጥፎ ለተላላኪው ሰጠውና ተቀ
መጠ፤ በምኵራብም የነበሩት ሁሉ ዐይናቸውን
አትኵረው ተመለከቱት። ፳፩እርሱም፥ "የዚህ
የመጽሐፍ ነገር ዛሬ በጆሮአችሁ ደረሰ፤ ተፈጸ
መም" ይላቸው ጀመር። ፳፪ሁሉም የንግግሩን
መከናወን መሰከሩለት፤ የአንደበቱንም ቅልጥፍና
እያደነቁ፥ "ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን?"
ይሉ ነበር። ፳፫እርሱም፥ "በውኑ ባለ መድኀ
ኒት ራስህን አድን፤ በቅፍርናሆም ያደረግኸው
ንና የሰማነውን ሁሉ በዚህም በሀገርህ ደግሞ
አድርግ ብላችሁ ይህችን ምሳሌ ትመስሉብኛላ
ችሁ" አላቸው። ፳፬እንዲህም አላቸው፥ "እው
ነት እላችኋለሁ፤ ነቢይ በሀገሩ አይከብርም።
፳፭እውነት እላችኋለሁ፤ በነቢዩ በኤልያስ ዘመን
በምድር ሁሉ ብርቱ ረኃብ እስኪሆን ድረስ
ሰማይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር በተዘጋበት
ጊዜ ብዙ መበለቶች በእስራኤል ውስጥ ነበሩ።
፳፮ኤልያስ የሲዶና ክፍል በምትሆን በስራጵታ
ወደምትኖር ወደ አንዲት መበለት ሴት እንጂ
ከእነዚህ ወደ አንዲቱ እንኳን አልተላከም። ፳፯በነ
ቢዩ በኤልሳዕ ዘመንም ብዙ ለምጻሞች በእስራ
ኤል ውስጥ ነበሩ፤ ነገር ግን ከሶርያዊው ከንዕ
ማን በቀር ከእነዚያ አንድ እንኳን አልነጻም።"
፳፰በምኵራብም የነበሩት ሁሉ ይህን ሰም
ተው ተቈጡ። ፳፱ያንጊዜም ተነሥተው ከከ
ተማ ወደ ውጭ አወጡት፤ ገፍተውም ይጥ
ሉት ዘንድ ከተማቸው ተሠርታባት ወደ ነበ
ረች ተራራ ጫፍ ወሰዱት። ፴እርሱ ግን በመ
ካከላቸው አልፎ ሄደ።

### ወደ ቅፍርናሆም ስለ መሄዱ

፴፩ወደ ገሊላ ከተማም ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፤
በሰንበትም ያስተምራቸው ነበር። ፴፪አነጋገሩም
በትእዛዝ ነበርና ትምህርቱን ያደንቁ ነበር።

### ጋኔን የያዘውን ስለ ማዳኑ
(ማር. ፩፥፳፩-፳፰)

፴፫በምኵራብም ርኩስ መንፈስ የያዘው አንድ
ሰው ነበር፤ በታላቅ ቃልም ጮኸ፦ ፴፬"የናዝ
ሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን?
ያለጊዜአችን ልታጠፋን መጣህን? የእግዚአብ
ሔር ቅዱስ ሆይ፥ አንተ ማን እንደሆንህ ዐው
ቅሃለሁ" አለ። ፴፭ጌታችን ኢየሱስም፥ "ዝም
በልና ከእርሱ ውጣ" ብሎ ገሥጸው፤ ጋኔኑም
በምኵራቡ መካከል ጣለውና ከእርሱ ወጣ፤
ነገር ግን ምንም አልጐዳውም። ፴፮ሁሉም ደነ
ገጡ፤ እርስ በርሳቸውም ተነጋገሩ፤ እንዲህም
አሉ፥ "ይህ ነገር ምንድን ነው? ክፉዎችን
አጋንንት በሥልጣንና በኀይል ያዝዛቸዋልና፥
እነርሱም ይወጣሉና።" ፴፯ዝናውም በዙሪያዉ
ባሉ መንደሮች ሁሉ ወጣ፤ ተሰማም።

### ስለ ጴጥሮስ አማትና ስለ ሌሎችም በሽተኞች መፈወስ
(ማቴ. ፰፥፲፬-፲፯፤ ማር. ፩፥፳፱-፴፬)

፴፰ከምኵራቡም ወጥቶ ወደ ስምዖን ቤት
ገባ፤ የስምዖን አማትም በብርቱ ንዳድ ታማ
ነበርና ስለ እርስዋ ነገሩት። ፴፱በአጠገብዋም
ቆሞ ንዳድዋን ገሥጸውና ተዋት፤ ወዲያውም
ተነሥታ አገለገለቻቸው። ፵ፀሐይም በገባ ጊዜ
ልዩ ልዩ ደዌ ያለባቸውን ድውያን ሁሉ አመ
ጡለት፤ ከእነርሱም በእያንዳንዱ ላይ እጁን
ጭኖ ፈወሳቸው። ፵፩ብዙ አጋንንትም፥ "አንተ
የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ" እያሉና
እየጮሁ ይወጡ ነበር፤ እርሱም ይገሥጻቸው
ነበር፤ ክርስቶስም እንደ ሆነ ያውቁ ነበርና እን
ዲናገሩ አይፈቅድላቸውም ነበር።
፵፪በነጋ ጊዜም ወጥቶ ወደ ምድረ በዳ
ሄደ፤ ሕዝቡም እየፈለጉት ወደ እርሱ

፬፥፲፰-፲፱ ኢሳ. ፷፩፥፩-፪። ፬፥፳፬ ዮሐ. ፬፥፵፬። ፬፥፳፭ ፩ነገ. ፲፯፥፰-፲፮። ፬፥፳፯ ፪ነገ. ፭፥፩-፲፬።
፬፥፴፪ ማቴ. ፯፥፳፰-፳፱።

ሄዱ፤ አልፎአቸው እንዳይሄድም አቆሙት።
፵፫እርሱ ግን፥ "ስለዚህ ተልኬአለሁና ለሌ
ሎች ከተሞች ደግሞ ስለ እግዚአብሔር
መንግሥት ወንጌል እነግራቸው ዘንድ ይገ
ባኛል" አላቸው። ፵፬በገሊላ ምኵራቦችም
ይሰብክ ነበር።

## ምዕራፍ ፭

### ስለ ስምዖንና ስለ ዘብዴዎስ ልጆች መጠራት
(ማቴ. ፬፥፲፰-፳፪፤ ማር. ፩፥፲፮-፳)

፩ብዙ ሰዎችም በእርሱ ዘንድ ነበሩ፤ የእ
ግዚአብሔርንም ቃል ይሰሙ ነበር፤ እርሱ
ግን በጌንሴሬጥ ባሕር ወደብ ቁሞ ነበር።
፪በባሕሩም ዳር ሁለት ታንኳዎች ቁመው
አየ፤ ከእነርሱም ውስጥ ዓሣ አጥማጆች
መረባቸውን ሊያጥቡ ወረዱ። ፫ከሁለቱ ታን
ኳዎች ወደ አንዲቱ ታንኳ ወጣ፤ ይቺውም
ታንኳ የስምዖን ነበረች፤ "ከምድር ጥቂት
እልፍ አድርጋት" አለው፤ በታንኳዪቱም
ውስጥ ተቀምጦ ሕዝቡን አስተማራቸው።
፬ትምህርቱንም ከፈጸመ በኋላ ስምዖንን፥
"ወደ ጥልቁ ባሕር ፈቀቅ በል፤ መረቦቻች
ሁንም ለማጥመድ ጣሉ" አለው። ፭ስምዖ
ንም መልሶ፥ "መምህር፥ ሌሊቱን ሁሉ ደክ
መናል፤ የያዝነውም የለም፤ ነገር ግን ስለ
አዘዝኸን መረቦቻችንን እንጥላለን" አለው።
፮እንዳዘዛቸውም ባደረጉ ጊዜ፥ መረቡ እስኪ
ቀደድ ድረስ ብዙ ዓሣ ተያዘ። ፯መጥተውም
ይረዱአቸው ዘንድ በሌላ ታንኳ የነበሩትን
ባልንጀሮቻቸውን ጠሩ፤ መጥተውም እስ
ኪጠልቁ ድረስ ሁለቱን ታንኳዎች ሞሉ።
፰ስምዖን ጴጥሮስም ይህን አይቶ ከጌታችን
ከኢየሱስ እግር በታች ሰገደና፥ "እኔ ኀጢ
አተኛ ሰው ነኝና አቤቱ ከእኔ ፈቀቅ በል፤"
አለው። ፱እርሱና ከእርሱ ጋር የነበሩት ሁሉ
ስለ ተያዘው ዓሣ ተደንቀው ነበርና። ፲እንዲ
ሁም የስምዖን ባልንጀራዎች የነበሩ የዘብዴ
ዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ ተደነቁ፤ ጌታ
ችን ኢየሱስም ስምዖንን፥ "አትፍራ፤ ከእን
ግዲህ ወዲህስ ሰውን ታጠምዳለህ" አለው።
፲፩ታንኳዎቻቸውንም ወደ ምድር አወጡና
ሁሉን ትተው ተከተሉት።

### ለምጻሙን ስለ ማዳኑ
(ማቴ. ፰፥፩-፬፤ ማር. ፩፥፵-፵፭)

፲፪በአንዲት ከተማ ሳለም ሁለመናው ለምጻም
የሆነ ሰው መጣ፤ ጌታችን ኢየሱስንም ባየው
ጊዜ በፊቱ ወድቆ ሰገደለትና፥ "አቤቱ ብት
ወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ" እያለ ማለደው።
፲፫እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፥ "እወዳለሁ ንጻ"
አለው፤ ያንጊዜም ለምጹ ለቀቀው። ፲፬ለማንም
እንዳይናገር ከለከለው፤ "ነገር ግን ሄደህ ራስ
ህን ለካህን አስመርምር፤ ምስክርም ይሆንባ
ቸው ዘንድ ስለ ነጻህ ሙሴ እንደ አዘዘ መባ
ህን አቅርብ" ብሎ አዘዘው። ፲፭ዜናውም በሁሉ
ተሰማ፤ ብዙ ሰዎችም ትምህርቱን ሊሰሙ፥
ከደዌአቸውም ሊፈወሱ ይመጡ ነበር። ፲፮እርሱ
ግን ወደ ምድረ በዳ እየወጣ ይጸልይ ነበር።

### ስለ መጻጉዕ መፈወስ
(ማቴ. ፱፥፩-፰፤ ማር. ፪፥፩-፲፪)

፲፯ከዚህም በኋላ፥ ከዕለታት በአንድ ቀን ሲያ
ስተምራቸው እንዲህ ሆነ፤ ከገሊላና ከይሁዳ
መንደሮች፥ ከኢየሩሳሌምም የመጡ ፈሪሳውያ
ንና የኦሪት መምህራን ነበሩ፤ እርሱም ይፈውስ
ዘንድ የእግዚአብሔር ኀይል ነበረ። ፲፰እነሆ፥
ሰዎች በአልጋ ተሸክመው ሽባ የሆነ ሰው ወደ
እርሱ አመጡ፤ እንዲፈውሰውም ወደ እርሱ
ሊያስገቡት ወደዱ። ፲፱ሰውም ተጨናንቆ ነበርና
የሚያስገቡበት አጡ፤ ወደ ሰገነትም ወጡ፤
ጣራውንም አፍርሰው ወደ ቤቱ ውስጥ በጌ
ታችን በኢየሱስ ፊት ከነአልጋው አወረዱት።
፳እምነታቸውንም አይቶ ያን ሰው፥ "ኀጢ
አትህ ተሰረየልህ" አለው። ፳፩ጻፎችና ፈሪሳ
ውያንም፥ "የሚሳድብ ይህ ማን ነው? ከአ
ንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኀጢአትን ማስተ
ስረይ ማን ይችላል?" ብለው ያስቡ ጀመር።
፳፪ጌታችን ኢየሱስም የሚያስቡትን ዐወቀባቸ
ውና እንዲህ አላቸው፥ "በልባችሁ ምን ታስ
ባላችሁ? ፳፫ኀጢአትህ ተሰረየልህ ከማለትና
ተነሥተህ ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል?
፳፬ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን ያስተ
ሰርይ ዘንድ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፤
ያን ሽባ፦ ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ወደ
ቤትህ ሂድ ብዬሃለሁ" አለው። ፳፭ያንጊዜም
ተነሥቶ ተኝቶበት የነበረውን አልጋ በፊታቸው

፭፥፩-፫ ማቴ. ፲፫፥፩-፪፤ ማር. ፫፥፱-፲፤ ፬፥፩። ፭፥፭ ዮሐ. ፳፩፥፫። ፭፥፮ ዮሐ. ፳፩፥፮።
፭፥፲፬ ዘሌ. ፲፬፥፩-፴፪።

ተሽክሞ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ቤቱ
ሄደ። ፳፮ሁሉም ተደነቁ፤ እግዚአብሔርንም
አመሰገኑት፤ እጅግም እየፈሩ፥ "ዛሬ ድንቅ
ነገር አየን" አሉ።

### ስለ ቀራጩ ሌዊ መጠራት

(ማቴ. ፱፥፱-፲፫፤ ማር. ፪፥፲፫-፲፯)

፳፯ከዚህም በኋላ ከዚያ ወጥቶ ሌዊ የሚባል
ቀራጭ ሰው በቀረጥ መቀበያው ቦታ ተቀምጦ
አየና፥ "ተከተለኝ" አለው። ፳፰ሁሉንም ተወና
ተነሥቶ ተከተለው። ፳፱ሌዊም በቤቱ ታላቅ
ግብዣ አደረገለት፤ ብዙ ሰዎችም ከእርሱ ጋር
ነበሩ፤ ከእርሱም ጋር ለምሳ ተቀምጠው የነበሩ
ቀራጮችና ኀጢአተኞች፥ ሌሎችም ብዙዎች
ነበሩ። ፴ጸፎችና ፈሪሳውያንም፥ "ከቀራጮችና
ከኃጥኣን ጋር ለምን ትበላላችሁ? ትጠጡማላ
ችሁ?" ብለው በደቀ መዛሙርቱ ላይ አንጐራ
ጐሩ። ፴፩ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላ
ቸው፥ "ባለ መድኀኒትን በሽተኞች እንጂ ጤነ
ኞች አይሹትም። ፴፪ኃጥኣንን ወደ ንስሓ እንጂ
ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም።"

### ስለ ጾም

(ማቴ. ፱፥፲፬-፲፯፤ ማር. ፪፥፲፰-፳፪)

፴፫እነርሱም፥ "የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለ
ምን በብዙ ይጾማሉ? ጸሎትስ ስለምን ያደር
ጋሉ? የፈሪሳውያን ወገኖች የሆኑትም ስለምን
እንዲሁ ያደርጋሉ? ያንተ ደቀ መዛሙርት ግን
ለምን ይበላሉ? ይጠጣሉም?" አሉት። ፴፬ጌታ
ችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ "የሙ
ሽራው ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ
መጾም አይችሉም። ፴፭ነገር ግን ሙሽራውን
ከእነርሱ የሚወስዱበት ቀን ይመጣል፤ ያንጊ
ዜም ይጾማሉ።" ፴፮በምሳሌም እንዲህ አላቸው፥
"በአሮጌ ልብስ ቀዳዳ ላይ የአዲስ ልብስ እራፊ
የሚጥፍ የለም፤ ያለዚያ ግን አዲሱ አሮጌውን
ይቀድደዋል፤ አዲሱ እራፊም ከአሮጌው ጋር
አይስማማም። ፴፯አዲስ የወይን ጠጅንም በአ
ሮጌ ረዋት የሚያደርግ የለም፤ ያለዚያ ግን ይቀ
ድደዋል፤ ወይኑም ይፈስሳል፤ ረዋቱም ይቀደ
ዳል። ፴፰ነገር ግን አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ
ረዋት ያደርጉታል፤ እርስ በርሳቸውም ይጠባ
በቃሉ። ፴፱የከረመውን የወይን ጠጅ ሊጠጣ
ወድዶ አዲሱን የሚሻ የለም፤ የከረመው ይሻ
ላል ይላልና።"

## ምዕራፍ ፮

### ስለ ሰንበት

(ማቴ. ፲፪፥፩-፰፤ ማር. ፪፥፳፫-፳፰)

፩ከዚህም በኋላ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ በሰ
ንበት ቀን በእርሻ መካከል ሄደ፤ ደቀ መዛ
ሙርቱም እሸት ቈርጠው በእጃቸው እያሹ
በሉ። ፪ፈሪሳውያንም፥ "በሰንበት ሊደረግ የማ
ይገባውን ለምን ታደርጋላችሁ?" አሉአቸው።
፫ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥
"እርሱና ከእርሱ ጋር የነበሩትም በተራቡ ጊዜ
ዳዊት ያደረገውን አላነበባችሁምን? ፬ወደ ቤተ
እግዚአብሔር እንደ ገባ፥ ከካህናቱም ብቻ
በቀር ሊበሉት የማይገባውን የመሥዋዕቱን ኅብ
ስት ወስዶ እንደ በላ፥ አብረውት ለነበሩትም
እንደ ሰጣቸው አላነበባችሁምን? ፭የሰው ልጅ
ለሰንበት ጌታዋ ነው" አላቸው።

### እጁ ስለ ደረቀችው ሰው

(ማቴ. ፲፪፥፱-፲፬፤ ማር. ፫፥፩-፮)

፮ከዚህም በኋላ በሌላይቱ ሰንበት ወደ ምኵ
ራቡ ገባና አስተማራቸው፤ በዚያም ቀኝ እጁ
የሰለለች ሰው ነበረ። ፯ጻፎችና ፈሪሳውያንም
የሚከሱበት ምክንያት ያገኙ ዘንድ፥ በሰንበት
ይፈውሰው እንደ ሆነ ብለው ይጠባበቁት ነበር።
፰እርሱ ግን ዐሳባቸውን ያውቅባቸው ነበርና
እጁ የሰለለችውን ሰው፥ "ተነሥተህ በመካከል
ቁም" አለው፤ ተነሥቶም ቆመ። ፱ጌታችን ኢየ
ሱስም እንዲህ አላቸው፥ "እጠይቃችኋለሁ፤
በሰንበት ሊደረግ የሚገባው ምንድነው? መል
ካም መሥራት ነውን? ወይስ ክፉ መሥራት?
ነፍስን ማዳን ነውን? ወይስ መግደል?" ፲እነ
ርሱም ዝም አሉ፤ ወደ እነርሱም ዞሮ ከተ
መለከተ በኋላ፦ ያን ሰው፥ "እጅህን ዘርጋ"
አለው፤ ሰውዬውም ዘረጋት፤ እጁም ዳነችና
እንደ ሁለተኛይቱ ሆነች። ፲፩እነርሱ ግን፥ እጅግ
ተቈጡ፤ በጌታችን በኢየሱስም ምን እንድሚያ
ደርጉበት እርስ በርሳቸው ተማከሩ።

### ሐዋርያትን ስለ መምረጡ

(ማቴ. ፲፥፩-፬፤ ማር. ፫፥፲፫-፲፱)

፲፪በዚያም ወራት ጌታችን ኢየሱስ ሊጸልይ
ወደ ተራራ ወጣ፤ ሌሊቱን ሁሉ ወደ እግዚአ
ብሔር ይጸልይ ነበር፤ ፲፫ሲነጋም ደቀ መዛሙ

፭፥፴ ሉቃ. ፲፭፥፩-፪። ፮፥፩ ዘዳ. ፳፫፥፳፭። ፮፥፫-፬ ፩ሳሙ. ፳፩፥፩-፮። ፮፥፬ ዘሌ. ፳፬፥፱።

ርቱን ወደ እርሱ ጠራቸው፤ ከውስጣቸውም
ዐሥራ ሁለቱን መረጠ፤ ሐዋርያት ብሎም ሰየ
ማቸው። [፲፬]እነርሱም እነዚህ ናቸው፦ ጴጥሮስ
የተባለው ስምዖን፥ ወንድሙም እንድርያስ፥
ያዕቆብና ዮሐንስ፥ ፊልጶስና በርተሎሜዎስ።
[፲፭]ማቴዎስና ቶማስ፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብና
ቀናዒ የሚባለው ስምዖን። [፲፮]የያዕቆብ ወንድም
ይሁዳ፥ የከዳውና[፩] አሳልፎ የሰጠው ያስቆሮቱ
ሰው ይሁዳም ናቸው።

[፲፯]ከእነርሱም ጋር ወርዶ በሰፊ ቦታ ቆመ፤
ከደቀ መዛሙርቱም ወገን ብዙ ሰዎች ነበሩ፤
ከመላው ይሁዳና ከኢየሩሳሌም፥ ከጢሮስና
ከሲዶና ባሕር ዳርቻ ትምህርቱን ሊሰሙ፥ ከደ
ዌአቸውም ሊፈወሱ የመጡት ከሕዝቡ ወገን
እጅግ ብዙዎች ነበሩ። [፲፰]ከፉዎች አጋንንት
ያደሩባቸውም ይፈወሱ ነበር። [፲፱]ሕዝቡ ሁሉ
ሊዳስሱት ይሹ ነበር፤ ኀይል ከእርሱ ይወጣ
ነበርና፥ ሁሉንም ይፈውሳቸው ነበር።

### በተራራ ላይ ስለ አስተማረው ትምህርት
(ማቴ. ፭፥፩-፲፪)

[፳]እርሱም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዐይኖቹን አን
ሥቶ እንዲህ አላቸው፥ "እናንተ ድሆች፥ ብፁ
ዓን ናችሁ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ
ናትና። [፳፩]ዛሬ የምትራቡ፥ ብፁዓን ናችሁ፤ ትጠ
ግባላችሁና፤ ዛሬ የምታለቅሱ፥ ብፁዓን ናችሁ፤
ትስቃላችሁና። [፳፪]ሰዎች ስለ ሰው ልጅ ቢጠሉ
አችሁ፥ ከሰው ለይተው ቢአሳድዱአችሁ፥ ቢሰ
ድቡአችሁ፥ ክፉ ስምም ቢአወጡላችሁ ብፁ
ዓን ናችሁ። [፳፫]ያንጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ በደስ
ታም ዝለሉ፤ ዋጋችሁ በሰማይ ብዙ ነውና፤
አባቶቻቸውም ነቢያትን እንዲሁ አድርገዋቸው
ነበርና። [፳፬]ነገር ግን እናንተ ባለጠጎች፥ ወዮላ
ችሁ፥ ደስታችሁን ጨርሳችኋልና። [፳፭]ዛሬ ለም
ትጠግቡ፥ ወዮላችሁ፥ ትራባላችሁና፤ ዛሬ ለም
ትስቁም ወዮላችሁ፥ ታዝናላችሁና፤ ታለቅሳላች
ሁምና። [፳፮]ሰዎች ሁሉ ስለ እናንተ መልካሙን
ነገር ቢናገሩላችሁ ወዮላችሁ፥ አባቶቻቸው ለሐ
ሰተኞች ነቢያት እንዲህ ያደርጉ ነበርና።

[፳፯]"ለምትሰሙኝ ለእናንተ ግን እንዲህ እላ
ችኋለሁ፦ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚጠሉአ
ችሁም መልካም አድርጉ። [፳፰]የሚረግሙአች
ሁን መርቁአቸው፤ ለሚበድሉአችሁም ጸልዩላ
ቸው። [፳፱]ጉንጭህን ለሚመታህም ሁለተኛይቱን
ስጠው፤ መጐናጸፊያህን ለሚወስድም ቀሚስ
ህን ደግሞ አትከልክለው። [፴]ለሚለምንህም ሁሉ
ስጥ፤ ገንዘብህን የሚወስደውንም እንዲመልስ
አትጠይቀው። [፴፩]ሰዎች ሊያደርጉላችሁ እንደ
ምትወዱትም እንዲሁ እናንተ አድርጉላቸው።
[፴፪]የሚወድዱአችሁን ብቻ ብትወዱማ እንግዲህ
ዋጋችሁ ምንድን ነው? ይህንስ ኃጥአንም ያደ
ርጋሉ፤ የሚወድዳቸውንም ይወድዳሉ። [፴፫]በጎ
ለሚያደርጉላችሁ በጎ ብታደርጉ እንግዲህ ዋጋ
ችሁ ምንድን ነው? እንዲህስ ኃጥአንም ያደር
ጋሉ። [፴፬]እንዲከፍላችሁ ተስፋ ለምታደርጉት
ብታበድሩ እንግዲህ ዋጋችሁ ምንድን ነው?
ኃጥአንም በአበደሩት ልክ ይከፍሉአቸው ዘንድ
ለኃጥአን ያበድራሉና። [፴፭]አሁንም ጠላቶቻች
ሁን ውደዱ፤ መልካምም አድርጉላቸው፤ እን
ዲመልሱላችሁ ተስፋ ሳታደርጉ አበድሩ፤ ዋጋ
ችሁም ብዙ ይሆናል፤ የልዑልም ልጆች ትሆ
ናላችሁ፤ እርሱ ለበጎዎችና[፪] ለክፉዎች ቸር
ነውና። [፴፮]ሰማያዊ[፫] አባታችሁ የሚራራ እንደ
ሆነ እናንተም የምትራሩ ሁኑ። [፴፯]አትፍረዱ፥
አይፈረድባችሁምም፤ አትበድሉ፥ አይበድሉአ
ችሁምም፤ ይቅር በሉ፥ ይቅርም ይሉአችኋል።
[፴፰]ስጡ፥ ይሰጣችኋልም፤ የሞላና የበዛ፥ የተት
ረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በዕቅፋችሁ ይሰ
ጡአችኋል፤ በሰፈራችሁበትም መስፈሪያ ይሰ
ፍሩላችኋል።"

[፴፱]ምሳሌም መሰለላቸውና እንዲህ አላቸው፥
"ዕውር ዕውርን ሊመራ ይችላልን? ሁለቱስ
በጕድጓድ ውስጥ ይወድቁ የለምን? [፵]ከመ
ምህሩ የሚበልጥ ደቀ መዝሙር የለም፤ ለሁ
ሉም መጠኑ እንደ መምህሩ ይሆናል። [፵፩]በወ
ንድምህ ዐይን ውስጥ ያለውን ጕድፍ ለምን
ታያለህ? በዐይንህ ውስጥ ያለውን ምሰሶ አታ
ይምን? [፵፪]ወንድምህንም፦ ወንድሜ ሆይ፥
ታገሥ፤ በዐይንህ ያለውን ጕድፍ ላውጣልህ
ልትለው እንደምን ትችላለህ? አንተ ግን በዐ
ይንህ ውስጥ ያለውን ምሰሶ አታይም፤ አንተ
ግብዝ፥ አስቀድሞ ከዐይንህ ምሰሶውን አውጣ፤

---

፩ "የከዳውና" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ በግሪኩ "ለማያመሰግኑና" ይላል።

፫ በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ "ሰማያዊ" የሚለው አይገኝም።

፮፥፳፪ ፩ጴጥ. ፬፥፲፬። ፮፥፳፫ ፪ዜመ. ፴፮፥፲፮፤ ሐሥ. ፯፥፶፪። ፮፥፴፩ ማቴ. ፯፥፲፪። ፮፥፴፱ ማቴ. ፲፭፥፲፬።
፮፥፵ ማቴ. ፲፥፳፬-፳፭፤ ዮሐ. ፲፫፥፲፮፤ ፲፭፥፳።

ከዚህ በኋላ በባልንጀራህ ዐይን ውስጥ ያለውን
ጉድፍ ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ። ፵፫ክፉ
ፍሬን የሚያፈራ መልካም ዛፍ የለም፤ መል
ካም ፍሬ የሚያፈራ ክፉ ዛፍም የለም። ፵፬ዛፍ
ሁሉ ከፍሬው ይታወቃል፤ ከእሾህ በለስን አይ
ለቅሙም፤ ከደንደርም ወይንን አይለቅሙም።
፵፭መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መል
ካምን ያወጣል፤ ክፉ ሰውም ከልቡ ክፉ መዝ
ገብ ክፉ ነገርን ያወጣል፤ ከልብ የተረፈውን
አፍ ይናገራልና።

፵፮"ለምን አቤቱ፥ አቤቱ፥ ትሉኛላችሁ?
የምላችሁንም አታደርጉም። ፵፯ወደ እኔ የሚመ
ጣና ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገውም ሁሉ የሚ
መስለውን አሳያችኋለሁ። ፵፰መሠረቱን አጥልቆ
ቈፍሮ የመሠረተና ቤቱን በዐለት ላይ የሠራ
ሰውን ይመስላል፤ ብዙ ፈሳሾች በመጡ ጊዜ
ጎርፎች ያን ቤት ገፉት፤ ሊያነዋውጡትም አል
ቻሉም፤ በዐለት ተሠርቶአልና። ፵፱ቃሌን ሰምቶ
የማያደርገው ሰው ግን ቤቱን ያለ መሠረት
በአፈር ላይ የሠራ ሰውን ይመስላል፤ ጎርፎች
ገፉት፤ ወዲያውኑም ወደቀ፤ የዚያም ቤት አወ
ዳደቁ ታላቅ ሆነ።"

## ምዕራፍ ፯

### የመስፍኑ ሎሌ እንደ ዳነ
(ማቴ. ፰፥፭-፲፫)

፩ለሕዝቡም ቃሉን ነግሮ ከፈጸመ በኋላ ወደ
ቅፍርናሆም ገባ። ፪አንድ የመቶ አለቃም ነበረ፤
አገልጋዩም ታሞ ሊሞት ቀርቦ ነበር፤ እርሱም
በእርሱ ዘንድ የተወደደ ነበር። ፫የጌታችን የኢ
የሱስንም ነገር በሰማ ጊዜ፥ መጥቶ አገልጋ
ዩን እንዲያድንለት ይማልዱት ዘንድ የአይሁ
ድን ሽማግሎች ወደ እርሱ ላከ። ፬ወደ ጌታ
ችን ወደ ኢየሱስም መጥተው ማለዱት፤ እንዲ
ህም አሉት፥ "ፈጥነህ ውረድ፤[፩] ይህን ልታደ
ርግለት ይገባዋልና። ፭እርሱ ወገናችንን ይወዳ
ልና፤ ምኵራባችንንም ሠርቶልናልና።" ፮ጌታ
ችን ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ሄደ፤ ወደ ቤቱም
በቀረበ ጊዜ፥ የመቶ አለቃዉ ወዳጆቹን እንዲህ
ብሎ ላከ፥ "አቤቱ፥ አትድከም፤ ከቤቴ ጣራ
በታች ልትገባ አይገባኝምና። ፯እኔም ወደ አንተ
ልመጣ አይገባኝም፤ ነገር ግን በቃልህ እዘዝ፤
ብላቴናዬም ይድናል። ፰እኔም እኮ ገዢ ሰው
ነኝ፤ ወታደሮችም አሉኝ፤ አንዱን ሂድ ብለው
ይሄዳል፤ ሌላውንም ና ብለው ይመጣል፤ አገ
ልጋዬንም እንዲህ አድርግ ብለው ያደርጋል።"
፱ጌታችን ኢየሱስም ይህን ከእርሱ በሰማ ጊዜ
አደነቀው፤ ዘወር ብሎም ይከተሉት ለነበሩት
ሕዝብ፥ "እላችኋለሁ፥ በእስራኤልስ እንኳ እን
ዲህ ያለ እምነት ያለው ሰው አላገኘሁም" አላ
ቸው። ፲የተላኩትም በተመለሱ ጊዜ ብላቴና
ውን ድኖ አገኙት።

### ስለ መበለቲቱ ልጅ መዳን

፲፩በማግሥቱም ናይን ወደምትባል ወደ አን
ዲት ከተማ ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም ብዙ
ሕዝብም አብረውት ሄዱ። ፲፪ወደ ከተማው
በር በደረሰ ጊዜም እነሆ፥ ያንዲት መበለት
ሴት ልጅ ሙቶ ሬሳውን ተሸክመው ሲሄዱ
አገኙ፤ ይኸውም ለእናቱ አንድ ነበረ፤ ብዙዎ
ችም የከተማ ሰዎች አብረዋት ነበሩ። ፲፫ጌታ
ችንም በአያት ጊዜ አዘነላትና፥ "አታልቅሺ"
አላት። ፲፬ቀርቦም ቃሬዛውን ያዘ፤ የተሸከሙ
ትም ቆሙ፤ እርሱም፥ "አንተ ጐበዝ ተነሥ
እልሃለሁ" አለው። ፲፭የሞተውም ተነሥቶ ተቀ
መጠ፤ መናገርም ጀመረ፤ ለእናቱም ሰጣት።
፲፮ሁሉም ፈሩ፤ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ፤
እንዲህም አሉ፥ "ታላቅ ነቢይ ተነሣልን፤ እግ
ዚአብሔር ሕዝቡን ጐብኝቶአልና።" ፲፯ይህም
የእርሱ ዜና በይሁዳ ሀገሮች ሁሉና በአውራ
ጃዋ ሁሉ ተሰማ።

### ከዮሐንስ ስለ ተላኩት መልእክተኞች
(ማቴ. ፲፩፥፪-፲፱)

፲፰ይህንም ሁሉ ደቀ መዝሙርቱ ለዮሐንስ
ነገሩት። ፲፱ዮሐንስም ከደቀ መዛሙርቱ ሁለ
ቱን ጠርቶ፥ "የሚመጣው አንተ ነህን? ወይስ
ተስፋ የምናደርገው ሌላ አለ?" ብሎ ወደ
ጌታችን ወደ ኢየሱስ ላካቸው። ፳መልእክተኞ
ችም ወደ እርሱ ደርሰው፥ "የሚመጣው አንተ
ነህን? ወይስ ተስፋ የምናደርገው ሌላ አለ?
ብሎ መጥምቁ ዮሐንስ ወደ አንተ ልኮናል"
አሉት። ፳፩ያንጊዜም ብዙዎችን ከደዌአቸውና
ከሕመማቸው ከክፉዎች አጋንንትም ፈወሳ
ቸው፤ ለብዙዎች ዕውራንም እንዲያዩ ብርሃ
ንን ሰጣቸው። ፳፪ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እን
ዲህ አላቸው፥ "ሄዳችሁ ያያችሁትንና የሰማች

[፩] "ፈጥነህ ውረድ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፮፥፵፬ ማቴ. ፲፪፥፴፫። ፮፥፵፭ ማቴ. ፲፪፥፴፬። ፯፥፳፪ ኢሳ. ፴፭፥፭-፮፤ ፷፩፥፩።

ሁትን ለዮሐንስ ንገሩት፤ ዕውሮች ያያሉ፤ አን
ካሶችም ይሄዳሉ፤ ለምጻሞችም ይነጻሉ፤ ደን
ቆሮችም ይሰማሉ፤ ሙታንም ይነሣሉ፤ ለድሆ
ችም ወንጌል ይሰበካል። ፳፫በእኔም የማይሰና
ከል ብፁዕ ነው።”

### ጌታ መጥምቁ ዮሐንስን ስለ ማመስገኑ

፳፬የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትም ከሄዱ በኋላ
ለሕዝቡ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ እንዲህ ይላ
ቸው ጀመር፥ “ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ
ወጣችሁ? ከነፋስ የተነሣ የሚወዛወዝ ሸንበ
ቆን ነውን? ፳፭ወይስ ምን ልታዩ ወጥታችኋል?
ቀጭን ልብስ የለበሰውን ሰው ነውን? እነሆ፥
በክብር ልብስ ያጌጡስ በነገሥታት ቤት አሉ።
፳፮ወይስ ምን ልታዩ ወጥታችኋል? ነቢይን
ነውን? አዎን፥ እላችኋለሁ፤ ከነቢይም ይበ
ልጣል። ፳፯እነሆ፥ መንገድህን በፊትህ የሚጠ
ርግ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ፥ ተብሎ
ስለ እርሱ የተጻፈለት ይህ ነው። ፳፰እውነት
እላችኋለሁ፤ ሴቶች ከወለዱአቸው መካከል
ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ ማንም አልተነ
ሣም፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ግን የሚያን
ሰው ይበልጠዋል።” ፳፱ሕዝቡም ሁሉ ቀራጮ
ችም በሰሙ ጊዜ እግዚአብሔርን ጻድቅ ነው
አሉት፤ የዮሐንስን ጥምቀት ተጠምቀው ነበ
ርና። ፴ፈሪሳውያንና የሕግ ጻፎች ግን የእግዚ
አብሔርን ትእዛዝ[፪] ተቃወሙ፤ በእርሱ አልተ
ጠመቁምና።

፴፩“እንግዲህ የዚችን ትውልድ ሰዎች
በምን እመስላቸዋለሁ? ማንንስ ይመስላሉ?
፴፪በገበያ ተቀምጠው ባልንጀሮቻቸውን ጠር
ተው፥ “አቀነቀንላችሁ፥[፫] አልዘፈናችሁ
ምም፤ ሙሾም አወጣንላችሁ፥ አላለቀሳች
ሁምም የሚሉአቸው ልጆችን ይመስላሉ።
፴፫መጥምቁ ዮሐንስ እህል ሳይበላ ወይንም
ሳይጠጣ መጥቶ ነበርና ጋኔን አለበት አላ
ችሁት። ፴፬የሰው ልጅም እየበላና እየጠጣ
መጣ፤ እናንተ ግን እነሆ፥ በላተኛና ወይን
ጠጪ ሰው፥ የኃጥአንና የቀራጮች ወዳጅ
አላችሁት። ፴፭ጥበብም ከልጆችዋ ሁሉ ጸደ
ቀች።”

### ስለ ፈሪሳዊውና ስለ ኀጢአተኛዪቱ ሴት

፴፮ከፈሪሳውያንም አንዱ በእርሱ ዘንድ ምሳ
እንዲበላ ለመነው፤ ወደ ፈሪሳዊውም ቤት
ገብቶ በማዕድ ተቀመጠ። ፴፯እነሆ፥ ከዚያች
ከተማ ሰዎችም አንዲት ኀጢአተኛ ሴት በፈ
ሪሳዊው ቤት በማዕድ እንደተቀመጠ ዐውቃ
ሽቱ የሞላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ ገዝታ
መጣች። ፴፰በስተኋላውም በእግሮቹ አጠገብ
ቆማ አለቀሰች፤ እግሮቹንም በእንባዋ ታርስ
ነበር፥ በራስ ጠጕርዋም እግሮቹን ታብሰውና
ትስመው፥ ሽቱም ትቀባው ነበር። ፴፱የጠራው
ፈሪሳዊም ባየ ጊዜ በልቡ ዐሰበ፤ እንዲህም
አለ፥ “ይህስ ነቢይ ቢሆን ኖሮ ይህቺ የምትዳ
ስሰው ሴት ማን እንደ ሆነች፥ እንዴትስ እንደ
ነበረች ባላወቀም ነበርን? ኀጢአተኛ ናትና።”
፵ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ “ስምዖን ሆይ፥
የምነግርህ ነገር አለኝ” አለው፤ እርሱም፥
“መምህር ሆይ፥ ተናገር” አለው። ፵፩እርሱም
እንዲህ አለው፥ “ለአንድ አበዳሪ ሁለት ባለ
ዕዳዎች ነበሩት፤ በአንዱ አምስት መቶ ዲናር
ነበረበት፤ በሁለተኛውም አምሳ። ፵፪የሚከፍሉ
ትም ባጡ ጊዜ ለሁለቱም ተወላቸው፤ እንግ
ዲህ ከሁለቱ አብልጦ ሊወደው የሚገባው ማን
ኛው ነው?” ፵፫ስምዖንም መልሶ፥ “ብዙውን
የተወለት ነው እላለሁ” አለው፤ እርሱም፥
“መልካም ፈረድህ” አለው። ፵፬ወደ ሴቲቱም
ዘወር ብሎ ስምዖንን እንዲህ አለው፥ “ይህ
ቺን ሴት ታያታለህን? እኔ ወደ ቤትህ ገባሁ፤
ለእግሮቼ ውኃ ስንኳ አልሰጠኸኝም፤ እርስዋ
ግን አልቅሳ በእንባዋ እግሬን አራሰች፤ በጠ
ጕርዋም አበሰች። ፵፭አንተስ ሰላምታ አልሰጠ
ኸኝም፤ እርስዋ ግን ከገባሁ ጀምሮ እግሬን
ከመሳም አላቋረጠችም። ፵፮አንተ ራሴን እንኳ
ዘይት አልቀባኸኝም፤ እርስዋ ግን እግሬን ሽቱ
ቀባችኝ። ፵፯ስለዚህም እልሃለሁ፤ ብዙ ኀጢ
አቷ ተሰርዮላታል፤ በብዙ ወድዳለችና፤ ጥቂት
የሚወድድ ጥቂት ይሰረይለታል፤ ብዙ የሚወ
ድድም ብዙ ይሰረይለታል።”[፬] ፵፰ሴቲቱንም፥
“ኀጢአትሽ ተሰረየልሽ” አላት። ፵፱በማዕዱ
የተቀመጡትም እርስ በርሳቸው፥ “ኀጢአትን

---

፪ በግሪኩ “ምክር” ይላል።

፫ በግሪኩ “እምቢልታ ነፋንላችሁ” ይላል።

፬ “ብዙ የሚወድድ ብዙ ይሰረይለታል” የሚለው በግሪኩ የለም።

፯፥፳፯ ሚል. ፫፥፩። ፯፥፳፱-፴ ማቴ. ፳፩፥፴፪፤ ሉቃ. ፫፥፲፪።

፯፥፴፯-፴፰ ማቴ. ፳፮፥፯፤ ማር. ፲፬፥፫፤ ዮሐ. ፲፪፥፫።

የሚያስተሰርይ ይህ ማነው?" ይሉ ጀመር።
፶ሴቲቱንም አላት፥ "እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰ
ላም ሂጂ።"

## ምዕራፍ ፰

### ጌታችን የገሊላን አውራጃዎች ተዘዋውሮ ስለ ማስተማሩ

፩ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ በየከተማ
ዉና በየመንደሩ ተመላለሰ፤ የእግዚአብሔርንም
መንግሥት ሰበከላቸው፤ አስተማራቸውም፤
ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርትም ከእርሱ ጋር
ነበሩ። ፪ከክፉዎች አጋንንትና ከደዌያቸው ያዳ
ናቸው ሴቶችም አብረውት ነበሩ። እነርሱም፦
መግደላዊት የምትባለው ሰባት አጋንንት የወጡ
ላት ማርያም፥ ፫የሄሮድስ አዛዥ የነበረው የኩዛ
ሚስት ዮሐና፥ ሶስናም፥ በገንዘባቸው ያገለግ
ሉት፩ የነበሩ ብዙዎች ሌሎችም ነበሩ።

### ስለ ዘሪው ምሳሌ

(ማቴ. ፲፫፥፩-፱፤ ማር. ፬፥፩-፱)

፬ሕዝቡም ሁሉ፥ ከየከተማዉም ሁሉ ወደ
እርሱ የመጡት ሲያዳምጡት እንዲህ ያለ
ምሳሌ ነገራቸው። ፭"ዘሪ ዘሩን ሊዘራ ወጣ፤
ሲዘራም አንዳንዱ በመንገድ ወደቀና ተረገጠ፤
የሰማይ ወፎችም በሉት። ፮ሌላውም በጭንጫ
መሬት ላይ ወደቀ፤ በበቀለም ጊዜ ወዲያው
ደረቀ፤ ሥር አልነበረውምና። ፯ሌላዉም በእ
ሾህ መካከል ወደቀ፤ እሾሁም አብሮ አደገና
አነቀው። ፰በመልካም መሬት ላይ የወደቀ ዘርም
ነበረ፤ በበቀለም ጊዜ መቶ እጥፍ አፈራ።"
ይህንም ብሎ፥ "የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ"
አላቸው።

፱ደቀ መዛሙርቱም፥ "ይህቺ ምሳሌ ምን
ድን ናት?" ብለው ጠየቁት። ፲እርሱም እን
ዲህ አላቸው፥ "የእግዚአብሔርን መንግሥት
ምሥጢር ማወቅ ለእናንተ ተሰጥቶአችኋል፤
ለእነዚያ ግን አይተው እንዳያዩ፥ ሰምተውም
እንዳይሰሙ፥ እንዳያስተውሉም በምሳሌ ነው።
፲፩ምሳሌዉም ይህ ነው፤ ዘሩ የእግዚአብሔር
ቃል ነው፤ ፲፪በመንገድ የወደቀው ቃሉን የሚ
ሰሙ ናቸው፤ አምነውም እንዳይድኑ ሰይጣን
መጥቶ ቃሉን ከልባቸው ይወስድባቸዋል።
፲፫በጭንጫም ላይ የወደቀው ሰምተው ነገሩን
በደስታ የሚቀበሉት ናቸው፤ ነገር ግን ለጊዜው
ያምናሉ እንጂ ሥር የላቸውም፤ መከራም በአገ
ኛቸው ጊዜ ይክዳሉ። ፲፬በእሾህም መካከል የወ
ደቀው ቃሉን ሰምተው የባለጠግነት ዐሳብ፥ የኑ
ሮም መቈርቈር የተድላና የደስታ መጣፈጥም
የሚአስጨንቃቸውና ፍሬ የማያፈሩ ናቸው።
፲፭በመልካም ምድር የወደቀው ግን ቃሉን በበ
ጎና በንጹሕ ልብ የሚሰሙና የሚጠብቁት፥
ታግሠውና ጨክነውም የሚያፈሩ ናቸው።

፲፮"መብራትን አብርቶ፥ ዕቃም ከድኖ ከአ
ልጋ በታች የሚያኖራት የለም፤ ነገር ግን የሚ
መላለሱት ብርሃንን ያዩ ዘንድ በመቅረዝ ላይ
ያኖራታል። ፲፯የማይገለጥ የተሰወረ የለምና፤
የማይታይም ወደ ግልጥም የማይመጣ የተከደነ
የለም፤ ፲፰እንግዲህ እንዴት እንደምትሰሙ አስ
ተውሉ፤ ላለው ይሰጠዋል፤ ከሌለው ግን ያው
ያለው የሚመስለው እንኳ ይወሰድበታል።"

### ወንድሞቹ ስለሚባሉት የተናገረው

(ማቴ. ፲፪፥፵፮-፶፤ ማር. ፫፥፴፩-፴፭)

፲፱እናቱና ወንድሞቹም ወደ እርሱ መጡ፤
ነገር ግን ሕዝቡ ብዙ ነበርና ሊያገኙት አልቻ
ሉም። ፳"እናትህና ወንድሞችህ ከውጭ ቆመ
ዋል፤ ሊያዩህም ይሻሉ" አሉት። ፳፩እርሱም
መልሶ፥ "እናቴና ወንድሞቼ የእግዚአብሔርን
ቃል ሰምተው የሚያደርጉ እነዚህ ናቸው" አላ
ቸው።

### ባሕርን ስለ መገሠጹ

(ማቴ. ፰፥፳፫-፳፯፤ ማር. ፬፥፴፭-፵፩)

፳፪ከዕለታት በአንዲት ቀንም እንዲህ ሆነ፤
እርሱ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ታንኳ
ወጣና፥ "ኑ ወደ ባሕሩ ማዶ እንሻገር" አላ
ቸው እነርሱም ሄዱ። ፳፫ሲሄዱም አንቀላፋ፤
በባሕሩም ላይ ዐውሎ ነፋስ መጣ፤ ውኃ
ዉም ታንኳቸውን ሞላው፤ እነርሱም ተጨ
ነቁ። ፳፬ቀርበውም፥ "መምህር ሆይ፥ መም
ህር ሆይ፥ ልንጠፋ ነው" ብለው ቀሰቀሱት፤
ተነሥቶም ነፋሱንና የውኃዉን ማዕበል ገሠጻ
ቸው፤ እነርሱም ዝም አሉ፤ ታላቅ ፀጥታም

---

፩ በግሪኩ "ያገለግሏቸው" ነበር ይላል።

፰፥፪-፫ ማቴ. ፳፯፥፶፭-፶፮፤ ማር. ፲፭፥፵-፵፩፤ ሉቃ. ፳፫፥፵፱። ፰፥፲ ኢሳ. ፮፥፱-፲።

፰፥፲፮ ማቴ. ፭፥፲፭፤ ሉቃ. ፲፩፥፴፫። ፰፥፲፯ ማቴ. ፲፥፳፮፤ ሉቃ. ፲፪፥፪።

፰፥፲፰ ማቴ ፳፭፥፳፱፤ ሉቃ. ፲፱፥፳፮።

ሆነ። ፳፭እርሱም “እምነታችሁ ወዴት አለ?”
አላቸው፤ እነርሱም ፈርተው ተደነቁ፤ እርስ
በርሳቸውም፥ “ውኃም ነፋስም የሚታዘዙለት
ይህ ማነው?” አሉ።

### ጋኔን ያደረበትን ሰው ስለ ማዳኑ

(ማቴ. ፰፥፳፰-፴፬፤ ማር. ፭፥፩-፳)

፳፮ከዚህ በኋላ በገሊላ ወደብ አቅጣጫ ወዳ
ለችው ወደ ጌርጌሴኖን ሀገር በታንኳ ሄዱ።
፳፯ወደ ምድርም በወረዱ ጊዜ ጋኔን ያደረ
በት ሰው ከከተማ ወጥቶ ተገናኘው፤ ልብሱ
ንም ከጣለ ብዙ ዘመን ሆኖት ነበር፤ በመቃ
ብር ብቻ ይኖር ነበር እንጂ ወደ ቤት አይገ
ባም ነበር፤ ፳፰ጌታችን ኢየሱስንም ባየው ጊዜ
ጮኸ፤ ሮጦም ሰገደለት፤ “የልዑል እግዚአ
ብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ካንተ ጋር ምን
አለኝ?” እያለም በታላቅ ቃል ጮኸ፤ እንዳያ
ሠቃየውም ማለደው። ፳፱ክፉውን ጋኔን ከዚያ
ሰው ላይ እንዲወጣ ያዝዘው ነበርና፤ ዘወትርም
አእምሮዉን ያሳጣው ነበርና፤ ብላቴኖችም በእ
ግር ብረት አስረው ይጠብቁት ነበር፤ እግር
ብረቱንም ይሰብር ነበር፤ ጋኔኑም በምድረ በዳ
ያዞረው ነበር። ፴ጌታችን ኢየሱስም፥ “ስምህ
ማነው?” ብሎ ጠየቀው፤ እርሱም፥ “ስሜ
ሌጌዎን ነው” አለው፤ ብዙ አጋንንት ይዘውት
ነበርና። ፴፩ወደ ጥልቁም ይገቡ ዘንድ እንዳይ
ሰድዳቸው ማለዱት። ፴፪በዚያም ብዙ የእሪያ
መንጋ በተራራ ላይ ተሰማርቶ ነበር፤ ወደ እሪ
ያዎችም እንዲገቡባቸው ይፈቅድላቸው ዘንድ
ማለዱት፤ እርሱም ፈቀደላቸው። ፴፫እነዚያ አጋ
ንንትም ከዚያ ሰው ላይ ወጥተው ወደ እሪያ
ዎች ገቡ፤ የእሪያዎችም መንጋ አብደው ከገ
ደሉ ወደ ባሕር ጠልቀው ሞቱ።

፴፬እረኞችም የሆነውን ባዩ ጊዜ ሸሽተው
ሄዱና ገብተው በከተማዉና በመንደሩ አወሩ።
፴፭ሰዎችም የሆነውን ያዩ ዘንድ ወጡ፤ ሄደውም
ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ በደረሱ ጊዜ አጋን
ንት የወጡለትን ያን ሰው አእምሮዉ ተመልሶ
ለት ልብሱን ለብሶ፥ ከጌታችን ከኢየሱስ እግር
አጠገብ ተቀምጦ አገኙትና ፈሩ። ፴፮ያዩትም
ሰዎች ጋኔን አድሮበት የነበረው ሰው እንዴት
እንደ ዳነ ነገሩአቸው። ፴፯በጌርጌሴኖንም ዙሪያ
ያሉ ሰዎች ከእነርሱ ዘንድ እንዲሄድላቸው ማለ
ዱት፤ ጽኑ ፍርሀት ይዞአቸዋልና፤ ጌታችን ኢየ
ሱስም በታንኳ ሆኖ ተመለሰ። ፴፰ያም አጋን
ንት የወጡለት ሰው ከእርሱ ጋር ይሄድ ዘንድ
ጌታችን ኢየሱስን ማለደው፤

39 እርሱ ግን፥ “ወደ ቤትህ ተመልሰህ እግ
ዚአብሔር ያደረገልህን ታላቅ ነገር ሁሉ ተና
ገር” ብሎ አሰናበተው። እርሱም ሄዶ በከተ
ማዉ ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ያደረገለትን ሁሉ
ተናገረ። ፵ጌታችን ኢየሱስም በተመለሰ ጊዜ
ሕዝቡ በአንድነት ተቀበሉት፤ ሁሉ ይጠባበ
ቁት ነበርና።

### ስለ ምኵራቡ ሹም ልጅና ደም ይፈስስባት ስለ ነበረችው ሴት

(ማቴ. ፱፥፲፰-፳፮፤ ማር. ፭፥፳፩-፵፫)

፵፩እነሆም ኢያኢሮስ የሚባል ሰው መጣ፤
እርሱም የምኵራብ ሹም ነበር፤ ከጌታችን
ኢየሱስ እግር በታችም ሰገደ። ወደ ቤቱም
ይገባ ዘንድ ለመነው። ፵፪ዕድሜዋ ዐሥራ ሁለት
ዓመት የሚሆናት አንዲት ልጅ ነበረችው፤ እር
ስዋም ልትሞት ቀርባ ነበረች።

፵፫ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ከእርሱ
ጋር ሲሄድ ሰዎች ያጨናንቁት ነበር፤ ከዐሥራ
ሁለት ዓመትም ጀምሮ ደም ይፈስሳት የነበረች
ሴት መጣች፤ ገንዘብዋንም ሁሉ ለባለመድኀኒ
ቶች ሰጥታ ጨርሳ ነበር፤ ነገር ግን ሊያድናት
የቻለ ማንም አልነበረም። ፵፬ቀርባም በጌታችን
በኢየሱስ በስተኋላው ቆመችና የልብሱን ጫፍ
ዳሰሰች፤ ያንጊዜም የደምዋ መፍሰስ ቆመ።
፵፭ጌታችን ኢየሱስም፥ “ማን ዳሰሰኝ?” አለ፤
ሁሉም ካዱ፤ ጴጥሮስና ከእርሱ ጋር የነበሩ
ትም፥ “መምህር ሆይ፥ ሰው ይጋፋሁና ያጨ
ናንቅህ የለምን? አንተ ግን ማን ዳሰሰኝ? ትላ
ለህ” አሉት። ፵፮ጌታችን ኢየሱስም፥ “የዳሰ
ሰኝ አለ፤ ከእኔ ኀይል እንደ ወጣ ዐውቃለ
ሁና” አላቸው። ፵፯ሴቲቱም እንዳልተሰወረላት
ባየች ጊዜ እየተንቀጠቀጠች ሄዳ ሰገደችለት፤
በሕዝቡም ሁሉ ፊት በምን ምክንያት ወደ
እርሱ እንደ ቀረበችና የልብሱን ጫፍ እንደ ዳሰ
ሰች ወዲያውም እንደ ዳነች ተናገረች። ፵፰እር
ሱም፥ “ልጄ ሆይ፥ እምነትሽ አዳነችሽ፤ በሰ
ላም ሂጂ” አላት። ፵፱ይህንም ሲናገር አንድ
ሰው ከምኵራቡ ሹም ቤት መጥቶ፥ “ልጅህስ
ሞታለች እንግዲህ መምህሩን አታድክመው”
አለው። ፶ጌታችን ኢየሱስም በሰማ ጊዜ የምኵ
ራቡን ሹም፥ “አትፍራ፥ ብቻ እመን፤ ልጅ
ህስ ትድናለች” አለው። ፶፩ወደ ቤትም በገባ
ጊዜ ከጴጥሮስ፥ ከያዕቆብና ከዮሐንስ፥ ከብላ
ቴናይቱም አባትና እናት በቀር ማንም ከእ
ርሱ ጋር ሌላ ሰው ይገባ ዘንድ አልፈቀደም።
፶፪ሁሉም እያለቀሱ ዋይ ዋይ ይሉላት ነበር፤

ጌታችን ኢየሱስ ግን፥ "አታልቅሱ፤ ብላቴ
ናይቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም" አላ
ቸው። ፶፫እንደ ሞተችም ዐውቀዋልና ሳቁበት።
፶፬እርሱ ግን ሁሉን ወደ ውጭ አስወጣና እጅ
ዋን ይዞ ጠራት፤ እንዲህም አላት፥ " አንቺ
ብላቴና ተነሺ።" ፶፭ወዲያውም ነፍስዋ ተመል
ሶላት ፈጥና ቆመች፥ የምትበላውንም ይሰጡ
አት ዘንድ አዘዘ። ፶፮አባቷና እናቷም አደነቁ፤
እርሱ ግን የሆነውን ለማንም እንዳይነግሩ ከለ
ከላቸው።

## ምዕራፍ ፱

### ስለ ሐዋርያት መላክ

(ማቴ. ፲፥፯-፲፭፤ ማር. ፮፥፯-፲፫)

፩ዐሥራ ሁለቱንም ሐዋርያት ጠራና፡- በአጋ
ንንት ሁሉ ላይ፥ ድውያንንም ይፈውሱ ዘንድ
ኀይልንና ሥልጣንን ሰጣቸው። ፪የእግዚአብ
ሔርን መንግሥት እንዲሰብኩ፥ ድውያንንና
ሕሙማንንም ሁሉ እንዲፈውሱ ላካቸው። ፫እን
ዲህም አላቸው፥ "በትርም ቢሆን፥ ከረጢትም
ቢሆን፥ እንጀራም ቢሆን፥ ወርቅም ቢሆን፥
ሁለት ልብስም ቢሆን ለመንገድ ምንም አት
ያዙ። ፬በምትገቡበት ቤት በዚያ ተቀመጡ፤
እስክትሄዱም ድረስ ከዚያ አትውጡ።[፩] ፭የማ
ይቀበሉአችሁ ቢሆን ግን ከዚያች ከተማ ወጥታ
ችሁ ምስክር ሊሆንባቸው የእግራችሁን ትቢያ
አራግፉ።" ፮ወጥተውም በየአውራጃዉ መንደ
ሮች ዞሩ፤ በስፍራውም ሁሉ ወንጌልን ሰበኩ፤
ድውያንንም ፈወሱ።

### ስለ ሄሮድስ ዐሳብ

(ማቴ. ፲፬፥፩-፲፪፤ ማር. ፮፥፲፬-፳፱)

፯የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስም የተደረገ
ውን ሁሉ ሰምቶ የሚናገረውን ያጣ ነበር፤ መጥ
ምቁ ዮሐንስ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ የሚሉ
ነበሩና። ፰ኤልያስ ተገለጠ የሚሉም ነበሩ፤ ከቀ
ደሙት ነቢያት አንዱ ተነሥቶአል የሚሉም ነበ
ሩና። ፱ሄሮድስም፥ "እኔ የዮሐንስን ራስ አስቈ
ረጥሁ፤ እንግዲህ ስለ እርሱ ሲወራ የምሰማው
ይህ ማነው?" አለ፤ ሊያየውም ይሻ ነበር።
፲ሐዋርያትም በተመለሱ ጊዜ ያደረጉትን
ሁሉ ነገሩት፤ እርሱም ለብቻቸው ይዞአቸው
ቤተ ሳይዳ ከምትባል ከተማ አጠገብ ወደ አለ
ምድረ በዳ ወጡ። ፲፩ሕዝቡም ዐውቀው ተከ
ተሉት፤ እርሱም ተቀበላቸው፤ ስለ እግዚአብ
ሔር መንግሥትም አስተማራቸው፤ ሊፈወሱ
የሚሹትንም አዳናቸው።

### ኅብስትን ስለ ማበርከቱ

(ማቴ. ፲፬፥፲፫-፳፩፤ ዮሐ. ፮፥፩-፲፬)

፲፪ቀኑም በመሸ ጊዜ ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙ
ርት መጥተው፥ "ያለንበት ምድረ በዳ ነውና በዙ
ሪያችን ወዳሉ መንደሮችና ገጠሮች ሄደው እንዲ
ያድሩ የሚበሉትንም እንዲያገኙ ሕዝቡን አሰና
ብት" አሉት። ፲፫እርሱ ግን፥ "እናንተ የሚበሉትን
ስጡአቸው" አላቸው፤ እነርሱም፥ "ለዚህ ሁሉ
ሕዝብ የሚበቃ ምግብ ልንገዛ ካልሄድን ከአምስት
እንጀራና ከሁለት ዓሣ በቀር ሌላ በዚህ የለንም"
አሉት። ፲፬ሰዎቹም አምስት ሺህ ያህሉ ነበር፤ ደቀ
መዛሙርቱንም፥ "አምሳ አምሳውን በየክፍላቸው
አስቀምጡአቸው" አላቸው። ፲፭እንዲሁም አደ
ረጉ፤ ሁሉም ተቀመጡ። ፲፮አምስቱን እንጀራና
ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ ተመለከተ፤ ባረከ፤
ቈርሶም ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ ለደቀ መዛሙርቱ
ሰጣቸው። ፲፯ሁሉም በልተው ጠገቡ፤ ያነሡትም
የተረፈው ቍርስራሽ ዐሥራ ሁለት መሶብ ሞላ።

### ሰው ማን ይለኛል? ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ስለ መጠየቁ

(ማቴ. ፲፮፥፲፫-፲፱፤ ማር. ፰፥፳፯-፳፱)

፲፰ከዚህም በኋላ ብቻውን ሲጸልይ ደቀ መዛ
ሙርቱም ከእርሱ ጋር ሳሉ፥ "ሰዎች ማን ይሉ
ኛል?" ብሎ ጠየቃቸው። ፲፱እነርሱም መልሰው፥
"መጥምቁ ዮሐንስ ነው የሚሉህ አሉ፤ ኤልያስ
ነው የሚሉህም አሉ፤ ከቀደሙት ነቢያት አንዱ
ተነሥቶአል የሚሉህም አሉ" አሉት። ፳እርሱም፥
"እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ?" አላቸው፤ ጴጥሮ
ስም መልሶ፥ "አንተ የእግዚአብሔር መሲሕ ነህ"
አለው። ፳፩ይህንም ለማንም እንዳይናገሩ ገሥጻቸ
ውና ከለከላቸው።

### ስለ ሕማሙና ስለሚከተሉት የተናገረው

(ማቴ. ፲፥፴፰፡፴፱፤ ማር. ፰፥፴፬-፴፰)

፳፪"ለሰው ልጅ ብዙ መከራ ያጸኑበት ዘንድ
ሽማግሌዎችና የካህናት አለቆች፥ ጻፎችም

---

፩ አንዳንድ ዘርዕ "ከዚያም ዉጡ" ይላል።

፱፥፫-፭ ሉቃ. ፲፥፬-፲፩፤ ሐ.ሥ. ፲፫፥፶፩።   ፱፥፯-፰ ማቴ. ፲፮፥፲፬፤ ማር. ፰፥፳፰፤ ሉቃ. ፱፥፲፱።

፱፥፲፱ ማቴ. ፲፬፥ ፩-፪፤ ማር. ፮፥፲፬-፲፭፤ ሉቃ. ፱፥፯-፰።   ፱፥፳ ዮሐ. ፮፥፷፰-፷፱።

ይፈትኑት ዘንድ፥ ይገድሉትም ዘንድ፥ በሦስ
ተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ አለው” አላቸው።
፳፫ሁሉንም እንዲህ አላቸው፥ “ሊከተለኝ የሚ
ወድ ሰው ራሱን ይካድ፤ ጨክኖም የሞቱን
መስቀል ይሸከም፤ ዕለት ዕለትም ይከተለኝ።
፳፬ሰውነቱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ይጥላታል፤
ስለ እኔ ሰውነቱን የጣለ ግን ያድናታል። ፳፭ሰው
ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ ነፍሱንም ካጣ ምን ይረ
ባዋል? ፳፮በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ የሰው
ልጅ በክብሩ፥ በአባቱም ክብር፥ ቅዱሳን መላ
እክትን አስከትሎ ሲመጣ ያፍርበታል። ፳፯እው
ነት እላችኋለሁ፤ በዚህ ከቆሙት የእግዚአብሔ
ርን መንግሥት እስኪያዩአት ድረስ ሞትን የማ
ይቀምሱ አሉ።”

## በደብረ ታቦር ክብሩን ስለ መግለጡ

(ማቴ. ፲፯፥፩-፰፤ ማር. ፱፥፪-፰)

፳፰ከዚህም ነገር በኋላ በስምንተኛው ቀን ጌታ
ችን ኢየሱስ ጴጥሮስን፥ ያዕቆብንና ዮሐንስን
ይዞአቸው ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ። ፳፱ሲጸ
ልይም የፊቱ መልክ ተለወጠ፤ ልብሱም ነጭ
ሆነ፤ እንደ መብረቅም አብለጨለጨ። ፴እነ
ሆም፥ ሁለት ሰዎች መጥተው ከእርሱ ጋር ይነ
ጋገሩ ነበር። እነርሱም ሙሴና ኤልያስ ነበሩ።
፴፩በክብርም ተገልጠው በኢየሩሳሌም ይደረግ
ዘንድ ያለውን ክብሩንና፬ መውጣቱን ተናገሩ፤
፴፪ጴጥሮስንና ከእርሱ ጋር የነበሩትንም ዐይኖቻ
ቸው በእንቅልፍ ፈዝዘው አገኘ፤ በነቁም ጊዜ
ክብሩንና ከእርሱ ጋር ቆመው የነበሩትን ሁለት
ሰዎች አዩ። ፴፫ከዚህም በኋላ ከእርሱ ሲለዩ
ጴጥሮስ ጌታችን ኢየሱስን፥ “መምህር፥ ሆይ፥
እዚህ ብንኖር ለእኛ መልካም ነው፤ ሦስት ሰቀ
ላዎችንም እንሥራ፤ አንዱን ለአንተ፥ አንዱ
ንም ለሙሴ፥ አንዱንም ለኤልያስ” አለው፤
የሚናገረውንም አያውቅም ነበር። ፴፬ይህንም
ሲናገር ደመና መጣና ጋረዳቸው፤ ወደ ደመና
ውም በገቡ ጊዜ ፈሩ። ፴፭ከደመናውም ውስጥ፥
“የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት”
የሚል ቃል መጣ። ፴፮ቃሉም ከመጣ በኋላ
ጌታችን ኢየሱስ ብቻውን ተገኘ፤ እነርሱ ግን
ዝም አሉ፤ ያዩትንና የሰሙትንም በዚያ ጊዜ
ለማንም አልተናገሩም።

## ጋኔን ይጥለው የነበረውን ስለ ማዳኑ

(ማቴ. ፲፯፥፲፬-፲፰፤ ማር. ፱፥፲፬-፳፯)

፴፯በሁለተኛውም ቀን ከተራራው ወረዱ፤
ብዙ ሕዝብም ተቀበሉት። ፴፰አንድ ሰውም በሕ
ዝቡ መካከል ጮኾ እንዲህ አለው፥ “መምህር
ሆይ፥ እርሱ ለእኔ አንድ ነውና ልጄን ታይልኝ
ዘንድ እለምንሃለሁ። ፴፱እነሆ፥ ጋኔን ሊነጥቀኝ
ነው፤፭ ድንገትም ያስጮኸዋል፤ ጥሎም ያፈራ
ግጠዋል፤ አረፋም ያስደፍቀዋል፤ ቀጥቅጦ በጭ
ንቅ ይተወዋል። ፵እንዲያወጡትም ደቀ መዛሙ
ርትህን ለመንሁአቸው፤ ነገር ግን ማውጣት
ተሳናቸው።” ፵፩ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥
“የማታምን ክፉ ትውልድ፥ እስከ መቼ
ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣ
ችኋለሁ? ልጅህን ወደዚህ አምጣው” አለው።
፵፪ሲያመጣውም ጋኔኑ ጣለውና አፈራገጠው፤
ጌታችን ኢየሱስም ያን ክፉ ጋኔን ገሠጸው፤
ልጁንም አዳነው፤ ለአባቱም ሰጠው። ሁሉም
ከእግዚአብሔር ታላቅነት የተነሣ አደነቁ።

## ስለ ሕማሙ

(ማቴ. ፲፯፥፳፪፡፳፫፤ ማር. ፱፥፴-፴፪)

፵፫እነርሱም ጌታችን ኢየሱስ ባደረገው ተአ
ምራት ሁሉ ሲደነቁ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ
አላቸው። ፵፬“እናንተስ ይህን ነገር በልባችሁ፮
አኑሩት፤ የሰው ልጅ በሰዎች እጅ ተላልፎ
ይሰጥ ዘንድ አለውና።” ፵፭እነርሱ ግን ይህን
ነገር አላስተዋሉትም፤ እንዳይመረምሩት ከእነ
ርሱ የተሰወረ ነውና፤ ስለዚህ ነገርም እንዳይጠ
ይቁት ይፈሩት ነበርና።

## ስለ ትሕትና

(ማቴ. ፲፰፥፩-፭፤ ማር. ፱፥፴፫-፴፯)

፵፮እርስ በርሳቸውም ከእነርሱ ማን እንደሚ
በልጥ ዐሰቡ። ፵፯ጌታችን ኢየሱስም በልቡና
ቸው የሚያስቡትን ዐወቀባቸውና አንድ ሕፃን
ወስዶ በመካከላቸው አቆመው። ፵፰እንዲህም

---

፬ በግሪኩ “ክብሩን ...” አይልም።

፭ “ሊነጥቀኝ ነው” የሚለው በግሪኩ አይገኝም።

፮ በግሪኩ “በጆሮአችሁ አኑሩት” ይላል።

፱፥፳፫ ማቴ. ፲፥፴፰፤ ሉቃ. ፲፬፥፳፯። ፱፥፳፬ ማቴ. ፲፥፴፱፤ ሉቃ. ፲፯፥፴፫፤ ዮሐ. ፲፪፥፳፭።
፱፥፴፭ ኢሳ. ፵፪፥፩፤ ማቴ. ፫፥፲፯፤ ፲፪፥፲፰፤ ማር. ፩፥፲፩፤ ሉቃ. ፫፥፳፪። ፱፥፵፮ ሉቃ. ፳፪፥፳፬።
፱፥፵፰ ማቴ. ፲፥፵፤ ሉቃ. ፲፥፲፮፤ ዮሐ. ፲፫፥፳።

አላቸው፥ “በስሜ እንደዚህ ያለውን ሕፃን የሚ
ቀበል እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላ
ከኝን ይቀበላል፤ ራሱን ከሁሉ፭ ዝቅ የሚያደ
ርግ እርሱ ታላቅ ይሆናል።”
፵፱ዮሐንስም መልሶ፥ “መምህር ሆይ፥ በስ
ምህ ጋኔን ሲያወጣ ያየነው አንድ ሰው አለ፤
ከእኛም ጋር አልተከተለህምና ከለከልነው፤”
አለው። ፶ጌታችን ኢየሱስም፥ “አትከልክሉት፤
ባለጋራችሁ ካልሆነ ባልንጀራችሁ፮ ነውና” አላ
ቸው። ፶፩የመውጣቱ ወራትም በቀረበ ጊዜ ወደ
ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና። ፶፪በፊቱም
መልእክተኞችን ላከ፤ ሄደውም ያዘጋጁለት
ዘንድ ወደ ሰማርያ ከተማ ገቡ። ፶፫ነገር ግን
አልተቀበሉትም፤ ፊቱን ወደ ኢየሩሳሌም አቅ
ንቶ ነበርና። ፶፬ደቀ መዛሙርቱ ያዕቆብና ዮሐን
ስም ይህን ባዩ ጊዜ፥ “አቤቱ፥ ኤልያስ እንደ
አደረገ እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እን
ድንል ትፈቅዳለህን?” አሉት። ፶፭እርሱ ግን
ዘወር ብሎ፥ “ከምን መንፈስ እንደ ሆናችሁ
አታውቁም” ብሎ ገሠጻቸው። ፶፮የሰው ልጅ
የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመ
ጣም። ወደ ሌላም መንደር ሄዱ።

### ሊከተሉት ስለ ጠየቁት ሰዎች
(ማቴ. ፰፥፲፱-፳፪)

፶፯ከዚህ በኋላ በመንገድ ሲሄዱ አንድ ሰው፥
“መምህር፥ ወደምትሄድበት ልከተልህን?”
አለው። ፶፰ጌታችን ኢየሱስም “ለቀበሮዎች
ጕድጓድ አላቸው፤ ለሰማይ ወፎችም ጎጆ አላ
ቸው፤ የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት
የለውም” አለው። ፶፱ሌላውንም፥ “ተከተለኝ”
አለው፤ እርሱ ግን፥ “አቤቱ፥ በፊት ሄጄ አባ
ቴን እንድቀብረው ፍቀድልኝ” አለው። ፷ጌታ
ችን ኢየሱስም፥ “ሙታኖቻቸውን ይቀብሩ
ዘንድ ሙታንን ተዉአቸው፤ አንተ ግን ሂድና
የእግዚአብሔርን መንግሥት ስበክ” አለው።
፷፩ሦስተኛውም፥ “አቤቱ፥ ልከተልህን? ነገር
ግን ሄጄ ቤተ ሰቦችን ሁሉ እንድሰናበት ፍቀድ
ልኝ” አለው። ፷፪ጌታችን ኢየሱስም፥ “ማንም
ዕርፍ ይዞ እያረሰ ወደ ኋላው የሚመለከት፯
ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይሆንም”
አለው።

## ምዕራፍ ፲

### ሌሎች ሰባ ሰዎችን ስለ መምረጡ

፩ከዚህም በኋላ ጌታችን ሌሎች ሰባ ሰዎ
ችን መረጠ፤፰ ሁለት ሁለት አድርጎም ሊሄድ
በት ወደ አለው ከተማና መንደር በፊቱ ላካ
ቸው። ፪ጌታችን ኢየሱስም አላቸው፥ “መከሩ
ብዙ ነው፤ ሠራተኛው ግን ጥቂት ነው፤ እን
ግዲህ ለመከሩ ሠራተኛ ጨምሮ ይልክ ዘንድ
ባለ መከሩን ለምኑት። ፫ሂዱ፤ እነሆ፥ እኔ እንደ
በጎች በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ። ፬ከረ
ጢትም፥ ስልቻም፥ ጫማም፥ ምንም ምን አት
ያዙ፤ በመንገድም ማንንም ሰላም አትበሉ።
፭ወደ ገባችሁበት ቤትም አስቀድማችሁ ‘ለዚህ
ቤት ሰዎች ሰላም ይሁን’ በሉ። ፮በዚያም የሰ
ላም ልጅ ቢኖር ሰላማችሁ ያድርበታል፤ ያለ
ዚያ ግን ሰላማችሁ ይመለስላችኋል። ፯በዚያም
ቤት ተቀመጡ፤ ከእነርሱ የተገኘውንም ብሉ፥
ጠጡም፤ ለሠራተኛ ዋጋው ይገባዋልና፤ ከቤ
ትም ወደ ቤት አትሂዱ። ፰ወደ ማናቸውም
ከተማ ብትገቡ፥ የዚያ ከተማ ሰዎችም ቢቀበ
ሉአችሁ ያቀረቡላችሁን ብሉ። ፱በውስጥዋ የሚ
ገኙትን ድውያንንም ፈውሱ፤ ‘የእግዚአብሔ
ርም መንግሥት ወደ እናንተ ቀርባለች’ በሉአ
ቸው። ፲ነገር ግን ወደ ማናቸውም ከተማ ብት
ገቡ፥ የዚያች ከተማ ሰዎችም ባይቀበሉአችሁ
ወደ አደባባይዋ ወጥታችሁ የእግራችሁን ትቢያ
አራግፉ።፱ እንዲህም በሉ፡- ፲፩ከከተማችሁ የተ
ጣበቀብንን ትቢያ እንኳን እናራግፍላችኋለን፤
ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እና
ንተ እንደ ቀረበች ይህን ዕወቁ። ፲፪በፍርድ ቀን
ሰዶም ከዚያች ከተማ ይልቅ እንደምትሻል ይቅ
ርታንም እንደምታገኝ እነግራችኋለሁ።

---

፭ በግሪኩ “ከሁላችሁ የሚያንስ እርሱ ታላቅ ይሆናል” ይላል።
፮ በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ “ከእናንተ ጋር ነውና” ይላል።
፯ አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ “ዕርፍ ይዞ ወደኋላ የሚያርስ የለም የእግዚአብሔር መንግሥት የቀናች ናትና” ይላል።
፰ በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ “አርአየ” ይላል።
፱ “የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፱፥፶፬ ፪ነገ. ፩፥፱-፲፪።  ፱፥፷፩ ፩ነገ. ፲፱፥፳።  ፲፥፪ ማቴ. ፱፥፴፯-፴፰።  ፲፥፫ ማቴ. ፲፥፲፮።
፲፥፬-፲፩ ማቴ. ፲፥፯-፲፬፤ ማር. ፮፥፰-፲፩፤ ሉቃ. ፱፥፫-፭።  ፲፥፯ ፩ቆሮ. ፱፥፲፬፤ ፩ጢሞ. ፭፥፲፰።
፲፥፲-፲፩ ሐ.ሥ. ፲፫፥፶፩።  ፲፥፲፪ ዘፍ. ፲፱፥፳፬-፳፰፤ ማቴ. ፲፩፥፳፬፤ ፲፥፲፭።

፲፫"ኮራዚ ወዮልሽ! ቤተ ሳይዳ ወዮልሽ! በእ
ናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና
ተደርጎ ቢሆን ቀድሞ ማቅ ለብሰው አመድም
ነስንሰው በተቀመጡ ንስሓም በገቡ ነበር።
፲፬ነገር ግን ጢሮስና ሲዶና ከእናንተ ይልቅ በፍ
ርድ ቀን ይቅርታን ያገኛሉ። ፲፭አንቺም ቅፍርና
ሆም እስከ ሰማይ ድረስ ከፍ ከፍ ብትዪ እስከ
ሲኦል ትወርጃለሽ።
፲፮"እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል፤ እናን
ተንም እንቢ የሚል እኔን እንቢ ይላል፤ እኔ
ንም እንቢ የሚል የላከኝን እንቢ ይላል፤ እኔ
ንም የሚሰማ የላከኝን ይሰማል።"፫

## ስለ ሰባው መልእክተኞች መመለስ

፲፯እነዚያም ሰባው ደስ ብሎአቸው ተመለ
ሱና፥ "አቤቱ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገ
ዙልን" አሉት። ፲፰እርሱም እንዲህ አላቸው፥
"ሰይጣንን ከሰማይ እንደ መብረቅ ሲወድቅ
አየሁት። ፲፱እነሆ፥ ጊንጦችንና እባቦችን፥ የጠ
ላትንም ኀይል ሁሉ ትረግጡ ዘንድ ሥልጣንን
ሰጠኋችሁ፤ የሚጐዳችሁም ነገር የለም። ፳ነገር
ግን አጋንንት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይ
በላችሁ፤ ግን ስማችሁ በሰማያት ስለ ተጻፈ
ደስ ይበላችሁ።"
፳፩በዚያች ሰዓትም ጌታችን ኢየሱስ በመን
ፈስ ቅዱስ ደስ አለው፤ እንዲህም አለ፥ "የሰ
ማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፥ ይህን ከዐዋ
ቂዎችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለገ
ለጥኸው አመሰግንሃለሁ፤ አዎን፥ አባት ሆይ፥
ፈቃድህ በፊትህ እንዲሁ ሆኖአልና። ፳፪ሁሉ
ከአባቴ ዘንድ ተሰጠኝ፤ ወልድ ማን እንደ ሆነ
ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም፤ አብም ማን
እንደ ሆነ ከወልድ በቀር የሚያውቅ የለም።
ወልድ ግን ለወደደው ይገልጥለታል።"
፳፫ተመልሶም ደቀ መዛሙርቱን ለብቻቸው
አድርጎ እንዲህ አላቸው፥ "እናንተ የምታዩ
ትን የሚያዩ ዐይኖች ብፁዓን ናቸው። ፳፬ብዙ
ነቢያትና ነገሥታት እናንተ የምታዩትን ሊያዩ
ተመኙ፤ አላዩምም፤ እናንተ የምትሰሙትንም
ሊሰሙ ተመኙ፥ አልሰሙም።"

## ጌታን ስለ ፈተነው ሕግ ዐዋቂ

፳፭ከዚህ በኋላ አንድ ሕግ ዐዋቂ ሊፈትነው
ተነሣና፥ "መምህር ሆይ፥ የዘለዓለም ሕይወ
ትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ?" አለው።
፳፮እርሱም፥ "በኦሪት ምን ተጽፎአል? እንዴ
ትስ ታነብባለህ?" አለው። ፳፯እርሱም መልሶ፥
"እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፥
በፍጹም ሰውነትህ፥ በፍጹም ኀይልህ፥ በፍ
ጹም ዐሳብህ ውደደው፤ ባልንጀራህንም እንደ
ራስህ ውደድ ይላል" አለው። ፳፰ጌታችን ኢየ
ሱስም፥ "መልካም መለስህ፤ እንዲሁ አድ
ርግ፤ ትድናለህም" አለው።
፳፱ራሱን ሊያከብር ባልንጀራውንም ሊንቅ፬
ወድዶ፥ "ባልንጀራዬ ማነው?" አለው።

## ስለ ደጉ ሳምራዊ

፴ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፥
"አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ይወርድ
ነበር፤ ሽፍቶችም አገኙት፤ ደበደቡት፥ አቈሰ
ሉት፥ ልብሱንም ገፈፈው፤ በሕይወትና በሞት
መካከል ጥለውት ሄዱ። ፴፩አንድ ካህንም በዚ
ያች መንገድ ሲወርድ ድንገት አገኘው፤ አይ
ቶም አልፎት ሄደ። ፴፪እንዲሁም አንድ ሌዋዊ
በዚያ ቦታ አገኘውና፥ አይቶ እንደ ፊተኛው አል
ፎት ሄደ። ፴፫አንድ ሳምራዊ ግን በዚያች መን
ገድ ሲሄድ አገኘው፤ አይቶም አዘነለት። ፴፬ወደ
እርሱም ቀረበ፤ ቍስሉንም አጋጥሞ አሰረለት፤
በቍስሉ ላይም ወይንና ዘይት ጨመረለት፤ በአ
ህያውም ላይ አስቀምጦ እንዲፈውሰው የእንግዶ
ችን ቤት ወደሚጠብቀው ወሰደው፤ የሚድንበ
ትንም ዐሰበ። ፴፭በማግሥቱም ሁለት ዲናር አው
ጥቶ ለእንግዳ ቤት ጠባቂው ሰጠውና፡- 'በዚህ
አስታምልኝ፤ ከዚህ የሚበልጥ ለእርሱ የምታወ
ጣው ቢኖር እኔ በተመለስሁ ጊዜ እከፍልሃለሁ'
አለው። ፴፮እንግዲህ ሽፍቶች ለደበደቡት ሰው
ከእነዚህ ከሦስቱ ባልንጀራ የሚሆነው ማንኛው
ይመስልሃል?" ፴፯እርሱም"ምሕረት ያደረገለት
ነዋ" አለው፤ ጌታችን ኢየሱስም፥ "እንኪያስ
አንተም ሂድና እንዲሁ አድርግ" አለው።

---

፫ "እኔን የሚሰማኝ የላከኝን ይሰማል" የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ አይገኝም።
፬ ግሪኩ እና አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ "ባልንጀራውን ሊንቅ" የሚለውን አይጽፉም።
፲፥፲፫ ኢሳ. ፳፫፥፩-፳፤ ሕዝ. ፳፮፥፩-፳፰፤ ፳፯፤ ኢዩ. ፫፥፬-፰፤ አሞጽ ፩፥፱-፲፤ ዘካ. ፱፥፪-፬።
፲፥፲፭ ኢሳ. ፲፬፥፲፫-፲፭። ፲፥፲፮ ማቴ. ፲፥፵፤ ማር. ፱፥፴፯፤ ሉቃ. ፱፥፵፰፤ ዮሐ. ፲፫፥፳። ፲፥፲፱ መዝ. ፺፥፲፫።
፲፥፳፪ ዮሐ. ፫፥፴፭፤ ፲፥፲፭። ፲፥፳፭-፳፰ ማቴ. ፳፪፥፴፭-፵፤ ማር. ፲፪፥፳፰-፴፬።
፲፥፳፯ ዘሌ. ፲፱፥፲፰፤ ዘዳ. ፮፥፭። ፲፥፳፰ ዘሌ. ፲፰፥፭። ፲፥፴፫-፴፬ ፪ዜ.መ. ፳፰፥፲፭።

### ስለ ማርያምና ስለ ማርታ

፴፰ከዚህም በኋላ ሄደው ወደ አንዲት መንደር
ገቡ፤ ማርታ የምትባል አንዲት ሴትም በቤቷ
ተቀበለችው። ፴፱ማርያም የምትባል እኅትም
ነበረቻት፤ እርስዋም ከጌታችን ኢየሱስ እግር
አጠገብ ተቀምጣ ትምህርቱን ትሰማ ነበር።
፵ማርታ ግን ብዙ በማዘጋጀት ትደክም ነበር፤
ቆማም፥ "ጌታዬ ሆይ፥ እኅቴ ትታኝ ብቻዬን
ስሠራ አያሳዝንህምን? ርዳት በላት" አለችው።
፵፩ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላት፥
"ማርታ፥ ማርታ፥ በብዙ ነገር ትደክሚያለሽ፥
ትቸገሪያለሽም፤ ታዘጋጂያለሽም። ፵፪ጥቂት ይበ
ቃል፤ ያም ባይሆን አንድ ይበቃል፤ ማርያምስ
የማይቀሙአትን መልካም ዕድል መረጠች።"

## ምዕራፍ ፲፩

### ስለ ጸሎት

(ማቴ. ፮፥፱-፲፫፤ ፯፥፯-፲፩)

፩ከዚህም በኋላ በአንዲት ቦታ ጸለየ፤ ጸሎ
ቱን በጨረሰ ጊዜም ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፥
"ጌታ ሆይ፥ ዮሐንስ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ
አስተማራቸው ጸሎት አስተምረን" አለው።
፪እርሱም እንዲህ አላቸው፥ "በምትጸልዩበት
ጊዜ እንዲህ በሉ፡- በሰማያት የምትኖር አባ
ታችን ሆይ፥ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ
ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነ እንዲሁም
በምድር ይሁን። ፫የዕለት ምግባችንን በየዕለቱ
ስጠን። ፬እኛም የበደለንን ሁሉ ይቅር እንድንል
በደላችንን ይቅር በለን፤ አቤቱ፥ ወደ ፈተና
አታግባን፤ ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ።"
፭እንዲህም አላቸው፥ "ከመካከላችሁ ወዳጅ
ያለው ሰው ቢኖር በመንፈቀ ሌሊትም ወደ
እርሱ ሄዶ እንዲህ ቢለው፡- 'ወዳጄ ሆይ ሦስት
እንጀራ አበድረኝ። ፮ወዳጄ ከመንገድ መጥቶ
ብኖልና የማቀርብለት የለኝም።' ፯ያ ወዳጁም
ከውስጥ ሆኖ፡- 'አትዘብዝበኝ፤ ደጁን አጥብ
ቀን ዘግተናል፤ ልጆችም ከእኔ ጋር በአልጋ
ላይ ተኝተዋል፤ እሰጥህ ዘንድ መነሣት አል
ችልም' ይለዋልን? ፰ወዳጁ ስለሆነ ሊሰጠው
ባይነሣ እንኳ እንዳይዘበዝበው ተነሥቶ የወደደ
ውን ያህል ይሰጠዋል። ፱እኔም እላችኋለሁ፡-
ለምኑ፥ ይሰጣችኋልም፤ ፈልጉ፥ ታገኛላች
ሁም፤ ደጅ ምቱ፥ ይከፈትላችኋልም። ፲የሚ
ለምን ሁሉ ይሰጠዋልና፤ የሚፈልግም ያገኛ
ልና፤ ደጅ ለሚመታም ይከፈትለታልና። ፲፩ከእ
ናንተ መካከል ልጁ ዳቦ የሚለምነው አባት
ቢኖር ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሣ ቢለምነውስ
በዓሣ ፋንታ እባብን ይሰጠዋልን? ፲፪ወይስ ዕን
ቍላል ቢለምነው በዕንቍላል ፋንታ ጊንጥ ይሰ
ጠዋልን? ፲፫እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻ
ችሁ መልካም ስጦታን መስጠትን የምታውቁ
ከሆነ፥ የሰማይ አባታችሁማ ለሚለምኑት መል
ካሙን ሀብተ መንፈስ ቅዱስ[፩] እንዴት አብዝቶ
ይሰጣቸው ይሆን?"

### ደንቆሮ ጋኔን ስለ ያዘው ሰው

(ማቴ. ፲፪፥፳፪-፴፤ ማር. ፫፥፳-፳፯)

፲፬ዲዳና ደንቆሮ[፪] ጋኔንንም ያወጣ ነበር፤ ጋኔ
ኑም በወጣ ጊዜ ዲዳና ደንቆሮ የነበረው ተና
ገረ፤ ሰዎችም አደነቁ። ፲፭ነገር ግን ከመካከ
ላቸው፥ "በአጋንንት አለቃ በብዔል ዜቡል
አጋንንትን ያወጣቸዋል" ያሉ ነበሩ፤ እርሱም
መልሶ፥ "ሰይጣን ሰይጣንን ማውጣት እንደ
ምን ይቻለዋል?" አላቸው።[፫] ፲፮ሌሎችም ሊፈ
ትኑት ከእርሱ ዘንድ ከሰማይ ምልክትን ይፈ
ልጉ ነበር። ፲፯እርሱ ግን የሚያስቡትን ዐወቀባ
ቸውና እንዲህ አላቸው፥ "እርስ በርስዋ የም
ትለያይ መንግሥት ሁሉ ትጠፋለች፤ ቤትም
እርስ በርሱ ቢለያይ ያ ቤት ይወድቃል። ፲፰ሰይ
ጣንስ እርስ በርሱ ከተለያየ መንግሥቱ እንዴት
ይጸናል? በአጋንንት አለቃ በብዔል ዜቡል አጋ
ንንትን ያወጣል ትላላችሁና። ፲፱እኔ በብዔል
ዜቡል አጋንንትን የማወጣ ከሆነ፥ ልጆቻችሁ
በምን ያወጡአቸዋል? ስለዚህ እነርሱ ይፋረ
ዱአችኋል።[፬] ፳እኔ በእግዚአብሔር ጣት አጋ
ንንትን የማወጣ ከሆነ እንግዲህ አሁን የእግዚ
አብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።
፳፩ኀይለኛ ሰው በጦር መሣሪያ ቤቱን የጠበቀ
እንደ ሆነ ገንዘቡ ሁሉ ደኅና ይሆናል። ፳፪ከእ
ርሱ የሚበረታው ቢመጣና ቢያሸንፈው ግን፥

---

፩ በግሪክ "መንፈስ ቅዱስን" ይላል።

፪ "ደንቆሮ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፫ "እርሱም መልሶ ሰይጣን ሰይጣንን ማውጣት እንደምን ይቻለዋል" የሚለው በግሪኩ የለም።

፬ በግሪኩ "ይፈርዱባችኋል" ይላል።

፲፥፴፰-፴፱ ዮሐ. ፲፩፥፩። ፲፩፥፲፭ ማቴ ፱፥፴፬፤ ፲፥፳፭። ፲፩፥፲፮ ማቴ. ፲፪፥፴፰፤ ፲፮፥፩፤ ማር. ፰፥፲፩።

ይታመንበት የነበረውን የጦር መሣሪያውን ይገ
ፈዋል፤ የማረከውንና የዘረፈውን[፳] ገንዘቡንም
ይወስዳል። ፳፫ ከእኔ ጋር ያልሆነ ባለጋራዬ ነው፤
ከእኔ ጋር የማይሰበስብም ይበትንብኛል።
፳፬ "ክፉ ጋኔንም ከሰው በወጣ ጊዜ ውኃ ወደ
ሌለበት ምድረ በዳ ይሄዳል፤ የሚያርፍበትንም
መኖሪያ ይሻል፤ ያላገኘ እንደ ሆነም ወደ ወጣ
ሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል። ፳፭ በመጣም
ጊዜ ተጠርጎ አጊጦም ያገኘዋል። ፳፮ ከዚህም
በኋላ ይሄድና ከእርሱ የሚከፉ ሌሎች ባልንጀ
ሮቹን[፳፩] ሰባት አጋንንት ያመጣል፤ ገብተውም
በዚያ ሰው ያድሩበታል፤ ለዚያ ሰውም ከፊተ
ኛው ይልቅ የኋለኛው የከፋ ይሆንበታል።"

### በአሕዛብ መካከል አሰምታ ስለ ተናገረችው ሴት

፳፯ ከዚህም በኋላ ይህን ሲናገር ከሕዝቡ መካ
ከል አንዲት ሴት ድምፅዋን አሰምታ፥ "የተ
ሸከመችህ ማኅፀን ብፅዕት ናት፤ የጠባሃቸው
ጡቶችም ብፁዓት ናቸው" አለችው። ፳፰ እር
ሱም፥ "ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰም
ተው የሚጠብቁ ናቸው" አላት።

### ምልክትን ስለሚጠይቁ ሰዎች

(ማቴ. ፲፪፥፴፰-፵፪)

፳፱ ብዙ ሰዎችም ተሰብስበው ሳሉ እንዲህ
ይላቸው ጀመረ፥ "ይቺ ትውልድ ክፉ ናት፤
ምልክትም ትሻለች፤ ነገር ግን ከነቢዩ ከዮናስ
ምልክት በቀር ምልክት አይሰጣትም። ፴ ዮናስ
ለነነዌ ሰዎች ምልክት እንደ ሆናቸው የሰው
ልጅም ለዚች ትውልድ እንዲሁ ምልክት ይሆ
ናታል። ፴፩ የአዜብ ንግሥት በፍርድ ቀን ከዚች
ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፋረዳቸዋለች፤ የሰሎ
ሞንን ጥበብ ልትሰማ ከምድር ዳርቻ መጥታለ
ችና፤ እነሆ፥ ከሰሎሞን የሚበልጥ በዚህ አለ።
፴፪ የነነዌ ሰዎች በፍርድ ቀን ከዚች ትውልድ
ጋር ተነሥተው ይፋረዱአታል፤[፳፪] ያሳፍሩአታ
ልም፤[፳፫] ዮናስ በሰበከላቸው ጊዜ ንስሓ ገብተዋ
ልና፤ እነሆ፥ ከዮናስ የሚበልጥ በዚህ አለ።
፴፫ "በስውር ቦታ ወይም ከዕንቅብ በታች ሊያ
ኖራት መብራትን የሚያበራ የለም፤ የሚመላ
ለሱ ሁሉ ብርሃንን ያዩ ዘንድ በመቅረዝዋ ላይ
ያኖራታል እንጂ። ፴፬ የሰውነትህ መብራት ዐይ
ንህ ነው፤ ዐይንህ ብሩህ ከሆነ ሰውነትህ ሁሉ
ብሩህ ነው፤ ዐይንህ ታማሚ ቢሆን ግን፤ ሰው
ነትህ ሁሉ ጨለማ ነው። ፴፭ እንግዲህ ብርሃ
ንህ ጨለማ እንዳይሆን ተጠንቀቅ። ፴፮ ሰውነትህ
ሁሉ ብሩህ ከሆነ በአንተም ላይ ምንም ጨለማ
ባይኖርብህ የመብረቅ ብርሃን እንደሚያበራልህ
ሁለንተናህ ብሩህ ይሆናል።"

### ጌታችን ኢየሱስን ወደ ምሳ ስለ ጠራው ፈሪሳዊ

(ማቴ. ፳፫፥፩-፴፮፤ ማር. ፲፪፥፴፰-፵)

፴፯ ይህንም ሲነግራቸው አንድ ፈሪሳዊ በእርሱ
ዘንድ ምሳ እንዲበላ ለመነው፤ ገብቶም ለምሳ
ተቀመጠ። ፴፰ ፈሪሳዊውም አይቶ አደነቀ፤ ምሳ
ለመብላት እጁን አልታጠበም ነበርና። ፴፱ ጌታ
ችን ኢየሱስም እንዲህ አለው፥ "እናንተ ፈሪ
ሳውያን፥ ዛሬ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭውን
ታጥቡታላችሁ፤ ታጠሩታላችሁም፤ ውስጡ
ግን ቅሚያንና ክፋትን የተመላ ነው። ፵ እናንተ
ሰነፎች፥ የውጭውን የፈጠረ የውስጡንስ የፈ
ጠረ አይደለምን? ፵፩ ነገር ግን የሚወደደውን
ምጽዋት አድርጋችሁ ስጡ፤ ሁሉም ንጹሕ
ይሆንላችኋል። ፵፪ የእንስላልና የጤና አዳም፥
ከአትክልትም ሁሉ ዐስራት የምታገቡ ፍርድ
ንና የእግዚአብሔርን ፍቅር ቸል የምትሉ እና
ንተ ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ወዮላችሁ! ይህንም
ልታደርጉ ይገባችኋል፥ ያንም አትተዉ። ፵፫ እና
ንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ወዮላችሁ!
በምኵራብ ፊት ለፊት መቀመጥን፥ በገበያም
እጅ መነሣትን ትወዳላችሁና። ፵፬ እናንተ ግብ
ዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ወዮላችሁ! ሰዎች
ሳያውቁ በላዩ እንደሚመላለሱበት እንደ ተሰ
ወረ መቃብር ናችሁና።"
፵፭ ከሕግ ዐዋቂዎችም አንዱ መልሶ፥ "መም
ህር ሆይ፥ ይህን ስትል እኛን እኮ መስደብህ
ነው" አለው። ፵፮ እርሱም እንዲህ አለው፤
"ለእናንተ ለሕግ ዐዋቂዎች ወዮላችሁ! ሰውን
ከባድ ሸክም ታሸክሙታላችሁ፤ እናንተ ግን
ያን ሸክም በአንዲት ጣታችሁ እንኳን አትነኩ

---

[፳] "የዘረፈውን" የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ አይገኝም።
[፳፩] "ባልንጀሮቹን" የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ አይገኝም።
[፳፪] በግሪኩ "ይፈርዱባታል" ይላል።
[፳፫] "ያሳፍሩአታልም" የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ አይገኝም።

፲፩፥፳፫ ማር. ፱፥፵።   ፲፩፥፳፱ ማቴ. ፲፪፥፴፱፤ ማር. ፰፥፲፪።   ፲፩፥፴ ዮናስ ፫፥፬።   ፲፩፥፵፪ ዘሌ. ፳፯፥፴።

ትም። ፵፯እናንተ ጻፎችና ፈሪሳውያን÷[፱] ወዮላ
ችሁ! አባቶቻችሁ የገደሉአቸውን የነቢያትን
መቃብር ትሠራላችሁና። ፵፰የአባቶቻችሁም
ሥራ ደስ አሰኝቶአችኋል፤ የምትመሰክሩባቸ
ውም እናንተ ራሳችሁ ናችሁ፤ እነርሱ የገደ
ሉአቸውን መቃብራቸውን እናንተ ትሠራላች
ሁና። ፵፱ስለዚህ የእግዚአብሔር ጥበቡ እንዲህ
አለች፡- እነሆ÷ እኔ ነቢያትንና ሐዋርያትን ወደ
እነርሱ እልካለሁ፤ ከእነርሱም ይገድላሉ፤ ያሳ
ድዳሉም። ፶ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከዚ
ህች ትውልድ ድረስ ስለ ፈሰሰው ስለ ነቢያት
ሁሉ ደም ይበቀላቸው ዘንድ÷ ፶፩ከአቤል ደም
ጀምሮ በመሠዊያውና በቤተ መቅደሱ መካከል
እስከ ገደሉት እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ እው
ነት እላችኋለሁ ከዚች ትውልድ ይፈለጋል።
፶፪እናንተ ጻፎችና ፈሪሳውያን÷ ወዮላችሁ! የጽ
ድቅንና የዕውቀትን መክፈቻ ወስዳችሁ ትሰው
ራላችሁና፤ እናንተም አትገቡምና፤ የሚገቡት
ንም መግባትን ትከለክሉአቸዋላችሁ።” ፶፫በሕ
ዝቡም ሁሉ ፊት ይህን ሲነግራቸው ጻፎችና
ፈሪሳውያን አጽንተው ይጣሉት÷ ይቀየሙትም
ጀመር። ፶፬በአነጋገሩም ሊያስቱትና ሊያጣሉት
ያደቡበት ነበር።

## ምዕራፍ ፲፪

### ስለ ፈሪሳውያን እርሾ

(ማቴ. ፲፡፳፮-፳፯)

፩በዚያን ጊዜም እጅግ ብዙ ሰዎች እርስ በር
ሳቸው እስኪረጋገጡ ድረስ ወደ እርሱ ተሰበ
ሰቡ፤ ደቀ መዛሙርቱንም እንዲህ ይላቸው
ጀመረ÷ “አስቀድማችሁ ከፈሪሳውያን እርሾ
ተጠበቁ፤ ይኸውም ግብዝነት ነው። ፪የማይ
ገለጥ የተሰወረ÷ የማይታይም የተሸሸገ የለ
ምና። ፫በጨለማ የምትናገሩት በብርሃን ይሰ
ማል፤ በእልፍኝም ውስጥ በጆሮ የምትንሾካሾ
ኩት በሰገነት ይሰበካል። ፬ለእናንተ ለወዳጆቼ
እላችኋለሁ፡- ሥጋችሁን የሚገድሉትን አትፍ
ሩአቸው፤ ከዚህም የበለጠ ማድረግ የሚችሉት
የላቸውም። ፭ነገር ግን፤ የምትፈሩትን አሳያ
ችኋለሁ፤ እናንተስ ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም
ሊጥል ሥልጣን ያለውን ፍሩት፤ አዎ÷ እላች
ኋለሁ፤ እርሱን ፍሩ። ፮አምስት ወፎች በሁለት
ሻሚ መሐለቅ ይሸጡ የለምን? ከእነርሱ አን
ዲቱ ስንኳን በእግዚአብሔር ፊት አትረሳም።
፯የእናንተስ የራስ ጠጕራችሁ ሁሉ የተቈጠረ
ነው፤ እንግዲህ አትፍሩ፤ ከብዙ ወፎች እናንተ
ትበልጣላችሁና።

፰“እላችኋለሁ፡- በሰው ፊት የሚያምንብ
ኝን ሁሉ እኔም[፩] በእግዚአብሔር መላእክት
ፊት አምነዋለሁ። ፱በሰው ፊት የሚክደኝን ግን
እኔም በእግዚአብሔር መላእክት ፊት እክደዋ
ለሁ። ፲በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚና
ገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ
የስድብ ቃል የሚናገር ግን በዚህ ዓለምም ሆነ
በሚመጣው ዓለም[፪] አይሰረይለትም። ፲፩ወደ
አደባባይ[፫] ወደ ሹሞቹና ወደ ነገሥታቱ÷ ወደ
መኳንንቱም በሚወስዱአችሁ ጊዜ የምትሉት
ንና የምትናገሩትን አታስቡ። ፲፪ያንጊዜ በእና
ንተ ላይ የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ ነውና።”

### ርስት ሊካፈል ስለ ወደደው ሰው

፲፫ከሕዝቡም አንዱ÷ “መምህር ሆይ÷ ርስ
ቱን እንዲያካፍለኝ ለወንድሜ ንገረው”
አለው። ፲፬ጌታችን ኢየሱስም÷ “አንተ ሰው÷
በእናንተ ላይ አካፋይና ዳኛ አድርጎ ማን
ሾመኝ?” አለው። ፲፭“ዕወቁ፤ ከቅሚያም ሁሉ
ተጠበቁ፤ ሰው የሚድን ገንዘብ በማብዛት አይ
ደለምና” አላቸው።

### እርሻው ስለ በጀለት ባለጸጋ

፲፮ምሳሌም መሰለላቸው፤ እንዲህም አላቸው፤
“እርሻው የበጀለትና ሀገር የተመቸው[፬] አንድ
ባለጸጋ ሰው ነበረ። ፲፯እህሌን የማኖርበት የለኝ
ምና ምን ላድርግ ብሎ በልቡ ዐሰበ። ፲፰እር
ሱም አለ፡- እንዲህ አደርጋለሁ፤ የቀድሞውን
ጎተራዬን አፈርሳለሁ፤ ከእርሱ የሚበልጥ ሌላ
ጎተራም እሠራለሁ፤ እህሌንና በረከቴንም በዚያ
እሰበስባለሁ። ፲፱ሰውነቴንም እንዲህ እላታለሁ፡-
ሰውነቴ ሆይ÷ የሰበሰብሁልሽ ለብዙ ዓመታት

---

፱ “ጻፎችና ፈሪሳውያን” የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ አይገኝም።

፩ በግሪኩ “የሰው ልጅም ...” ይላል።

፪ “በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም” የሚለው በግሪኩ የለም።

፫ በግሪኩ ወደ ምኵራብ” ይላል።

፬ “ሀገር የተመቸው” የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፪፡፩ ማቴ. ፲፮፡፮፤ ማር. ፰፡፲፭። ፲፪፡፪ ማር. ፬፡፳፪፤ ሉቃ. ፰፡፲፯። ፲፪፡፲ ማቴ. ፲፪፡፴፪፤ ማር. ፫፡፳፱።

የሚበቃሽ የደለበ ብዙ ሀብት አለሽ፤ እንግዲህ
ወዲህ ዕረፊ፥ ብዪ፤ ጠጪም፤ ደስም ይበልሽ።
፳እግዚአብሔርም፦ አንተ ሰነፍ! በዚች ሌሊት
ነፍስህን ከሥጋህ ለይተው ይወስዷታል፤ እን
ግዲህ ያጠራቀምኸው ለማን ይሆናል? አለው።
፳፩ሀብትን ለራሱ የሚሰበስብ፤ ሀብቱም ከእግ
ዚአብሔር ያልሆነ እንዲሁ ነው።”

## በከንቱ መጨነቅ ስለማይገባ

(ማቴ. ፮፥፳፭-፴፬)

፳፪ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አላቸው፥
“ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ለነፍሳችሁ ስለምትበሉ
ትና ስለምትጠጡት፥ ለሰውነታችሁም ስለምት
ለብሱት አትጨነቁ። ፳፫ነፍስ ከምግብ ትበልጣለ
ችና፤ ሰውነትም ከልብስ ይበልጣልና። ፳፬የማይ
ዘሩትንና የማያጭዱትን፥ ጎተራና ጕድጓድ የሌ
ላቸውን የቍራዎችን ጫጭቶች[፩] ተመልከቱ፤
እግዚአብሔር ግን ይመግባቸዋል፤ እንግዲህ
እናንተ ከወፎች እንዴት እጅግ አትበልጡም?
፳፭ከእናንተስ ዐስቦ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ
መጨመር የሚቻለው ማነው? ፳፮ይህን ቀላሉን
የማትችሉ ከሆነ በሌላው ለምን ትጨነቃላችሁ?
፳፯እነሆ፥ አበባዎችን እንደሚያድጉ ተመልከቱ፤
አይፈትሉም፤ አይደክሙም፤ ነገር ግን እላችኋ
ለሁ፤ ሰሎሞን እንኳ በክብሩ ዘመን[፪] ሁሉ ከእ
ነርሱ እንደ አንዱ አልለበሰም። ፳፰እነሆ፥ ዛሬ
ያለውን፥ ነገም ወደ እሳት የሚጣለውን የእ
በባ አገዳ እግዚአብሔር እንዲህ የሚያደርገው
ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጐደላችሁ፥ ለእናን
ተማ እንዴት አብልጦ አያደርግላችሁ? ፳፱እና
ንተም የምትበሉትንና የምትጠጡትን አትፈ
ልጉ፤ ወዲያና ወዲህም አትበሉ፤ አትጨነቁለ
ትም። ፴ይህን ሁሉ በውጭ ያሉ የዓለም አሕ
ዛብ ይሹታልና፤ ለእናንተስ አባታችሁ ይህን
ሁሉ እንደምትሹት ያውቃል። ፴፩ነገር ግን የእ
ግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ ሹ፤ ይህም
ሁሉ ይጨመርላችኋል።

፴፪“አንተ ታናሽ መንጋ፥ አትፍራ፤ አባ
ታችሁ መንግሥቱን ሊሰጣችሁ ወዶአልና።
፴፫ሀብታችሁን ሽጣችሁ ምጽዋት ስጡ፤ ሌባ
በማያገኝበት ነቀዝም በማያበላሽበት፥ የማያረጅ
ከረጢት፥ የማያልቅም መዝገብ በሰማያት ለእ
ናንተ አድርጉ። ፴፬መዝገባችሁ ካለበት ልባ
ችሁ በዚያ ይኖራልና።

## ስለ መትጋት

፴፭“ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም
የበራ ይሁን። ፴፮እናንተም፥ በመጣና በር
በመታ ጊዜ ወዲያው ይከፍቱለት ዘንድ ከሰ
ርግ እስኪመለስ ጌታቸውን እንደሚጠብቁ
ሰዎች ሁኑ። ፴፯ጌታቸው በመጣ ጊዜ እን
ዲህ ሲያደርጉና ሲተጉ የሚያገኛቸው አገል
ጋዮች ብፁዓን ናቸው፤ እውነት እላችኋለሁ፤
ወገቡን ታጥቆ በማዕድ ያስቀምጣቸዋል፤ እየ
ተመላለሰም ያገለግላቸዋል። ፴፰ከሌሊቱ በሁ
ለተኛው ወይም በሦስተኛው ክፍል ቢመጣና
እንዲሁ ቢያገኛቸው እነዚያ አገልጋዮች ብፁ
ዓን ናቸው። ፴፱ነገር ግን ይህን ዕወቁ፤ ባለ
ቤት ሌባ የሚመጣበትን ጊዜ ቢያውቅ ተግቶ
በጠበቀ፥ ቤቱንም እንዲቈፍሩት ባልፈቀደም
ነበር። ፵እናንተም ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፤ የሰው
ልጅ ባልጠረጠራችሁበት ሰዓት ይመጣልና።”
፵፩ጴጥሮስም፥ “አቤቱ፥ ይህን ምሳሌ የምት
ናገረው ለእኛ ነውን? ወይስ ለሁሉ ነው?”
አለው። ፵፪ጌታችንም እንዲህ አለው፥ “ምግ
ባቸውን በየጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው
በቤተሰቡ ላይ የሚሾመው ደግ[፫] ታማኝና
ብልህ መጋቢ ማን ይሆን? ፵፫ጌታው በመጣ
ጊዜ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው አገልጋይ
ብፁዕ ነው። ፵፬እውነት እላችኋለሁ፥ በሀብቱ
ሁሉ ላይ ይሾመዋል፤ ፵፭ነገር ግን ያ ክፉ አገ
ልጋይ በልቡ፦ ጌታዬ ቶሎ አይመጣም ቢል፥
በጌታው ቤት ያሉትንም ወንዶችንና ሴቶችን
አገልጋዮች ሊደበድብና ሊያጕላላ ቢጀምር፥
ከሰካራሞችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፥ ቢሰክ
ርም፥ ፵፮የዚያ አገልጋይ ጌታ ባልጠረጠረው
ዕለት፥ ባላወቀውም ሰዓት መጥቶ ከሁለት
ይሰነጥቀዋል፤ ዕድሉንም ከማይታመኑ ጋር
ያደርገዋል። ፵፯የጌታውን ፈቃድ ዐውቆ እንደ
ፈቃዱ የማይሠራና የማያዘጋጅ የዚያ አገልጋይ
ቅጣቱ ብዙ ነው። ፵፰ያላወቀ ግን ባይሠራም
ቅጣቱ ጥቂት ነው፤ ብዙ ከሰጡት ብዙ ይፈ

---

፩ “ጫጭቶች” የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ አይገኝም።

፪ “ዘመን” የሚለው በግሪኩ የለም።

፫ “ደግ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፪፥፳፯ ፩ነገ. ፲፥፬-፯፤ ፪ዜ.መ. ፱፥፫-፮። ፲፪፥፴፭ ማቴ. ፳፭፥፩-፲፫። ፲፪፥፴፮ ማር. ፲፫፥፴፬-፴፮።
፲፪፥፴፱-፵ ማቴ ፳፬፥፵፫-፵፬።

ልጉበታልና። ጥቂት ከሰጡትም ጥቂት ይፈ
ልጉበታልና።፰

### ስለ ሰይፍና ስለ መለያየት
(ማቴ. ፲፥፴፬-፴፮)

፵፱"በምድር ላይ እሳትን አምጥቼአለሁ፤ እር
ስዋን ከማንደድ በቀር ምን እሻለሁ? ፶ነገር
ግን የምጠመቃት ጥምቀት አለችኝ፤ እስክፈጽ
ማትም ድረስ እጅግ እታገሣለሁ።" ፶፩ሕዝቡ
ንም እንዲህ አላቸው፥ "ለምድር ሰላምን ያመ
ጣሁ ይመስላችኋልን? እላችኋለሁ፤ አይደለም፤
ሰይፍንና፱ መለያየትን ነው እንጂ። ፶፪ከእንግዲ
ህስ ወዲህ አምስት ሰዎች በአንድ ቤት ቢኖሩ
ሦስቱ ከሁለቱ፥ ሁለቱም ከሦስቱ ይለያሉ፤፲
፶፫አባት ከልጁ፥ ልጅም ከአባቱ ይለያል፤ እናት
ከልጅዋ፥ ልጅም ከእናቷ ትለያለች፤ አማት
ከምራቷ፥ ምራትም ከአማቷ ትለያለች።"
፶፬ከዚህም በኋላ ሕዝቡን እንዲህ አላቸው፥
"ደመና በምዕራብ በኩል ደምኖ ባያችሁ ጊዜ
'ዝናም ይመጣል' ትላላችሁ፤ እንዲሁም ይሆ
ናል። ፶፭የአዜብ ነፋስ በነፈሰ ጊዜም 'ድርቅ
ይሆናል፤' ትላላችሁ እንዲሁም ይሆናል። ፶፮እና
ንት ግብዞች! የሰማዩንና የምድሩን ፊት መመር
መር ታውቃላችሁ፤ ነገር ግን እነዚህን ዘመናት
መመርመርን እንዴት አታውቁም? ፶፯እናንተ
ራሳችሁ እውነቱን ለምን አትፈርዱም? ፶፰ከባ
ለጋራህ ጋር ወደ ሹም በምትሄድበት ጊዜ ወደ
ዳኛ እንዳይወስድህ በመንገድ ሳለህ ታረቅ፤ ዕዳ
ህንም ክፈል፤ ዳኛው ለሎሌው አሳልፎ ይሰጥሃ
ልና። ሎሌውም በወኅኒ ቤት ያስርሃል። ፶፱ያለብ
ህን የመጨረሻዋን ግማሽ ሣንቲም ቢሆን እስክ
ትጨርስ ድረስ አትወጣም እልሃለሁ።"

## ምዕራፍ ፲፫

### ስለ ንስሓ

፩በዚያ ወራትም ሰዎች ወደ እርሱ መጥተው
ጲላጦስ ደማቸውን ከመሥዋዕታቸው ጋር ስለ
ቀላቀለው ስለ ገሊላ ሰዎች ነገሩት። ፪ጌታችን
ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ "ይህች
መከራ ስለ አገኘቻቸው እነዚህ ገሊላውያን ከገ
ሊላ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ተለይተው ኀጢአተ
ኞች የሆኑ ይመስሉአችኋልን? ፫አይደለም፤ እላ
ችኋለሁ፤ እናንተም ንስሓ ካልገባችሁ ሁላችሁ
እንደ እነርሱ ትጠፋላችሁ። ፬ወይስ እነዚያ በሰ
ሊሆም ግንብ ተጭኖ የገደላቸው ዐሥራ ስም
ንቱ ሰዎች ከኢየሩሳሌም ሰዎች ይልቅ ተለይ
ተው ኀጢአተኞች ይመስሉአችኋልን? ፭አይደ
ለም፤ እላችኋለሁ፤ እናንተም ንስሓ ካልገባችሁ
ሁላችሁ እንደ እነርሱ ትጠፋላችሁ።"

### ፍሬ ስለሌላት በለስ

፮እንዲህም ብሎ መሰለላቸው፥ "አንድ ሰው
በታወቀች በወይኑ ቦታ ውስጥ፩ በለስ ነበረ
ችው፤ ፍሬዋን ሊወስድ ወደ እርስዋ ሄዶ አላ
ገኘም። ፯የወይኑን ጠባቂም፡-፪ 'የዚችን በለስ
ፍሬ ልወስድ ስመላለስ እነሆ፥ ሦስት ዓመት
ነው፤ አላገኘሁም፤ እንግዲህስ ምድራችንን እን
ዳታበዝን ቍረጣት' አለው። ፰እርሱም መልሶ
እንዲህ አለው፥ 'አቤቱ አፈር ቈፍሬ በሥሯ
እስከ አስታቅፋት፥ ፍግም እስከ አፈስባት
ድረስ የዘንድሮን እንኳ ተዋት። ፱ምናልባት
ለከርሞ ታፈራ እንደ ሆነ፥ ያለዚያ ግን እንቈ
ርጣታለን።'"

### በሰንበት ቀን ስለ ዳነችው ሴት

፲በሰንበትም በአንድ ምኵራብ ውስጥ አስተማ
ራቸው። ፲፩ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ ጋኔን
ያጐበጣት አንዲት ሴት ነበረች፤ ጐባጣም ነበ
ረች፤ ከቶ ቀጥ ብላ መቆም አትችልም ነበር።
፲፪ጌታችን ኢየሱስም አይቶ ራራላት፥፫ ጠር
ቶም፥ "ሴትዮ፥ ከደዌሽ ተፈትተሻል" አላት።
፲፫እጁንም በላይዋ ጫነ፤ ያንጊዜም ፈጥና ቀጥ
አለች፤ እግዚአብሔርንም አመሰገነችው። ፲፬የም
ኵራቡ ሹምም ጌታ ኢየሱስ በሰንበት ፈውሶ
አልና፤ እየተቈጣ መልሶ ሕዝቡን እንዲህ አላ
ቸው፥ "ሥራችሁን የምትሠሩባቸው ስድስት
ቀኖች ያሉ አይደለምን? ያንጊዜ ኑና ተፈወሱ፤

---

፰ በግሪኩ እና አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ "ብዙ አደራ ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል" ይላል።
፱ በግሪኩ "ሰይፍን" የሚል የለም።
፲ በግሪኩ እና በብዙ የግእዝ ዘርዕ "አንዱም ከሌላው ይለያል" የሚል ይጨምራል።
፩ በግሪኩ "የተተከለች" ይላል።
፪ በግሪኩ "የወይን አትክልት ሠራተኛውን" ይላል።
፫ በግሪኩ "ራራላት" አይልም።
፲፪፥፶ ማር. ፲፥፴፰።   ፲፪፥፶፫ ሚክ. ፯፥፮።   ፲፫፥፲፬ ዘፀ. ፳፥፱-፲፤ ዘዳ. ፭፥፲፫-፲፬።

በሰንበት ቀን ግን አይሆንም።” ፲፭ጌታችን ኢየ
ሱስም መልሶ አላቸው፥ “እናንት ግብዞች፥
እናንተሳ አህያችሁን ወይም በሬአችሁን በሰን
በት ቀን ገለባ ከሚበላበት አትፈቱትምን? ውኃ
ልታጠጡትስ አትወስዱትምን? ፲፮ይህቺ የአብር
ሃም ልጅ እነሆ፥ ሰይጣን ከአሰራት ዐሥራ ስም
ንት ዓመት ነው፤ እርስዋስ በሰንበት ቀን ከእ
ስራቷ ልትፈታ አይገባምን?” ፲፯ይህንም ባለ
ጊዜ በእርሱ ላይ በጠላትነት የተነሡበት ሁሉ
አፈሩ፤ ነገር ግን ሕዝቡ ሁሉ ከእርሱ ስለሚደ
ረገው ድንቅ ነገር ሁሉ ደስ አላቸው።

## ስለ ሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌ

(ማቴ. ፲፫፥፴፩-፴፪፤ ማር. ፬፥፴-፴፪)

፲፰በዚያ ቀንም ጌታችን ኢየሱስ እንዲህ አላ
ቸው፥ “መንግሥተ ሰማያት[፩] ምን ትመስላ
ለች? በምንስ እመስላታለሁ? ፲፱ሰው ወስዶ በእ
ርሻ ውስጥ የዘራት የሰናፍጭ ቅንጣትን ትመስ
ላለች፤ አደገች፤ ታላቅ ዛፍም ሆነች፤ የሰማይ
ወፎችም በቅርንጫፎችዋ ውስጥ ተጠለሉ።”

## ስለ እርሾ

(ማቴ. ፲፫፥፴፫)

፳ዳግመኛም እንዲህ አለ፥ “የእግዚአብሔ
ርን መንግሥት በምን እመስላታለሁ? ፳፩ሴት
ወስዳ ሦስት መስፈሪያ ዱቄት የለወሰችበትን፥
ሁሉንም እንዲቦካ ያደረገውን እርሾ ትመስላ
ለች።”

## ስለሚድኑት

(ማቴ. ፯፥፲፫-፲፬፤ ፳፩-፳፫)

፳፪በየከተማውና በየመንደሩ እየሄደ፥ በኢየሩ
ሳሌምም እየተመላለሰ ያስተምር ነበር። ፳፫አንድ
ሰውም፥ “አቤቱ የሚድኑ ጥቂቶች ናቸውን?”
አለው። እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፡- ፳፬“ወደ
ጠባቡ በር ትገቡ ዘንድ በርቱ፤ እላችኋለሁ፥
ሊገቡ የሚሹ ብዙዎች ናቸው፤ ግን አይች
ሉም። ፳፭ባለቤቱ ተነሥቶ ደጁን ይዘጋልና፤
ያንጊዜ ከደጅ ቆመው፡- ‘አቤቱ፥ አቤቱ፥ ክፈ
ትልን’ እያሉ በር ሊመቱ ይጀምራሉ፤ መል
ሶም፡- ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላውቃችሁም
ይላቸዋል። ፳፮ከዚህም በኋላ፡- በፊትህ በላን፥
ጠጣን፥ በአደባባያችንም አስተማርህ ልትሉ
ትጀምራላችሁ። ፳፯እርሱም እንዲህ ይላቸ
ዋል፡- እናንተ ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላውቃ
ችሁም፤ ዐመፅን የምታደርጉ ሁላችሁ፥ ከእኔ
ራቁ፤ ፳፰አብርሃምን፥ ይስሐቅንና ያዕቆብን፥
ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት
በአያችኋቸው ጊዜ እናንተን ወደ ውጭ ያወ
ጡአችኋል፤ በዚያም ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት
ይሆናል። ፳፱ከምሥራቅና ከምዕራብ፥ ከሰሜንና
ከደቡብ ይመጣሉ፤ በእግዚአብሔርም መንግ
ሥት በማዕድ ይቀመጣሉ፤ ፴ኋለኞች ፊተኞች
ይሆናሉ፤ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ።”

## ስለ ሄሮድስ

፴፩በዚያችም ቀን ከፈሪሳውያን ወገን ሰዎች
መጥተው፥ “ከዚህ ውጣና ሂድ፤ ሄሮድስ ሊገ
ድልህ ይሻልና” አሉት። ፴፪እርሱም እንዲህ
አላቸው፥ “ሂዱና ያችን ቀበሮ እንዲህ በሉ
አት፤ እነሆ፥ ዛሬና ነገ አጋንንትን አወጣለሁ፤
ሕይወትንም አድላለሁ፤ በሦስተኛውም ቀን
እፈጽማለሁ። ፴፫ዛሬና ነገስ አለሁ፤ በሦስተኛው
ቀን ግን እሄዳለሁ፤[፪] ነቢይ በኢየሩሳሌም እንጂ
በውጭ ሊሞት አይገባውምና።

## ስለ ኢየሩሳሌም መፈታት

(ማቴ. ፳፫፥፴፯-፴፱)

፴፬“ነቢያትን የምትገድሊያቸው፥ ወደ አንቺ
የተላኩትን ሐዋርያትንም የምትደበድቢያቸው
ኢየሩሳሌም፥ ኢየሩሳሌም፥ ዶሮ ጫጩቶች
ዋን ከክንፍዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆች
ሽን ልሰበስባቸው ምን ያህል ወደድሁ? ነገር
ግን እንቢ አላችሁ። ፴፭እነሆ፥ ቤታችሁ ምድረ
በዳ ሆኖ ይቀርላችኋል፤ ከዛሬ ወዲያ ‘በእግዚ
አብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው’ እስክትሉ
ድረስ እንደማታዩኝ እነግራችኋለሁ።”

## ምዕራፍ ፲፬

### ሆዱ የተነፋውን ሰው እንደ ፈወሰ

፩ከዚህም በኋላ ሄዶ ከፈሪሳውያን አለቆች ወደ
አንዱ ቤት በሰንበት ቀን እህል ሊበላ ገባ፤ እነ
ርሱ ግን ይጠባበቁት ነበር። ፪እነሆም፥ ሆዱ የተነፋ

---

[፩] በግሪኩ “መንግሥተ እግዚአብሔር” ይላል።

[፪] በግሪኩ “ዛሬና ነገ ከነገ ወዲያም እሄዳለሁ” ይላል።

፲፫፥፳፯ መዝ. ፮፥፰። ፲፫፥፳፰ ማቴ. ፳፬፥፲፫፤ ፳፭፥፴። ፲፫፥፳፱ ማቴ. ፰፥፲፩-፲፪።
፲፫፥፴ ማቴ. ፲፱፥፴፤ ፳፥፲፮፤ ማር. ፲፥፴፩። ፲፫፥፴፭ መዝ. ፻፲፯፥፳፮፤ ኤር. ፳፪፥፭።

አንድ ሰው በፊቱ ነበር። ፫ጌታችን ኢየሱስም መልሶ
ሕግ ዐዋቂዎችንና ፈሪሳውያንን፥ “በሰንበት ድውይ
መፈወስ ይገባልን? ወይስ አይገባም?” ብሎ ጠየ
ቃቸው። ፬እነርሱም ዝም አሉ፤ ይዞም ፈወሰውና
ሰደደው። ፭“ከእናንተ በሬው ወይም አህያው በጕ
ድጓድ ውስጥ የወደቀበት አንድ ሰው ቢኖር ዕለቱን
በሰንበት ቀን ያነሣው የለምን?” አላቸው። ፮ስለዚ
ህም ነገር ሊመልሱለት አልተቻላቸውም።

## በራስጌ መቀመጥን ስለሚወዱ ሰዎች

፯በምሳ ላይ ለነበሩትም ወደ ላይኛው ወንበር ሲሽ
ቀዳደሙ ባያቸው ጊዜ ምሳሌ መስሎ አስተማራ
ቸው። ፰እንዲህም አለ፥ “ለምሳ[፩] የጠራህ ሰው ቢኖ
ርና ብትሄድ በላይኛው መቀመጫ አትቀመጥ፤ ምና
ልባት ከአንተ የሚበልጥ ይመጣ ይሆናል። ፱በኋላ ያ
አንተንም እርሱንም የጠራ መጥቶ፡- ይህን ቦታ ለእ
ርሱ ተውለት ይልሃልና፤ ያንጊዜም አፍረህ ትመ
ለሳለህ፤ ወደ ዝቅተኛ ቦታም ትወርዳለህ። ፲የጠ
ራህ ሰው ቢኖርና ብትሄድ ግን የጠራህ በመጣ ጊዜ
ወዳጄ ወደ ላይኛው መቀመጫ ውጣ ይልህ ዘንድ
በታችኛው መቀመጫ ተቀመጥ፤ ያንጊዜም ከአንተ
ጋር ለማዕድ በተቀመጡት ሰዎች ፊት ክብር ይሆን
ልሃል። ፲፩ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፤
ራሱንም ያሚያዋርድ ከፍ ይላልና።”

፲፪የጠራውንም እንዲህ አለው፥ “በበዓል ምሳ
ወይም ራት በምታደርግበት ጊዜ ወዳጆችህንና
ወንድሞችህን፥ ዘመዶችህንና ጎረቤቶችህን፥ ባለጸ
ጎች ባልንጀሮችህንም አትጥራ፤ እነርሱም ይጠሩሃ
ልና፤ ብድርም ይሆንብሃልና። ፲፫ነገር ግን በበዓል
ምሳ በምታደርግበት ጊዜ ድሆችንና ጦም አዳሪዎ
ችን፥ ዕውሮችን፥ እጅና እግርም የሌላቸውን ጥራ።
፲፬አንተም ብፁዕ ትሆናለህ፤ የሚከፍሉህ የላቸው
ምና፤ ነገር ግን ጻድቃን በሚነሡበት ጊዜ ዋጋህን
ታገኛለህ።” ፲፭ለምሳ ከተቀመጡትም አንዱ ይህን
ሰምቶ፥ “በእግዚአብሔር መንግሥት እህል የሚበላ
ብፁዕ ነው” አለው።

## ለምሳ ስለ መጠራት
(ማቴ. ፳፪፥፩-፲)

፲፮ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥
“አንድ ሰው ታላቅ ምሳ[፪] አደረገና ብዙ ሰዎ
ችን ጠራ። ፲፯ለምሳ የተጠሩበትም ቀን በደ
ረሰ ጊዜ የታደሙትን ይጠራቸው ዘንድ አገል
ጋዩን ላከ፤ እርሱም ሄዶ የታደሙትን፡- አሁን
ምሳውን ፈጽመን አዘጋጅተናልና ኑ አላቸው።
፲፰ሁሉም በአንድ ቃል ተባብረው እንቢ አሉ፤
የመጀመሪያው፡- እርሻ ገዝቼአለሁ፤ ሄጄም
ላያት እሻለሁ፤ እንቢ እንደ አላልሁ ቍጠር
ልኝ በለው አለው። ፲፱ሁለተኛውም፡- አምስት
ጥማድ በሬ ገዝቻለሁ፤ ላያቸውና ልፈትናቸው
እሄዳለሁ፤ እንደ መጣሁ፥ እንቢ እንደ አላ
ልሁም ቍጠርልኝ በለው አለው። ፳ሦስተኛ
ውም፡- ሚስት አግብቻለሁ፤ ስለዚህ ልመጣ
አልችልም በለው አለው። ፳፩አገልጋዩም ተመ
ልሶ ለጌታው ይህንኑ ነገረው፤ ያንጊዜም ባለ
ቤቱ ተቈጣ፤ አገልጋዩንም፡- ፈጥነህ ወደ አደ
ባባይና ወደ ከተማው ጐዳና ሂድ፤ ድሆች
ንና ጦም አዳሪዎችን፥ ዕውሮችንና አንካሶችን
ወደዚህ አምጣልኝ አለው። ፳፪ከዚህም በኋላ
አገልጋዩ፡- አቤቱ እንደ አዘዝኸኝ አደረግሁ፤
ገናም ቦታ አለ አለው። ፳፫ጌታውም አገልጋ
ዩን፡- ወደ መንገዶችና ወደ ከተማው ቅጥር
ፈጥነህ ሂድና ቤቱ እንዲመላ ይገቡ ዘንድ ግድ
በላቸው አለው። ፳፬ከእነዚህ ከታደሙት ሰዎች
አንዱ ስንኳን ማዕዴን[፫] እንደማይቀምሳት እነግ
ራችኋለሁ።”

## ጌታን ስለ መከተል
(ማቴ. ፲፥፴፯፡፴፰)

፳፭ከዚህም በኋላ ብዙ ሰዎች አብረውት
ሲሄዱ መለስ ብሎ እንዲህ አላቸው። ፳፮“ወደ
እኔ የሚመጣ፥ ሊከተለኝም የሚወድ አባቱ
ንና እናቱን፥ ሚስቱንና ልጆቹን፥ ወንድሞቹ
ንና እኅቶቹን፥ የራሱንም ሰውነት እንኳ ቢሆን
የማይጠላ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።
፳፯መስቀሉን ተሸክሞ ሊከተለኝ የማይመጣ ደቀ
መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።”

## ቤት ስለሚሠራው ሰው ምሳሌ

፳፰“ከእናንተም ወገን የግንብ ቤት መሥራት
የሚወድ ቢኖር ይጨርሰው ዘንድ የሚችል
እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ የሚፈጅበትን

---

፩ በግሪኩ “ለሰርግ” ይላል።

፪ በግሪኩ “ራት” ይላል።

፫ በግሪኩና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ “ራቱን” ይላል።

፲፬፥፭ ማቴ. ፲፪፥፲፩። ፲፬፥፲፩ ማቴ. ፳፫፥፲፪፤ ሉቃ. ፲፰፥፲፬። ፲፬፥፳፮ ማቴ. ፲፥፴፯።

፲፬፥፳፯ ማቴ. ፲፥፴፰፤ ፲፮፥፳፬፤ ማር. ፰፥፴፬፤ ሉቃ. ፱፥፳፫።

የማያስብ ማን ነው? ፳፱መሠረቱን ጥሎ መጨ
ረስ ያቃተውም እንደ ሆነ ያዩት ሁሉ፥ ፴‘ይህ
ሰው ሊሠራ ጀመረ፤ ግን መጨረስ ተሳነው’
እያሉ ሊዘብቱበት ይጀምራሉ። ፴፩ንጉሥም ሌላ
ውን ንጉሥ ይወጋ ዘንድ ሊሄድ ቢወድ ሁለት
እልፍ ይዞ ወደ እርሱ የሚመጣውን በአንድ
እልፍ ሊዋጋው ይችል እንደ ሆነ አስቀድሞ
ተቀምጦ ይመክር የለምን? ፴፪ያለዚያ ግን፥
ገና በሩቁ ሳለ አማላጆች መልእክተኞችን ልኮ
ዕርቅ ይለምናል። ፴፫እንግዲህ እንደዚሁ ከእና
ንተ ወገን ከሁሉ ያልወጣ፥ የእርሱ ገንዘብ ከሆ
ነውም ሁሉ ያልተለየ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን
አይችልም።

፴፬“ጨው መልካም ነው፤ ጨው አልጫ
ከሆነ እንግዲህ በምን ያጣፍጡታል? ፴፭ለም
ድርም ቢሆን፥ ለፍግ መቆለያም ቢሆን አይረ
ባም፤ ነገር ግን ወደ ውጭ ይጥሉታል፤ የሚ
ሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።”

## ምዕራፍ ፲፭

### ስለ ባለ መቶ በጎች ምሳሌ

(ማቴ. ፲፰፥፲፪፡፲፫)

፩ቀራጮችና ኀጢአተኞችም ሊሰሙት ወደ
እርሱ ይቀርቡ ነበር። ፪ጻፎችና ፈሪሳውያንም፥
“ይህስ ኀጢአተኞችን ይቀበላል፤ አብሮአቸ
ውም ይበላል” ብለው አንጐራጐሩ። ፫እንዲህም
ብሎ መሰለላቸው። ፬“ከእናንተ መካከል መቶ
በጎች ያሉት ሰው ቢኖር፥ ከእነርሱ አንዲቱ ብት
ጠፋው ዘጠና ዘጠኙን በምድረ በዳ ትቶ እስኪ
ያገኛት ድረስ ይፈልጋት ዘንድ ወደ ጠፋችው
ይሄድ የለምን? ፭በአገኛትም ጊዜ ደስ ብሎት
በትከሻው ላይ ይሸከማታል። ፮ወደ ቤቱም በገባ
ጊዜ፥ ወዳጆቹንና ጎረቤቶቹን ጠርቶ፡- የጠፋች
ኝን በጌን አግኝቼአታለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበ
ላችሁ ይላቸዋል። ፯እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሓ
ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኙ ጻድቃን ይልቅ
ንስሓ ስለሚገባ ስለ አንድ ኀጢአተኛ በሰማያት
ፍጹም ደስታ ይሆናል።

### ድሪም ስለ ጠፋባት ሴት

፰“ዐሥር ድሪም ያላት ሴት ብትኖር፥ አን
ዲቱ ብትጠፋባት መብራት አብርታ በቤቷ
ያለውን ሁሉ እየፈነቀለች እስክታገኛት ድረስ
ተግታ ትፈልግ የለምን? ፱ያገኘቻት እንደ ሆነም
ወዳጆችዋንና ጎረቤቶችዋን ጠርታ፡- ‘የጠፋች
ኝን ድሪሜን አግኝቼአታለሁና፥ ከእኔ ጋር ደስ
ይበላችሁ’ ትላቸዋለች። ፲እላችኋለሁ፥ እንዲሁ
ንስሓ ስለሚገባ ስለ አንድ ኀጢአተኛ በእግ
ዚአብሔር መላእክት ፊት በሰማያት[፭] ደስታ
ይሆናል።”

### ሁለት ልጆች ስላሉት ሰው

፲፩ዳግመኛም እንዲህ አለ፥ “አንድ ሰው
ሁለት ልጆች ነበሩት። ፲፪ታናሹ ልጁም አባ
ቱን፡- ‘አባቴ ሆይ፥ ከገንዘብህ የሚደርሰኝን
ከፍለህ ስጠኝ’ አለው፤ ገንዘቡንም ከፍሎ
ሰጠው። ፲፫ከጥቂት ቀን በኋላም ያ ትንሹ ልጁ
ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሩቅ ሀገር ሄደ፤ በዚ
ያም በመዳራት እየኖረ ገንዘቡን ሁሉ በተነ፤
አጠፋም። ፲፬ገንዘቡንም ሁሉ በጨረሰ ጊዜ፥
በዚያ ሀገር ጽኑ ራብ መጣ፤ እርሱም ተቸ
ገረ። ፲፭ሄዶም ከዚያ ሀገር ሰዎች ለአንዱ ተቀ
ጠረ፤ እሪያዎችንም ይጠብቅ ዘንድ ወደ እር
ሻው ቦታ ሰደደው። ፲፮እሪያዎች ከሚመገቡት
ተረንቃሞም ይጠግብ ዘንድ ተመኘ፤ ግን የሚ
ሰጠው አልነበረም። ፲፯በልቡም እንዲህ ብሎ
ዐሰበ፡- እህል የሚተርፋቸው የአባቴ ሠራተኞች
ምን ያህል ናቸው? እኔ ግን በዚህ በረኃብ
ልሞት ነው። ፲፰ተነሥቼ ወደ አባቴ ልሂድና
እንዲህ ልበለው፡- ‘አባቴ ሆይ፥ በሰማይም፥
በፊትህም በደልሁ። ፲፱እንግዲህ ወዲህስ ልጅህ
ልባል አይገባኝም፤ ከአገልጋዮችህ እንደ አንዱ
አድርገኝ።’ ፳ተነሥቶም ወደ አባቱ ሄደ፤ አባ
ቱም ከሩቅ አየውና ራራለት፤ ሮጦም አንገቱን
አቅፎ ሳመው። ፳፩ልጁም፡- ‘አባቴ ሆይ፥ በሰ
ማይም፥ በፊትህም በደልሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህ
ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ነገር ግን ከአገልጋ
ዮችህ እንደ አንዱ አድርገኝ’[፮] አለው። ፳፪አባ
ቱም አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው፡- ‘ያማሩ
ልብሶችን ቶሎ አምጡና አልብሱት፤ ለጣቱም
ቀለበት፥ ለእግሩም ጫማ አድርጉለት፤’ ፳፫የሰባ
ውን ፍሪዳም አምጡና እረዱ፤ እንብላ፤ ደስም
ይበለን። ፳፬ይህ ልጄ ሞቶ ነበር፤ አሁን ግን
ሕያው ሆኖአልና፥ ጠፍቶም ነበር፤ ተገኝቶአ
ልና ደስ ይላቸውም ጀመር።

---

፭ “በሰማያት” የሚለው በግሪኩና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።

፮ “ነገር ግን ከአገልጋዮችህ እንደ አንዱ አድርገኝ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፭፡፩-፯ ማቴ. ፲፰፥፲፪-፲፬። ፲፭፥፲፪ ሉቃ. ፳፥፳፱-፴።

፳፭“ታላቁ ልጁም በእርሻ ነበርና ተመልሶ ወደ
ቤቱ አጠገብ በደረሰ ጊዜ የዘፈኑንና የመሰንቆ
ውን ድምፅ ሰማ። ፳፮ከአባቱ ብላቴኖችም አንዱን
ጠርቶ፦ ‘ይህ የምሰማው ምንድን ነው?’ አለው።
፳፯እርሱም፦ ‘ወንድምህ ከሄደበት መጣ፤ አባት
ህም የሰባውን ፍሪዳ አረደ፤ በሕይወት አግኝቶ
ታልና’ አለው። ፳፰ተቈጥቶም ‘አልገባም’ አለ፤
አባቱም ወጥቶ ማለደው። ፳፱መልሶም አባቱን
እንዲህ አለው፦ ‘እነሆ፥ ይህን ያህል ዓመት ተገ
ዛሁልህ፤ ፈጽሞ ከትእዛዝህ አልወጣሁም፤ ለእኔ
ግን ከባልንጀሮቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ የፍየል
ጠቦት እንኳ አልሰጠኸኝም። ፴ከአመንዝሮች ጋር
ገንዘብህን ሁሉ የጨረሰ ይህ ልጅህ በተመለሰ
ጊዜ ግን የሰባውን ፍሪዳ አረድህለት።’ ፴፩አባ
ቱም እንዲህ አለው፦ ‘ልጄ አንተማ እኮ ዘወትር
ከእኔ ጋር ነህ፤ የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው።
፴፪ነገር ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበረ፤ ሕያው
ሆኖአልና፥ ጠፍቶም ተገኝቶአልና፥ ደስ ሊለን፥
ሐሤትም ልናደርግ ይገባል።”

## ምዕራፍ ፲፮

### ስለ ዐመፀኛው መጋቢ

፩ጌታችን ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ
አላቸው፥ “መጋቢ የነበረው አንድ ባለጸጋ ሰው
ነበረ፤ ገንዘቡን ሁሉ እንደሚበትን አድርገው በእ
ርሱ ዘንድ ከሰሱት። ፪ጌታውም ጠርቶ፦ ‘በአ
ንተ ላይ የምሰማው ይህ ነገር ምንድን ነው?
እንግዲህ ወዲህ ለእኔ መጋቢ ልትሆን አትችል
ምና የመጋቢነትህን ሂሳብ አስረክበኝ’ አለው።
፫ያም መጋቢ ዐስቦ እንዲህ አለ፦ ‘ምን ላድ
ርግ? አሁን ጌታዬ ከመጋቢነቴ ይሽረኛል፤ ማረስ
አልችልም፤ ለመለመንም አፍራለሁ። ፬እንግዲህ
ጌታዬ ከምግብናዬ የሻረኝ እንደ ሆነ በቤታቸው
ይቀበሉኝ ዘንድ የማደርገውን እኔ ዐውቃለሁ።’
፭ለጌታውም ዕዳ የሚከፍሉትን ጠራቸው፤ የመ
ጀመሪያውንም፦ ‘ለጌታዬ የምትከፍለው ዕዳ
ምን ያህል ነው?’ አለው፤ እርሱም፦ ‘መቶ
ማድጋ ዘይት ነው’ አለው። ፮‘እነሆ፥ ደብዳቤህ፤
ተቀምጠህ አምሳ ማድጋ አለብኝ ብለህ ፈጥነህ
ጻፍ’ አለው። ፯ሁለተኛውንም፦ ‘አንተሳ ለጌታዬ
የምትከፍለው ዕዳ ምን ያህል ነው?’ አለው፤
እርሱም፦ ‘መቶ ማድጋ ስንዴ ነው’ አለው፤
‘እነሆ፥ ደብዳቤህ፤ ተቀምጠህ ሰማንያ አለብኝ
ብለህ ፈጥነህ ጻፍ’ አለው። ፰ጌታውም ዐመፀኛ
ውን መጋቢ እንደ ብልህ ሰው ስለ ሥራ አመሰገ
ነው፤ ከብርሃን ልጆች ይልቅ የዚህ ዓለም ልጆች
በዓለማቸው ይራቀቃሉና። ፱እኔም እላችኋለሁ፦
ባለቀባችሁ ጊዜ እነርሱ በዘለዓለም ቤታቸው[፩]
ይቀበሉአችሁ ዘንድ በዐመፃ ገንዘብ ለእናንተ
ወዳጆች አድርጉበት።

፲“በጥቂት የሚታመን በብዙ ይታመናል፤ በጥ
ቂት የሚያምፅም በብዙም ቢሆን ያምፃል። ፲፩በዐ
መፃ ገንዘብ ካልታመናችሁ በእውነተኛው ገንዘብ
ማን ያምናችኋል? ፲፪በሌላውስ ገንዘብ ካልታ
መናችሁ የራሱን[፪] ማን ይሰጣችኋል? ፲፫ለሁለት
ጌቶች መገዛት የሚችል አገልጋይ የለም፤ ካል
ሆነም አንዱን ይወድዳል፤ ሁለተኛውንም ይጠ
ላል፤ ወይም ለአንዱ ይታዘዛል፤ ለሁለተኛውም
እንቢ ይላል፤ እንዲሁም እናንተ ገንዘብ እየወደዳ
ችሁ ለእግዚአብሔር መገዛት አትችሉም።”

፲፬ገንዘብን የሚወዱ ፈሪሳውያንም ይህን ሁሉ
ነገር ሰምተው ተጠቃቀሱበት። ፲፭እርሱም፥
“እናንተስ ለሰው ይምሰል ትመጻደቃላችሁ፤
እግዚአብሔርም ልቡናችሁን ያውቃል፤ በሰው
ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀ[፫]
ይሆናልና።

### ስለ ኦሪትና ስለ ነቢያት

(ማቴ. ፲፩፥፲፪-፲፫፤ ማር. ፲፥፲፩-፲፪)

፲፮“ኦሪትም ነቢያትም ከጥንት ጀምሮ እስከ
ዮሐንስ ድረስ ነበሩ፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የእግዚ
አብሔር መንግሥት ይሰበካል፤ ሁሉም ወደ እር
ስዋ ይጋፋል። ፲፯ነገር ግን ከኦሪት አንዲት ቃል[፬]
ከምትወድቅ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል።
፲፰“ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ
ያመነዝራል፤ ባልዋ የፈታትንም የሚያገባ ያመ
ነዝራል።[፭]

---

፩ በግሪኩ “በዘለዓለም ቤቶች” ይላል።

፪ በግሪኩ “የእናንተን” ይላል።

፫ በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ “የረከሰ” ይላል።

፬ በግሪኩ “አንዲት ነቍጣ” ይላል።

፭ “ባልዋ የፈታትም ሌላ ወንድ ብታገባ ታመነዝራለች” የሚል ንባብ በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ ይገኛል።

፲፮፥፲፫ ማቴ. ፮፥፳፬። ፲፮፥፲፮ ማቴ. ፲፩፥፲፪-፲፫። ፲፮፥፲፯ ማቴ. ፭፥፲፰።
፲፮፥፲፰ ማቴ. ፭፥፴፪፤ ፩ቆሮ. ፯፥፲-፲፩።

### ስለ አንድ ባለጸጋና ስለ አልዓዛር

፲፱“አንድ ባለጸጋ ሰው ነበረ፤ ቀይ ሐርና ነጭ
ሐር፥ እጅግም ቀጭን ልብስ ይለብስ ነበር፤ ዘወ
ትርም ተድላና ደስታ ያደርግ ነበር። ፳በቍስል
ሕመም ተይዞ በባለጸጋው ደጅ የወደቀ አልዓዛር
የሚባል አንድ ድሃም ነበረ። ፳፩ከባለጸጋው ማዕድ
የሚወድቀውንም ፍርፋሪ ሊመገብ ይመኝ ነበር፤
ውሾችም እየመጡ ቍስሉን ይልሱት ነበር።
፳፪ከዚህም በኋላ ድሃው ሞተ፤ መላእክትም ወደ
አብርሃም አጠገብ ወሰዱት፤ ባለጸጋውም ደግሞ
ሞተ፤ ተቀበረም፤ ፳፫በሲኦልም በሥቃይ ሳለ ዐይ
ኖቹን አንሥቶ አብርሃምን ከሩቅ አየው፤ አልዓዛ
ርንም በአጠገቡ ተቀምጦ አየው። ፳፬‘አባት አብር
ሃም ሆይ፥ እዘንልኝ፤ በዚች እሳት እጅግ ተሠቃይ
ቻለሁና፥ ጣቱን ከውኃ ነክሮ ምላሴን ያቀዘቅዝልኝ
ዘንድ አልዓዛርን ላከው’ ብሎ ተጣራ። ፳፭አብር
ሃም ግን እንዲህ አለው፦ ‘ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕ
ይወትህ ተድላና ደስታ እንዳደረግህ፥ አልዓዛርም
እንዲሁ ሁልጊዜ በችጋር እንደ ነበረ ዐስብ፤ አሁን
ግን እንዲሁ እርሱ በዚህ ፈጽሞ ተድላና ደስታ
ያደርጋል፤ አንተ ግን መከራ ትቀበላለህ። ፳፮ከዚ
ህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ማለፍ የሚሹ
እንዳይችሉ፥ ከእናንተ ወገን የሆኑትም ወደ እኛ
እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ
ገደል አለ’ ፳፯እርሱም እንዲህ አለው፦ ‘አባት
አብርሃም ሆይ፥ አልዓዛርን ወደ አባቴ ቤት እን
ድትልከው እለምንሃለሁ። ፳፰አምስት ወንድሞች
ስለ አሉኝ ይንገራቸው፤ እነርሱም ደግሞ ወደ
ዚች የሥቃይ ቦታ እንዳይመጡ ይስሙ።’፮ ፳፱አብ
ርሃምም፦ ‘ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን
ይስሙ’ አለው። ፴እርሱም፦ ‘የለም፤ አባት አብ
ርሃም ሆይ፥ ከሙታን አንዱ ወደ እነርሱ ካልሄደና
ካልነገራቸው ንስሓ አይገቡም’ አለው። ፴፩አብርሃ
ምም፦ ‘ሙሴንና ነቢያትን ካልሰሙማ ከሙታን
ተለይቶ የተነሣ ቢኖርም እንኳ አይሰሙትም፤ አያ
ምኑትምም’ አለው።”

## ምዕራፍ ፲፯

### ስለ ጥፋት መምጣት

(ማቴ. ፲፰፥፮፡፯፤ ማር. ፱፥፵፪)

፩ጌታችን ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ እን
ዲህ አላቸው፥ “መሰናክል ግድ ይመጣል፤
ነገር ግን መሰናክልን ለሚያመጣት ሰው ወዮ
ለት። ፪ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን ከሚያሰና
ክል ይልቅ አህያ የሚፈጭበት የወፍጮ ድን
ጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር ቢሰጥም
በተሻለው ነበር። ፫ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ ወንድ
ምህ አንተን ቢበድል ብቻህን ምከረው፤ ቢጸ
ጸት ግን ይቅር በለው። ፬በየቀኑ ሰባት ጊዜ ቢበ
ድልም ሰባት ጊዜ ከተጸጸተ ይቅር በለው።”

### ስለ ሃይማኖት ኀይል

፭ሐዋርያትም ጌታን፥ “እምነትን ጨም
ርልን” አሉት። ፮ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ
አላቸው፥ “የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት
ብትኖራችሁ ይህችን ሾላ ከሥርሽ ተነቅለሽ በባ
ሕር ውስጥ ተተከዪ ብትሉአት ትታዘዝላችኋ
ለች።”

### ስለ መታዘዝ

፯“አራሽ ወይም ከብት ጠባቂ አገልጋይ
ያለው ከእናንተ ማን ነው? ከእርሻው በተመለሰ
ጊዜ ጌታው ና፥ ፈጥነህ ወደዚህ ውጣና ከእኔ
ጋር በማዕድ ተቀመጥ ይለዋልን? ፰እራቴን አዘ
ጋጅልኝ፥ እስክበላና እስክጠጣ ድረስም ታጥ
ቀህ አሳልፍልኝ፤ ከዚህም በኋላ አንተ ብላ፥
ጠጣም ይለው የለምን? ፱እንግዲህ ጌታው ያዘ
ዘውን ሥራውን ቢሠራ ለዚያ አገልጋይ ምስ
ጋና አለውን? ፲እንዲሁ እናንተም ያዘዝኋችሁን
ሁሉ አድርጋችሁ ‘እኛ ሥራ ፈቶች አገልጋዮች
ነን፤ ለመሥራትም የሚገባንን ሠራን’ በሉ።”

### ዐሥሩን ለምጻሞች እንዳነጻ

፲፩ከዚህ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በሰማ
ርያና በገሊላ መካከል ዐለፈ። ፲፪ወደ አንዲት
መንደርም ሲገባ ለምጽ የያዛቸው ዐሥር ሰዎች
ተቀበሉትና ራቅ ብለው ቆሙ። ፲፫ድምጻቸው
ንም ከፍ አድርገው፥ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥
እዘንልን” አሉ። ፲፬ባያቸውም ጊዜ፥ “ወደ
ካህን ሂዱና ራሳችሁን አስመርምሩ” አላቸው፤
ሲሄዱም ነጹ። ፲፭ከእነርሱም አንዱ እንደ ነጻ
ባየ ጊዜ፥ በታላቅ ቃል እያመሰገነ ተመለሰ።
፲፮በግንባሩም ወድቆ ከጌታችን ከኢየሱስ እግር
በታች ሰገደና አመሰገነው፤ ሰውየውም ሳም
ራዊ ነበር። ፲፯ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እን
ዲህ አለ፤ “የነጹ ዐሥር አልነበሩምን? እንግ

---

፮ በግሪኩ “ይመስክርላቸው” ይላል።

፲፯፥፫ ማቴ. ፲፰፥፲፭።   ፲፯፥፲፬ ዘሌ. ፲፬፥፩-፴፪።

ዲህ ዘጠኙ የት አሉ? [፲፰]ወገኑ ሌላ ከሆነ ከዚህ
ሰው በቀር ለእነዚያ ተመልሶ እግዚአብሔርን
ማመስገን ተሳናቸውን?” [፲፱]እርሱንም፥ “ተነ
ሥና ሂድ፤ እምነትህ አዳነችህ” አለው።

### ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መምጣት
(ማቴ. ፳፬፥፳፫-፳፰፤ ፴፮-፵፩)

[፳]ፈሪሳውያንም “የእግዚአብሔር መንግሥት
መቼ ትመጣለች?” ብለው ጠየቁት፤ እርሱም
መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “የእግዚአብሔር መን
ግሥት በመጠባበቅ አትመጣም። [፳፩]እንኋት፥
በዚህ ናት፤ ወይም እነኋት፥ በዚያ ናት አይሉ
አትም፤ የእግዚአብሔር መንግሥትስ እነኋት፥
በመካከላችሁ ናት።”

[፳፪]ደቀ መዛሙርቱንም እንዲህ አላቸው፥
“ከሰው ልጆች ቀኖች አንዲቱን ታዩ ዘንድ
የምትመኙበት ወራት ይመጣል፤ ነገር ግን አታ
ዩአትም። [፳፫]እነሆ፥ በዚህ ነው፥ ወይም እነሆ፥
በዚያ ነው ቢሉአችሁ አትውጡ፤ አትከተሉአቸ
ውም። [፳፬]መብረቅ ብልጭ ብሎ ከሰማይ ዳርቻ
እስከ ሰማይ ዳርቻ እንደሚያበራ የሰው ልጅ
አመጣጡ እንዲሁ ነውና። [፳፭]ነገር ግን ከዚህ
ሁሉ አስቀድሞ ብዙ መከራን ይቀበላል፤ ይህች
ትውልድም ትንቀዋለች፤ ትፈታተነዋለችም።
[፳፮]በኖኅ ዘመን እንደ ሆነው የሰው ልጅ በሚመ
ጣበት ጊዜ እንዲሁ ይሆናል። [፳፯]ኖኅ ወደ መር
ከብ እስከ ገባበት ቀን ድረስ ሲበሉና ሲጠጡ፥
ሲያገቡና ሲጋቡ ነበረ፤ የጥፋት ውኃም መጥቶ
ሁሉን አንድ አድርጎ አጠፋ። [፳፰]በሎጥ ዘመ
ንም ሲበሉና ሲጠጡ፥ ቤት ሲሠሩና ተክል
ሲተክሉ፥ ሲሸጡና ሲገዙ ነበረ። [፳፱]ሎጥ ከሰ
ዶም በወጣበት ቀን ግን ከሰማይ እሳትና ዲን
ዘነመ፤ ሁሉንም አጠፋ። [፴]የሰው ልጅም በሚ
መጣበት ቀን እንዲሁ ይሆናል፤ አይታወቅ
ምም። [፴፩]ያንጊዜም በሰገነት ላይ ያለ፥ ገንዘ
ቡም በምድር ቤት የሆነበት ሰው ለመውሰድ
አይውረድ፤ በዱር ያለም ወደ ኋላው አይመ
ለስ። [፴፪]የሎጥን ሚስት ዐስቡአት። [፴፫]ነፍሱን
ሊያድናት የሚወድ ይጣላት፤ ስለ እኔ[፩] ነፍ
ሱን የሚጥላትም ያድናታል። [፴፬]እላችኋለሁ፦
ሁለት ሰዎች በአንድ አልጋ ይተኛሉ፤ አንዱን
ይወስዳሉ፤ ሁለተኛውንም ይተዋሉ። [፴፭]ሁለት
ሴቶችም በአንድ ወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱን
ይወስዳሉ፤ ሁለተኛዪቱንም ይተዋሉ። [፴፮]ሁለት
ሰዎች በአንድ እርሻ ላይ ይኖራሉ፤ አንዱን
ይወስዳሉ፤ ሁለተኛውንም ይተዋሉ።” [፴፯]እነ
ርሱም መልሰው፥ “አቤቱ፥ ወዴት ነው?”
አሉት፤ እርሱም፥ “ገደላ በአለበት አሞሮች
በዚያ ይሰበሰባሉ” አላቸው።

## ምዕራፍ ፲፰

### ያለ መሰልቸት ስለ መጸለይ ምሳሌ

[፩]ዘወትር እንዲጸልዩ፥ እንዳይሰለቹም በምሳሌ
ነገራቸው። [፪]እንዲህም አላቸው፥ “በአንዲት
ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ፥ ሰውንም
የማያፍር አንድ ዳኛ ነበር። [፫]በዚያችም ከተማ
አንዲት መበለት ነበረች፤ ዕለት ዕለትም[፪] ወደ
እርሱ እየመጣች ከባለጋራዬ ፍረድልኝ ትለው
ነበር። [፬]እንቢ ብሎም አዘገያት። ከዚህም በኋላ
በልቡ ዐስቦ እንዲህ አለ፦ ‘ምንም እግዚአብ
ሔርን ባልፈራ፥ ሰውንም ባላፍር [፭]ይህቺ ሴት
እንዳትዘበዝበኝ፥ ዘወትርም እየመጣች እንዳታ
ታክተኝ እፈርድላታለሁ’።” [፮]ጌታችንም እን
ዲህ አላቸው፥ “ዐመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ።
[፯]እንግዲህ እግዚአብሔር በመዓልትና በሌሊት
ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለወዳጆቹ አይፈርድምን?
ወይስ ቸል ይላቸዋልን? [፰]እላችኋለሁ ፈጥኖ
ይፈርድላቸዋል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ
ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆን?”

### ስለ ፈሪሳዊዉና ስለ ቀራጩ

[፱]ራሳቸውን ለሚያመጻድቁና ባልንጀራቸውን
ለሚንቁ እንዲህ ብሎ መሰለላቸው። [፲]“ሁለት
ሰዎች ሊጸልዩ ወደ ቤተ መቅደስ ወጡ፤ አንዱ
ፈሪሳዊ፥ ሁለተኛውም ቀራጭ ነበር። [፲፩]ፈሪሳዊ
ውም ቆመና እንዲህ ብሎ ጸለየ፦ ‘አቤቱ እንደ
ሌሎች ሰዎች፥ እንደ ቀማኞችና እንደ ዐመፀ
ኞች፥ እንደ አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ
ቀራጭ ያላደረገኸኝ[፫] አመሰግንሃለሁ። [፲፪]እኔ

---

፩ “ስለ እኔ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ “ዕለት ዕለትም” የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።

፫ በግሪኩ “ስላልሆንሁ” ይላል።

፲፯፥፳፯ ዘፍ. ፯፥፮-፳፫።   ፲፯፥፳፱ ዘፍ. ፲፱፥፲፮-፳፬።   ፲፯፥፴፫-፴፱ ዘፍ. ፲፰፥፰-፲፱-፳፮።

፲፯፥፴፩ ማቴ. ፳፬፥፲፯-፲፰፤ ማር. ፲፫፥፲፭-፲፮።   ፲፯፥፴፪ ዘፍ. ፲፱፥፳፮።

፲፯፥፴፫ ማቴ. ፲፥፴፱፤ ፲፮፥፳፭፤ ማር. ፰፥፴፭፤ ሉቃ. ፱፥፳፬፤ ዮሐ. ፲፪፥፳፭።

በየሳምንቱ ሁለት ቀን እጾማለሁ፤ ከማገኘውም
ሁሉ ከዐሥር አንድ እሰጣለሁ።’ ፲፫ቀራጩ ግን
ራቅ ብሎ ቆመ፤ ዐይኖቹንም ወደ ላይ ወደ
ሰማይ ሊያነሣ አልወደደም፤ ደረቱንም እየ
መታ፦ ‘አቤቱ፥ እኔን ኀጢአተኛውን ይቅር
በለኝ’ አለ። ፲፬እላችኋለሁ፥ ከዚያ ይልቅ ይህ
ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ ከፍ
የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፤ ራሱንም የሚያ
ዋርድ ይከብራልና።”

### ጌታችን ሕፃናትን ስለ መባረኩ
(ማቴ. ፲፱፥፲፫-፲፭፤ ማር. ፲፥፲፫-፲፮)

፲፭ይባርካቸውም ዘንድ ሕፃናትን ወደ እርሱ
አመጡአቸው፤ ደቀ መዛሙርቱም አይተው
ገሠጹአቸው። ፲፮ጌታችን ኢየሱስም ጠራ
ቸው፤[፫] እንዲህም አላቸው፥ “ሕፃናትን ወደ
እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉአቸው፥ አትከልክሉአ
ቸውም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነ
ዚህ ላሉት ናትና። ፲፯እውነት እላችኋለሁ፥ የእ
ግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃናት ያልተ
ቀበላት አይገባባትም።”

### ስለ ሕይወት ጥያቄ
(ማቴ. ፲፱፥፲፮-፴፤ ማር. ፲፥፲፯-፴፩)

፲፰አንድ አለቃም፥ “ቸር መምህር፥ ምን
ሥራ ሠርቼ የዘለዓለም ሕይወትን እወርሳ
ለሁ?” አለው። ፲፱ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ
አለው፥ “ለምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእ
ግዚአብሔር በቀር ቸር የለም። ፳ትእዛዛቱን
አንተ ራስህ ታውቃለህ፤ ‘አትግደል፤ አታመ
ንዝር፤ አትስረቅ፤ በሐሰት አትመስክር፤ አባት
ህንና እናትህንም አክብር።’ ፳፩እርሱም፦ ‘ይህ
ንስ ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሬ እስከ ዛሬ ጠብቄአ
ለሁ’።” አለው። ፳፪ጌታችን ኢየሱስም ይህን
ሰምቶ እንዲህ አለው፥ “አንዲት ቀርታሃለች፤
ሂድና ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለነዳያን ስጥ፤ በሰ
ማይም መዝገብ ታገኛለህ፤ መጥተህም ተከ
ተለኝ።” ፳፫እርሱ ግን ይህን ሰምቶ በጣም
አዘነ፤ እርሱ እጅግ ባለጸጋ ነበርና። ፳፬ጌታ
ችን ኢየሱስም እጅግ ሲያዝን አይቶ እንዲህ
አለ፥ “ገንዘብ ላላቸው ሰዎች ወደ እግዚአብ
ሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ነው!
፳፭ባለጸጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚ
ገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ሊያልፍ ይቀ
ላል።” ፳፮የሰሙትም፥ “እንግዲህ ማን ሊድን
ይችላል?” አሉ። ፳፯እርሱ ግን “በሰው ዘንድ
የማይቻለው በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል”
አላቸው።

### የጴጥሮስ ጥያቄ

፳፰ጴጥሮስም፥ “እነሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን
ተከትለንሃል፤ እንግዲህ ምን እናገኛለን?”[፬]
አለው። ፳፱እርሱም እንዲህ አላቸው፥ “እው
ነት እላችኋለሁ፥ ቤቱንና ዘመዶቹን፥ ወንድ
ሞቹንና ሚስቱን፥ ልጆቹንም ስለ እግዚአብ
ሔር መንግሥት የሚተው፥ ፴በዚህ ዓለም መቶ
እጥፍ[፭] ዋጋ፥ በሚመጣውም ዓለም የዘለዓለም
ሕይወትን የማይቀበል ማንም የለም።”

### ስለ ሕማሙና ስለ ሞቱ
(ማቴ. ፳፥፲፯-፲፱፤ ማር. ፲፥፴፪-፴፬)

፴፩ዐሥራ ሁለቱንም ወሰዳቸው፤ እንዲህም
አላቸው፥ “እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣ
ለን፤ በነቢያትም የተጻፈው ሁሉ በሰው ልጅ
ላይ ይፈጸማል። ፴፪ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰ
ጡታል፤ ይዘብቱበታልም፤ ይሰድቡታልም፤
ይተፉበታልም። ፴፫ይገርፉታል፤ ይገድሉታ
ልም፤ በሦስተኛዩቱም ቀን ይነሣል።” ፴፬እነ
ርሱ ግን፤ ከተናገራቸው ያስተዋሉት የለም፤
ይህ ነገር ከእነርሱ የተሰወረ ነበርና፤ የተናገረ
ውንም አያውቁም ነበርና።

### በኢያሪኮ ስለ ነበረው ዕውር
(ማቴ. ፳፥፳፱-፴፬፤ ማር. ፲፥፵፮)

፴፭ከዚህም በኋላ ኢያሪኮ በደረሱ ጊዜ አንድ
ዕውር በጎዳና ተቀምጦ ይለምን ነበር። ፴፮የሚ
ያልፈውንም ሰው ድምፅ ሰምቶ፥ “ይህ የም
ሰማው ምንድን ነው?” አለ። ፴፯እነርሱም፥
“የናዝሬቱ ኢየሱስ ያልፋል” ብለው ነገሩት።
፴፰ድምፁንም ከፍ አድርጎ፥ “የዳዊት ልጅ ኢየ
ሱስ ሆይ፥ ማረኝ” አለ። ፴፱የሚመሩትም ዝም
እንዲል ገሠጹት፤ እርሱ ግን በጣም ጮኸ፥
“የዳዊት ልጅ ሆይ፥ ማረኝ” አለ። ፵ጌታችን
ኢየሱስም ቆመና ወደ እርሱ እንዲያመጡት

---

[፫] በግሪኩ “ሕፃናትን ጠርቶ አለ” ይላል።

[፬] “እንግዲህ ምን እናንገኛለን” የሚለውን ግሪኩ እና አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ አይጽፍም።

[፭] በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ “ብዙ ዕጥፍ” ይላል።

፲፰፥፲፬ ማቴ. ፳፫፥፲፪፤ ሉቃ. ፲፬፥፲፩። ፲፰፥፳ ዘፀ. ፳፥፲፪-፲፮፤ ዘዳ. ፭፥፲፮-፳።

አዘዘ። ፵፩ወደ እርሱም በደረሰ ጊዜ፥ “ምን
ላደርግልህ ትወዳለህ?” ብሎ ጠየቀው፤ እር
ሱም፥ “ጌታ ሆይ፥ ዐይኖቼ እንዲያዩ ነው”
አለው። ፵፪ጌታችን ኢየሱስም፥ “እይ፤ እምነ
ትህ አዳነችህ” አለው። ፵፫በዚያን ጊዜም አየ፤
እግዚአብሔርንም አመሰገነ፤ ተከተለውም፤
ሕዝቡም ሁሉ አይተው እግዚአብሔርን አመ
ሰገኑት።

## ምዕራፍ ፲፱

### ስለ ቀራጩ ዘኬዎስ

፩ጌታችን ኢየሱስም ወደ ኢያሪኮ ገብቶ
በዚያ ያልፍ ነበር። ፪እነሆ፥ የቀራጮች አለቃ
ስሙ ዘኬዎስ የተባለ አንድ ሰው ነበር፤ እር
ሱም ባለጸጋ ነበር። ፫ጌታችን ኢየሱስንም
ያየው ዘንድ፥ ማን እንደ ሆነም ያውቅ ዘንድ
ይሻ ነበር፤ የሰው ብዛትም ይከለክለው ነበር፤
ቁመቱ አጭር ነበርና። ፬ወደ ፊቱም ሮጠ፤
ያየው ዘንድም በሾላ ላይ ወጣ፤ በዚያች መን
ገድ ያልፍ ዘንድ አለውና። ፭ጌታችን ኢየሱ
ስም ወደዚያ በደረሰ ጊዜ አሻቅቦ አየውና፥
“ዘኬዎስ ሆይ፥ ፈጥነህ ውረድ፤ ዛሬ በቤ
ትህ እውል ዘንድ አለኝና” አለው። ፮ፈጥኖም
ወረደ፤ ደስ እያለውም ወደ ቤቱ ይዞት ገባ።
፯ሁሉም አይተው “ወደ ኀጢአተኛ ሰው ቤት
ሊውል ገባ” ብለው አንጐራጐሩ። ፰ዘኬዎስም
ቆመና ጌታችንን እንዲህ አለው፥ “ጌታዬ
ሆይ፥ አሁን የገንዘቤን እኩሌታ ለነዳያን እሰ
ጣለሁ፤ የበደልሁትም ቢኖር ስለ አንድ ፋንታ
አራት እጥፍ እከፍለዋለሁ።” ፱ጌታችን ኢየሱ
ስም እንዲህ አለው፥ “ዛሬ ለዚህ ቤት ሕይ
ወት ሆነ፤ እርሱ የአብርሃም ልጅ ነውና።
፲የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን
መጥቶአልና።”

### ዐሥር ምናን ስለ ተቀበሉት ሰዎች ምሳሌ
(ማቴ. ፳፭፥፲፬-፴)

፲፩ይህንም ሲሰሙ፤ ምሳሌ መስሎ ነገራቸው፤
ወደ ኢየሩሳሌም ቀርቦ ነበርና፤ እነርሱም የእግዚ
አብሔር መንግሥት ወዲያውኑ የምትገለጥ መስ
ሎአቸው ነበርና። ፲፪እንዲህም አለ፥ “አንድ የከ
በረ ሰው መንግሥት ይዞ ሊመለስ ወደ ሩቅ ሀገር
ሄደ። ፲፫ዐሥሩን አገልጋዮቹንም ጠርቶ ዐሥር
ምናን ሰጣቸውና፡- እንግዲህ እስክመለስ ድረስ
ነግዱ አላቸው። ፲፬የሀገሩ ሰዎች ግን ይጠሉት ነበ
ርና፥ ይህ በእኛ ላይ ሊነግሥ አንሻም ብለው አከ
ታትለው መልእክተኞችን ላኩ። ፲፭ከዚህም በኋላ፤
መንግሥትን ይዞ በተመለሰ ጊዜ እንደ አተረፉ
ያውቅ ዘንድ ምናን የሰጣቸውን ብላቴኖቹን እን
ዲያመጡአቸው አዘዘ። ፲፮አንደኛውም መጥቶ፡-
አቤቱ፥ ምናንህ ዐሥር ነበር፤ እነሆ ዐሥር ምናን
አትርፌአለሁ አለው። ፲፯ጌታውም፡- መልካም፥
አንተ በጎ አገልጋይ በጥቂት የታመንህ ስለሆንህ
በብዙ ላይ እሾምሃለሁ፤፩ በዐሥሩ ከተሞች ላይ
ተሾም አለው። ፲፰ሁለተኛውም መጥቶ፡- አቤቱ፥
ምናንህ አምስት ነበር፤፪ አምስት አትርፌአለሁ
አለው። ፲፱እርሱንም፡- አንተም በአምስት ከተ
ሞች ተሾም አለው። ፳ሦስተኛውም መጥቶ እን
ዲህ አለው፡- አቤቱ፥ በእኔ ዘንድ የነበረቺው ምና
ንህ እነኋት፤ በጨርቅ ጠቅልዬ አኑሬአት ነበር።
፳፩አንተ ያላኖርኸውን የምትወስድ፥ ያልዘራኸ
ውን የምታጭድ፥ ያልበተንኸውንም የምትሰበ
ስብ፫ ጨካኝ ሰው እንደ ሆንህ ስለማውቅህ ፈር
ቼሃለሁና። ፳፪ጌታውም እንዲህ አለው፡- አንተ
ክፉ ሰነፍ አገልጋይ፥ እኔ ያላስቀመጥሁትን የም
ወስድ፥ ያልዘራሁትን የማጭድ፥ ያልበተንሁት
ንም የምሰበስብ ጨካኝ ሰው እንደ ሆንሁ ታውቃ
ለህን? እንደ ቃልህ እፈርድብሃለሁ። ፳፫ለምን ገን
ዘቤን ወደ ለዋጮች አላስገባህም? እኔም መጥቼ
ከትርፉ ጋር በወሰድሁት ነበር። ፳፬ከዚያ የቆ
ሙትንም፡- ይህን ምናን ከእርሱ ተቀብላችሁ
ዐሥር ምናን ላለው ስጡት አላቸው። ፳፭እነር
ሱም አቤቱ፥ ዐሥር ምናን ያለው አይደለምን?
አሉት። ፳፮እርሱም እንዲህ አላቸው፡- ላለው ሁሉ
ይሰጡታል፤ ይጨምሩለታልም፤ የሌለውን ግን
ያን ያለውንም ቢሆን ይወስዱበታል። ፳፯ነገር ግን
እነዚያን ልነግሥባቸው ያልወደዱትን ጠላቶቼን
ወደዚህ አምጡና በፊቴ ውጉአቸው።”

### ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መግባቱ
(ማቴ. ፳፩፥፩-፲፩፤ ዮሐ. ፲፪፥፲፪-፲፱)

፳፰ይህንም ተናግሮ ወደ ፊት ሄደ፤ ወደ
ኢየሩሳሌምም ወጣ። ፳፱ደብረ ዘይት ወደ

---

፩ “በብዙ ላይ እሾምሃለሁ” የሚለው በግሪኩ የለም።
፪ “ምናንህ አምስት ነበር” የሚለው በግሪኩ የለም።
፫ “ያልበተንኸውን የምትሰበስብ” የሚለው በግሪኩ የለም።
፲፱፥፲ ማቴ. ፲፰፥፲፩። ፲፱፥፲፩-፳፯ ማቴ. ፳፭፥፲፬-፴። ፲፱፥፳፮ ማቴ. ፲፫፥፲፪፤ ማር. ፬፥፳፭፤ ሉቃ. ፰፥፲፰።

ሚባል ተራራ አጠገብ ወዳሉት ወደ ቤተ
ፋጌና ወደ ቢታንያ በቀረበ ጊዜ፥ ከደቀ
መዛሙርቱ ሁለቱን ላከ። ፴እንዲህም አላ
ቸው፥ "በፊታችሁ ወደ አለችው መንደር
ሂዱ፤ ገብታችሁም ሰው ያልተቀመጠበት
የታሰረ ውርንጫ ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁም
አምጡልኝ። ፴፩ለምን ትፈቱታላችሁ? የሚላ
ችሁ ቢኖር ጌታው ይሻዋል በሉ።" ፴፪የተላ
ኩትም ሄደው እንደ አላቸው አገኙ። ፴፫ውር
ንጫውንም ሲፈቱ ባለቤቶቹ "ውርንጫውን
ለምን ትፈቱታላችሁ?" አሉአቸው። ፴፬እነ
ርሱም "ጌታው ይሻዋል" አሉ። ፴፭ይዘ
ውም ወደ ጌታችን ኢየሱስ ወሰዱት፤ በው
ርንጫው ላይም ልብሳቸውን ጭነው ጌታ
ችን ኢየሱስን በዚያ ላይ አስቀመጡት።
፴፮ሲሄዱም በመንገድ ልብሳቸውን አነጠፉ።
፴፯ወደ ደብረ ዘይት ዐቀበት መውረጃም
በደረሱ ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ በሙሉ ስለ
አዩት ኀይል ሁሉ ደስ ይላቸውና እግዚአ
ብሔርን በታላቅ ቃል ያመሰግኑት ዘንድ
ጀመሩ። ፴፰እንዲህ እያሉ፥ "በእግዚአብሔር
ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው፤ የእስራኤል
ንጉሥ ቡሩክ ነው፤[፩] ሰላም በምድር፥ በአ
ርያምም ክብር ይሁን።" ፴፱ከፈሪሳውያንም
በሕዝቡ መካከል፥ "መምህር ሆይ፥ ደቀ
መዛሙርትህን ገሥጻቸው" ያሉት ነበሩ።
፵እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ "እነዚህ
ዝም ቢሉ እኒህ ድንጋዮች ይጮኹሉ።"

## ስለ ኢየሩሳሌም መጥፋት

፵፩በደረሰ ጊዜም ከተማዪቱን አይቶ አለ
ቀሰላት። ፵፪እንዲህም አላት፥ "አንቺስ ብታ
ውቂ ሰላምሽ ዛሬ ነበረ፤ ከእንግዲህ ወዲህ
ግን ከዐይኖችሽ ተሰወረ። ፵፫ጠላቶችሽ አን
ቺን የሚከቡበት ቀን ይመጣል፤ ይከትሙብ
ሻል፤ ያስጨንቁሻልም፤ በአራቱ ማዕዘንም
ከብበው ይይዙሻል። ፵፬አንቺን ይጥሉሻል፤
ልጆችሽንም ከአንቺ ጋር ይጥሉአቸዋል፤
ድንጋይንም በደንጋይ ላይ አይተዉልሽም፤
የይቅርታሽን ዘመን አላወቅሽምና።"

## ጌታችን ገበያተኞቹን ከቤተ መቅደስ ስለ ማስወጣቱ

(ማቴ. ፳፩፥፲፪-፲፯፤ ማር. ፲፩፥፲፭-፲፱)

፵፭ወደ ቤተ መቅደስም ገብቶ በዚያ የሚሸ
ጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አስወጣ፤ የለዋጮ
ችንም መደርደሪያ፥ የርግብ ሻጮችንም ወን
በር ገለበጠ።[፪] ፵፮"ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል
የሚል ጽሑፍ አለ፤ እናንተ ግን የሌቦችና የቀ
ማኞች ዋሻ አደረጋችሁት" አላቸው። ፵፯ዘወት
ርም በመቅደስ ያስተምር ነበር፤ የካህናት አለ
ቆች፥ ጻፎችና የሕዝብ ታላላቆችም ሊገድሉት
ይሹ ነበር። ፵፰ነገር ግን የሚያደርጉትን አጡ፤
ሕዝቡ ሁሉ ትምህርቱን በመስማት ይመሰጡ
ነበርና።

# ምዕራፍ ፳

## ከሊቃነ ካህናት የቀረበ ጥያቄ

(ማቴ. ፳፩፥፳፫-፳፯፤ ማር. ፲፩፥፳፯-፴፫)

፩ከዚህም በኋላ በአንድ ቀን ሕዝቡን በመ
ቅደስ ሲያስተምራቸው፥ ወንጌልንም ሲነግ
ራቸው፥ የካህናት አለቆች፥ ጻፎችና ሽማግ
ሌዎች ተነሡበት። ፪"ይህን በማን ሥልጣን
ታደርጋለህ? ይህንስ እንድታደርግ ማን ፈቀ
ደልህ? እስኪ ንገረን" አሉት። ፫እርሱም
መልሶ፥ "እኔም አንዲት ነገርን እጠይቃ
ችኋለሁ፤ ንገሩኝ፤ ፬የዮሐንስ ጥምቀት ከወ
ዴት ናት? ከሰማይ ናትን? ወይስ ከሰው?"
አላቸው። ፭እርስ በርሳቸውም እንዲህ ተባ
ባሉ፤ "ከሰማይ ነው ብንለው ለምን አላመና
ችሁትም? ይለናል። ፮ከሰው ነው ብንለውም
ሕዝቡ ሁሉ በድንጋይ ይወግሩናል፤ ሁሉም
ዮሐንስ ነቢይ እንደ ሆነ አምነውበታልና።
፯ከወዴት እንደ ሆነች አናውቅም" ብለው
መለሱለት። ፰ጌታችን ኢየሱስም፥ "እኔም
ይህን በማን ሥልጣን እንደማደርግ አልነግራ
ችሁም" አላቸው።

## ስለ ወይን ጠባቂዎች

(ማቴ. ፳፩፥፴፫-፵፮፤ ማር. ፲፪፥፩-፲፪)

፱ለሕዝቡም ይህን ምሳሌ ይመስልላቸው
ጀመረ፤ እንዲህም አላቸው፥ "አንድ ሰው

---

[፩] "የእስራኤል ንጉሥ ቡሩክ ነው" የሚለው በግሪኩ የለም።

[፪] "የለዋጮችንም መደርደሪያ የርግብ ሻጮንም ወንበር ገለበጠ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፱፥፴፰ መዝ. ፻፲፰፥፳፮። ፲፱፥፵፮ ኢሳ. ፶፮፥፯፤ ኤር. ፯፥፲፩። ፲፱፥፵፯ ሉቃ. ፳፩፥፴፯። ፳፥፱ ኢሳ. ፭፥፩።

ወይን ተከለ፤ መጭመቂያም አስቈፈረ፤ ግን
ብም ሠራለት፤[፩] ለገባሮችም ሰጥቶ ወደ ሩቅ
ሀገር ሄደ፤ ሳይመለስም ዘገየ። ፲የመከሩ ወራት
በሆን ጊዜም ወደ ገባሮቹ፥ ከወይኑ ፍሬ ይልኩ
ለት ዘንድ አገልጋዩን ላከ፤ ገባሮቹ ግን አገልጋ
ዩን ደብድበው ባዶ እጁን ሰደዱት። ፲፩ዳግመ
ኛም ሌላውን አገልጋዩን ላከ፤ እርሱንም ደብድ
በውና አዋርደው ባዶ እጁን ሰደዱት። ፲፪ደግሞ
ሦስተኛውን አገልጋዩን ላከ፤ እርሱንም አቍ
ስለው ሰደዱት። ፲፫የወይኑ ባለቤትም፦ እንግ
ዲህ ምን ላድርግ? ምናልባት እርሱን እንኳ
አይተው ያፍሩ እንደ ሆነ የምወደውን ልጄን
ልላክ ብሎ ላከው። ፲፬ገባሮቹም ባዩት ጊዜ
ወራሹ ይህ ነው፤ ኑ፥ እንግደለውና ርስቱን
እንውሰድ ብለው ተማከሩ። ፲፭ከወይኑ ቦታም
ወደ ውጭ አውጥተው ገደሉት። ፲፮የወይኑ ባለ
ቤት በመጣ ጊዜ እንግዲህ ምን ያደርጋቸዋል?
ይመጣል፤ እነዚያንም ገባሮች ይገድላቸዋል፤
ወይኑንም ለሌሎች ገባሮች ይሰጣል፤” ቃሉ
ንም ሰምተው፥ “አይሆንም፤ እንዲህ አይደ
ረግም” አሉ። ፲፯ጌታችን ኢየሱስም ተመለከ
ተና እንዲህ አላቸው፤ “ግንበኞች የናቁአት
ድንጋይ እርስዋ የማዕዘን ራስ ሆነች፥ የሚለው
ጽሑፍ ምንድነው? ፲፰በዚያች ድንጋይ ላይ የወ
ደቀ ሁሉ ይቀጠቀጣል፤ እርስዋም የወደቀችበ
ትን ታደቅቀዋለች።” ፲፱ያን ጊዜም የካህናት
አለቆችና ጻፎች ሊይዙት ወደዱ፤ ይህን ስለ
እነርሱ እንደ መሰለ ዐውቀዋልና፤ ነገር ግን
ሕዝቡን ፈሩአቸው።

### ለቄሣር ግብር ስለ መስጠት

(ማቴ. ፳፪፥፲፭-፳፪፤ ማር. ፲፪፥፲፫-፲፯)

፳ከእነርሱም ተለይተው ከሄዱ በኋላ፥ የሚ
ጠባበቁትን አዘጋጁለት፤ በአነጋገሩም ያስቱት
ዘንድ ወደ መኳንንትና ወደ መሳፍንት አሳል
ፈው ሊሰጡት ራሳቸውን የሚያመጻድቁ ሰላ
ዮችን ወደ እርሱ ላኩ። ፳፩እነርሱም እንዲህ
ብለው ጠየቁት፥ “መምህር ሆይ፥ አንተ እው
ነት እንደምትናገርና እንደምታስተምር፥ ፊት
አይተህም እንደማታዳላ፥ የእግዚአብሔርንም
መንገድ በቀጥታ እንደምታስተምር እናውቃለን።
፳፪ለቄሣር ግብር መስጠት ይገባል? ወይስ አይ
ገባም?” ፳፫ተንኰላቸውንም ዐውቆ፥ “ለምን
ትፈትኑኛላችሁ? ገንዘቡን አሳዩኝ” አላቸው።
፳፬አምጥተውም አሳዩት፤ “መልኩ፥ ጽሕፈ
ቱስ የማነው?” አላቸው፤ እነርሱም፥ “የቄ
ሣር ነው” ብለው መለሱለት። ፳፭እርሱም፥
“እንኪያስ የቄሣርን ለቄሣር፥ የእግዚአብሔር
ንም ለእግዚአብሔር ስጡ” አላቸው። ፳፮በሕዝ
ቡም ሁሉ ፊት በአነጋገሩ ማሳሳት ተሳናቸው፤
መልሱንም አድንቀው ዝም አሉ።

### ስለ ትንሣኤ ሙታን

(ማቴ. ፳፪፥፳፫-፴፫፤ ማር. ፲፪፥፲፰-፳፯)

፳፯“ሙታን አይነሡም” ከሚሉ ከሰዱቃውያ
ንም አንዳንድ ሰዎች ወደ እርሱ መጡ። ፳፰እነ
ርሱም እንዲህ ብለው ጠየቁት፥ “መምህር
ሆይ፥ ሙሴ፦ ‘ወንድሙ ልጅ ሳይወልድ ሚስ
ቱን ትቶ የሞተበት ሰው ቢኖር ወንድሙ ሚስ
ቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ’ ሲል ጽፎ
ልናል። ፳፱እንግዲህ ከእኛ ዘንድ ሰባት ወንድማ
ማቾች ነበሩ፤ ታላቁ ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይ
ወልድ ሞተ። ፴እንደዚሁም ሁለተኛው አገባት፤
እርሱም ልጅ ሳይወልድ ሞተ፤ ፴፩ሦስተኛውም
አገባት፤ እንዲሁም ሰባቱ ሁሉ አገቡአት፤ ልጅ
ሳይወልዱም ሞቱ። ፴፪ከሁሉም በኋላ ያቺ ሴት
ሞተች። ፴፫እንግዲህ ሙታን በሚነሡበት ጊዜ
ከእነርሱ ለማንኛው ሚስት ትሆናለች? ሰባቱም
ሁሉ አግብተዋት ነበርና።” ፴፬ጌታችን ኢየሱ
ስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “የዚህ ዓለም
ልጆች ያገባሉ፥ ይጋባሉም፤ ይወልዳሉ፥ ይዋለ
ዳሉም።[፪] ፴፭ያን ዓለም በሙታን ትንሣኤ ሊወ
ርሱ የሚገባቸው እነዚያ ግን አያገቡም፤ አይ
ጋቡም። ፴፮እንግዲህ ወዲህ ሞት የለባቸውም፤
እንደ እግዚአብሔር መላእክት ናቸው እንጂ፤
የትንሣኤ ልጆችም ስለሆኑ የእግዚአብሔር
ልጆች ይሆናሉ። ፴፯ሙታን እንደሚነሡስ እግ
ዚአብሔር፦ ‘እኔ የአብርሃም አምላክ፥ የይስ
ሐቅም አምላክ፥ የያዕቆብም አምላክ ነኝ’ ብሎ
በቍጥቋጦው ዘንድ እንደ አነጋገረው ሙሴ ተና
ግሮአል። ፴፰እንኪያስ የሕያዋን አምላክ እንጂ
የሙታን አምላክ አይደለም፤ ሁሉም በእርሱ
ዘንድ ሕያዋን ናቸውና።” ፴፱ከጻፎችም ወገን
የሆኑ ሰዎች፥ “መምህር ሆይ፥ መልካም ብለ
ሃል” ብለው መለሱ። ፵ከዚያ ወዲህ ግን ሊጠ
ይቀው የደፈረ ማንም የለም።

---

፩ “መጭመቂያም አስቈፈረ ግንብም ሠራለት” የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ “… ይወልዳሉ ይዋለዳሉም …” የሚለው በግሪኩ የለም።

፳፥፲፯ መዝ. ፻፲፰፥፳፪። ፳፥፳፯ ሐ.ሥ. ፳፫፥፰። ፳፥፳፰ ዘዳ. ፳፭፥፭። ፳፥፴፯ ዘፀ. ፫፥፮።

### ስለ መሲሕ የቀረበ ጥያቄ

(ማቴ. ፳፪፥፵፩-፵፮፤ ማር. ፲፪፥፴፭-፴፯)

፵፩እንዲህም አላቸው፥ “ክርስቶስን እንዴት
የዳዊት ልጅ ይሉታል? ፵፪እርሱ ራሱ ዳዊት
በመዝሙር መጽሐፍ ‘ጌታ ጌታዬን በቀኜ ተቀ
መጥ፥ ፵፫ጠላቶችህን ከእግርህ ጫማ በታች
እስከ አደርጋቸው ድረስ’ ብሏል። ፵፬እንግዲህ
እርሱ ራሱ ዳዊት ‘ጌታዬ’ ያለው እንዴት ልጁ
ይሆናል?”

### ደቀ መዛሙርቱን ስለ ማስጠንቀቁ

(ማቴ. ፳፫፥፩-፴፮፤ ማር. ፲፪፥፴፰-፵)

፵፭ሕዝቡም ሲሰሙ ደቀ መዛሙርቱን እን
ዲህ አላቸው። ፵፮“ልብሳቸውን አንዘርፍፈው
ወዲያ ወዲህ ማለትን ከሚሹ፥ በገበያ እጅ
መነሣትንና በአደባባይ ፊት ለፊት፥ በማዕድም
ጊዜ በከበሬታ መቀመጫ መቀመጥን ከሚወዱ
ጸፎች ተጠበቁ። ፵፯የመበለቶችን ገንዘብ የሚ
በሉ፥ ለምክንያት ጸሎትንም የሚያስረዝሙ እነ
ዚህ ታላቅ ፍርድን ይቀበላሉ።”

## ምዕራፍ ፳፩

### ሁለት መሐለቅ ስለ አገባችው ድሃ ሴት

(ማር. ፲፪፥፵፩-፵፬)

፩በሙዳየ ምጽዋቱ መባቸውን የሚያገቡ ባለ
ጠጎችን አየ። ፪አንዲት ድሃ መበለትም ሁለት
መሐለቅ ስታስገባ አየ። ፫እንዲህም አላቸው፥
“እውነት እላችኋለሁ፥ ይህቺ ድሃ መበለት
ከሁሉ ይልቅ አብዝታ ለእግዚአብሔር መባ
አገባች። ፬እነዚህ ሁሉ ከተረፋቸው ለእግዚአብ
ሔር መባ አግብተዋልና፤ ይህቺ ግን ከድህነቷ
ያላትን ጥሪቷን ሁሉ አገባች።”

### ስለ ኢየሩሳሌምና ስለ ቤተ መቅደስ መፍረስ

(ማቴ. ፳፬፥፩-፪፤ ማር. ፲፫፥፩-፪)

፭ስለ ቤተ መቅደስም ድንጋዩ ያማረ ነው፥
አሠራሩም ያጌጠ ነው የሚሉት ነበሩ። ፮እን
ዲህም አላቸው፥ “ይህን ታያላችሁን? በእ
ዚህ ቦታ ድንጋይ በድንጋይ ላይ የማይተው
በትና ሳይፈርስ የማይቀርበት ዘመን ይመ
ጣል።” ፯እነርሱም፥ “መምህር ሆይ፥ ይህ
መቼ ይደረጋል? ይህስ የሚሆንበት ጊዜው፥
ምልክቱስ ምንድን ነው?” ብለው ጠየቁት።
፰እርሱም እንዲህ አላቸው፥ “ብዙዎች እኔ
ክርስቶስ ነኝ፤ ጊዜውም ደርሶአል እያሉ
በስሜ ይመጣሉና እንዳያስቱአችሁ ተጠን
ቀቁ፤ እነርሱንም ተከትላችሁ አትሂዱ።
፱ጦርነትንና ጠብን፥ ክርክርንም በሰማችሁ
ጊዜ አትደንግጡ፤ አስቀድሞ ይህ ይሆን
ዘንድ ግድ ነውና፤ ነገር ግን ወዲያው የሚ
ፈጸም አይደለም።”
፲እንዲህም አላቸው፥ “ሕዝብ በሕዝብ
ላይ፥ ነገሥታትም በነገሥታት ላይ ይነሣሉ።
፲፩በየሀገሩ ታላቅ የምድር መነዋወጥና ራብ፥
በሰውም ላይ በሽታና ፍርሀት ይመጣል፤
በሰማይም ታላቅ ምልክት ይሆናል። ፲፪ከዚ
ህም ሁሉ አስቀድሞ ይይዙአችኋል፤ ወደ
አደባባዮችም ይወስዱአችኋል፤ ያሳድዱአች
ኋል፤ ያስሩአችኋል፤ ስለ ስሜም ወደ ነገ
ሥታትና ወደ መሳፍንት ይወስዱአችኋል።
፲፫ይህም በእነርሱ ላይ ምስክር ይሆንባቸ
ዋል። ፲፬ዕወቁ፤ የምትናገሩትንም በልባችሁ
አታስቡ። ፲፭በእናንተ ላይ የሚነሡ ሊመልሱ
ላችሁና ሊከራከሯችሁ እንዳይችሉ እኔ አፍ
ንና ጥበብን እሰጣችኋለሁ። ፲፮ወላጆቻችሁና
ወንድሞቻችሁ፥ ወዳጆቻችሁና ባልንጀሮቻ
ችሁ አሳልፈው ይሰጡአችኋል። ፲፯ሁሉም
ስለ ስሜ ይጠሉአችኋል፤ ይገድሉአችኋልም።
፲፰ነገር ግን ከራስ ጠጕራችሁ አንዲቱ እንኳ
አትጠፋም። ፲፱በትዕግሥታችሁም ነፍሳችሁን
ገንዘብ ታደርጓታላችሁ።

### ስለ ኢየሩሳሌም ጥፋት መድረስ

(ማቴ. ፳፬፥፲፮-፳፩፤ ማር. ፲፫፥፲፬-፲፱)

፳“ኢየሩሳሌምን ጭፍሮች ከብበዋት ባያ
ችሁ ጊዜ ጥፋቷ እንደ ደረሰ ዕወቁ። ፳፩ያን
ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራራ ይሽሹ፤ በመ
ካከልዋ ያሉም ከእርስዋ ይውጡ፤ በአው
ራጃዎችዋ ያሉም ወደ እርስዋ አይግቡ።
፳፪በእርስዋ ላይ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም
ዘንድ እርስዋን የሚበቀሉበት ጊዜዋ ነውና።
፳፫ነገር ግን በዚያ ወራት ለፀነሱና ለሚያ
ጠቡ ወዮላቸው፤ በምድር ላይ ጽኑ መከራ፥
በዚህም ሕዝብ ላይ መቅሠፍት ይሆናልና።
፳፬በሰይፍ ስለት ይወድቃሉ፤ በአሕዛብም
ሁሉ ይማረካሉ፤ የአሕዛብ ጊዜያቸው እስ
ኪፈጸም ድረስ አሕዛብ ኢየሩሳሌምን ይረ
ግጡአታል።

---

፳፥፵፪-፵፫ መዝ. ፻፲፥፩። ፳፩፥፲፬-፲፭ ሉቃ. ፲፪፥፲፩-፲፪። ፳፩፥፳፪ ሆሴዕ ፱፥፯።

### ስለ ክርስቶስ መምጣትና ስለ ምልክቶቹ

(ማቴ. ፳፬፥፳፱-፴፩፤ ማር. ፲፫፥፳፬-፳፯)

፳፭“በፀሐይና በጨረቃ፥ በከዋክብትም ላይ
ምልክት ይሆናል፤ በምድር ላይም አሕዛብ
ይጨነቃሉ፤ ፮ ከባሕሩና ከሞገዱ ድምፅ የተነ
ሣም ይሸበራሉ። ፳፮በዓለም ላይ ከሚመጣው
ፍርሀትና ሽብር የተነሣም የሰዎች ነፍስ ትዝ
ላለች፤ ያንጊዜ የሰማያት ኀይል ይናወጣልና።
፳፯ያንጊዜም በሰማይ ደመና፥ በፍጹም ኀይልና
ክብር ሲመጣ የሰውን ልጅ ያዩታል። ፳፰ይህም
ሁሉ በሆነ ጊዜ ወደ ላይ አቅንታችሁ ተመል
ከቱ፤ ራሳችሁንም አንሡ፤ የሚያድናችሁ መጥ
ቶአልና።”

፳፱ምሳሌም መስሎ እንዲህ አላቸው፥ “በለ
ስንና ዛፎችን ሁሉ እዩ። ፴ለምልመውም ያያ
ችኋቸው እንደ ሆነ መከር እንደ ደረሰ ታው
ቃላችሁ። ፴፩እንዲሁ እናንተም ይህ እንደ ሆነ
ስታዩ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ደረ
ሰች ዕወቁ። ፴፪እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ
እስኪደረግ ድረስ ይህቺ ትውልድ አታልፍም።
፴፫ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን አያል
ፍም።

### ትምህርትና ምክር

፴፬“ራሳችሁን ጠብቁ፤ በመብልና በመጠጥ፥
በመቅማጠልና የዓለምን ኑሮ በማሰብ ልባችሁን
አታደንድኑ፤ ያቺ ቀንም በድንገት ትደርስባች
ኋለች። ፴፭በምድር በሚኖሩት ሁሉ ላይ እንደ
ተዘረጋች ወጥመድ ትደርሳለችና። ፴፮እንግዲህ
ከዚህ ከሚመጣው ሁሉ በጸሎታችሁ ማምለጥ
እንድትችሉ፥ በሰው ልጅ ፊትም እንድትቆሙ
ሁልጊዜ ትጉ።”

### በደብረ ዘይት ስለ ማደሩ

፴፯ቀን ቀን በመቅደስ[፪] ያስተምር ነበር፤
ሌሊት ግን ወጥቶ ደብረ ዘይት በሚባለው
ተራራ ያድር ነበር። ፴፰ሕዝቡም ሁሉ ቃሉን
ሊሰሙ እርሱ ወዳለበት ወደ መቅደስ ማልደው
ይሄዱ ነበር።

## ምዕራፍ ፳፪

### የካህናት አለቆች ጌታን ለመግደል እንደ ፈለጉ

(ማቴ. ፳፮፥፩-፭፤ ዮሐ. ፲፩፥፵፭-፶፫)

፩ፋሲካም የሚባለው የቂጣ በዓል ቀረበ።
፪የካህናት አለቆችና ጻፎችም ሊገድሉት
ይሹ ነበር፤ ነገር ግን ሕዝቡን ይፈሩአቸው
ነበር።

### ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ለመስጥት እንደ ተስማማ

(ማቴ. ፳፮፥፲፬-፲፮፤ ማር. ፲፬፥፲-፲፩)

፫ቍጥሩ ከዐሥራ ሁለቱ በነበረው በአስቆሮቱ
ይሁዳ ልብ ሰይጣን አደረ። ፬ሄዶም ከካህናት
አለቆችና ከታላላቆች ጋር እርሱን አሳልፎ እን
ዲሰጣቸው ተነጋገረ። ፭ደስ ብሏቸውም ሠላሳ
ብር[፩] ሊሰጡት ተስማሙ። ፮እርሱም እሺ
አለ፤ ሰው ሳይኖርም እርሱን አሳልፎ ሊሰጣ
ቸው ምቹ ጊዜ ይሻ ነበር።

### የፋሲካን በግ ስለ ማዘጋጀት

(ማቴ. ፳፮፥፲፯-፳፭፤ ዮሐ. ፲፫፥፳፩-፴)

፯የፋሲካን በግ የሚያርዱባት የቂጣ በዓ
ልም ደረሰች። ፰ጌታችን ኢየሱስም ጴጥ
ሮስንና ዮሐንስን፥ “ሂዱና የምንበላውን
የፋሲካ በግ አዘጋጁልን” አላቸው። ፱እነር
ሱም፥ “ወዴት ልናዘጋጅልህ ትወዳለህ?”
አሉት። ፲እንዲህም አላቸው፥ “ወደ ከተማ
በገባችሁ ጊዜ፥ የውኃ ማድጋ የተሸከመ
ሰው ታገኛላችሁ፤ ወደሚገባበትም ቤት
እርሱን ተከተሉት። ፲፩የዚያን ቤት ጌታ፦
መምህር ከደቀ መዛሙርቴ ጋር የፋሲካን
በግ የምበላበት ቤት ወዴት ነው? ብሎሃል
በሉት። ፲፪እርሱም በሰገነት ላይ የተነጠፈ
ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል፤ በዚያ አዘጋጁ
ልን።” ፲፫በሄዱም ጊዜ እንዳላቸው አገኙ፤
የፋሲካውንም በግ አዘጋጁ።

---

፩ “ከዋክብትም ከሰማይ ወደ ምድር ይወድቃሉ” የሚል በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ ይገኛል።

፪ በግእዙ “በምኵራብ” ይላል።

፩ “ሰላሳ ብር” የሚለው በግሪኩ የለም።

፳፩፥፳፭ ኢሳ. ፲፫፥፲፤ ሕዝ. ፴፪፥፯፤ ኢዩ. ፪፥፴፩፤ ራእ. ፮፥፲፪-፲፫። ፳፩፥፳፯ ዳን. ፯፥፲፫፤ ራእ. ፩፥፯።
፳፩፥፴፯ ሉቃ. ፲፱፥፵፯። ፳፪፥፩ ዘፀ. ፲፪፥፩-፳፯።

## ስለ ምሥጢረ ቍርባን

(ማቴ. ፳፮፥፳፮-፴፤ ማር. ፲፬፥፳፪-፳፮)

፲፬ ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ በማ
ዕድ ተቀመጠ፤ ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙር
ቱም ከእርሱ ጋር ተቀመጡ። ፲፭ እርሱም እን
ዲህ አላቸው፥ "ከመከራዬ አስቀድሞ ይህን
ፋሲካ ከእናንተ ጋር ልበላ እጅግ ወደድሁ።
፲፮ ነገር ግን፤ በእግዚአብሔር መንግሥት እስ
ኪፈጸም ድረስ እንግዲህ ከእርሱ እንደማልበላ
እነግራችኋለሁ" አላቸው። ፲፯ ጽዋውንም ተቀ
ብሎ አመሰገነ፤ እንዲህም አለ፥ "ይህን እንኩ
ሁላችሁም ተካፈሉት። ፲፰ እላችኋለሁ፥ የእግዚ
አብሔር መንግሥት እስክትመጣ ድረስ፤[፩] እን
ግዲህ ወዲህ ከዚህ የወይን ፍሬ አልጠጣም።"
፲፱ ኅብስቱንም አንሥቶ፤ አመስገነ፤ ፈትቶም ሰጣ
ቸው፤ እንዲህም አላቸው፥ "ስለ እናንተ ቤዛ
ሆኖ የሚሰጥ ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህንም ለመ
ታሰቢያዬ አድርጉት፤" ፳ እንዲሁም ከእራት
በኋላ ጽዋዉን አንሥቶ እንዲህ አላቸው፥ "ይህ
ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈስሰው ደሜ የሚሆን
አዲስ ኪዳን ነው።

## ስለሚያሲዘው ሰው የተሰጠ ምልክት

፳፩ "ነገር ግን አሳልፎ የሚሰጠኝ ሰው እጅ
እነሆ፥ በማዕድ ከእኔ ጋር ነው። ፳፪ የሰው ልጅስ
ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል፤ ነገር ግን
የሰው ልጅ በእጁ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮ
ለት።" ፳፫ ደቀ መዛሙርቱም ከእነርሱ ይህን
የሚያደርግ ማን እንደ ሆነ እርስ በርሳቸው
ተነጋገሩ።

## ስለ ትሕትና

፳፬ ከዚህም በኋላ ከእነርሱ ማን እንደሚበልጥ
እርስ በርሳቸው ተከራከሩ። ፳፭ እርሱም እንዲህ
አላቸው፥ "አሕዛብን ንጉሦቻቸው ይገዙአቸ
ዋል፤ በላያቸውም ሥልጣን ያላቸው ቸርነት
አድራጊዎች ይባላሉ። ፳፮ ለእናንተ ግን እንዲህ
አይደለም፤ ነገር ግን ከእናንተ ታላቁ እንደ
ታናሽ ይሁናችሁ፤ አለቃውም እንደ አገልጋይ
ይሁን። ፳፯ የሚበልጥ ማንኛው ነው? በማዕድ
ላይ የተቀመጠው ነው? ወይስ የሚላላከው?
በማዕድ ላይ የተቀመጠው አይደለምን? እነሆ፥
እኔ በመካከላችሁ እንደ አገልጋይ ነኝ። ፳፰ ነገር
ግን ስለ እኔ የታገሣችሁ እናንተ በመከራዬ
ከእኔ ጋር ናችሁ። ፳፱ አባቴ ለእኔ እንደ ሰጠኝ፥
እኔም ለእናንተ መንግሥትን አዘጋጅላችኋለሁ፤
፴ በመንግሥቴ በማዕዴ ትበሉና ትጠጡ ዘንድ፥
በወንበሮችም ተቀምጣችሁ በዐሥራ ሁለቱ ነገደ
እስራኤል ትፈርዱ ዘንድ።"

## ሃይማኖትን ስለ ማጽናት

(ማቴ. ፳፮፥፴፩-፴፭፤ ዮሐ. ፲፫፥፴፮-፴፰)

፴፩ ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አለ፥ "ስም
ዖን፥ ስምዖን ሆይ፥ ሰይጣን እንደ አጃ ሊያበ
ጥራችሁ አሁን ለመናችሁ። ፴፪ እኔ ግን ሃይ
ማኖታችሁ እንዳይደክም ስለ እናንተ ጸለይሁ፤
አንተም ተመልሰህ ወንድሞችህን አጽናቸው።"
፴፫ እርሱም፥ "አቤቱ፥ እኔ ለመታሰርም ቢሆን፥
ለሞትም ቢሆን እንኳ ከአንተ ጋራ ለመሄድ
የተዘጋጀሁ ነኝ" አለው። ፴፬ እርሱ ግን፥ "ጴጥ
ሮስ ሆይ፥ እልሃለሁ፥ ዛሬ ዶሮ ሳይጮኽ እን
ደማታውቀኝ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ" አለው።
፴፭ ደግሞም፥ "ያለ ስልቻ፥ ያለ ከረጢትና ያለ
ጫማ በላክኋችሁ ጊዜ በውኑ የተቸገራችሁት
ነገር ነበርን?" አላቸው፤ እነርሱም፥ "የለም"
አሉት። ፴፮ እርሱም እንዲህ አላቸው፥ "አሁን
ግን ኮሮጆ ያለው ኮሮጆውን ይያዝ፤ ከረጢትም
ያለው እንዲሁ ያድርግ፤ ሰይፍ የሌለውም ልብ
ሱን ሸጦ ሰይፍ ይግዛ። ፴፯ እላችኋለሁ፥ ከኃ
ጥኣን ጋር ተቈጠረ ተብሎ የተጻፈው በእኔ
ይደርሳል፤ ስለ እኔ የተጻፈውም ሁሉ ይፈጸ
ማል።" ፴፰ እነርሱም፥ "አቤቱ፥ እነሆ፥ እዚህ
በእኛ ዘንድ ሁለት ሰይፎች አሉ" አሉት፤ እር
ሱም፥ "እንግዲያስ ይበቃችኋል" አላቸው።

## በደብረ ዘይት ስለ መጸለዩ

(ማቴ. ፳፮፥፴፮-፵፮፤ ማር. ፲፬፥፴፪-፵፪)

፴፱ ወጥቶም እንዳስለመደው ይጸልይ ዘንድ[፪]
ወደ ደብረ ዘይት ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም

---

፩ በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ "በእግዚአብሔር መንግሥት አዲሱን እስክጠጣው ድረስ" ይላል።

፪ "ይጸልይ ዘንድ" የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።

፳፪፥፳ ኤር. ፴፩፥፴፩-፴፬።  ፳፪፥፳፩ መዝ. ፵፥፱።  ፳፪፥፳፬ ማቴ. ፲፰፥፩፤ ማር. ፱፥፴፬፤ ሉቃ. ፱፥፵፮።
፳፪፥፳፭-፳፮ ማቴ. ፳፭-፳፯፤ ማር. ፲፥፵፪-፵፬።  ፳፪፥፳፯ ማቴ. ፳፫፥፲፩፤ ማር. ፱፥፴፭።
፳፪፥፳፰ ዮሐ. ፲፫፥፲፪-፲፭።  ፳፪፥፴ ማቴ. ፲፱፥፳፰።  ፳፪፥፴፭ ማቴ. ፲፥፱-፲፤ ማር. ፮፥፰-፱፤ ሉቃ. ፱፥፫፤ ፲፥፬።
፳፪፥፴፯ ኢሳ. ፶፫፥፲፪።

ተከተሉት። ፵ከዚያም ደርሶ፥ “ወደ መከራ
እንዳትገቡ ጸልዩ” አላቸው። ፵፩የድንጋይ ውር
ወራ ያህልም ከእነርሱ ፈቀቅ ብሎ እየሰገደ
ጸለየ። ፵፪እንዲህም አለ፥ “አባት ሆይ፥ ብትፈ
ቅድስ ይህን ጽዋ ከእኔ አሳልፈው፤ ነገር ግን
የአንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይ
ሁን።” ፵፫የሚያበረታታው የእግዚአብሔር መል
አክም ከሰማይ ታየው። ፵፬ፈራ፤ መላልሶም
ጸለየ፤ ላቡም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ
ደም ነጠብጣብ ሆነ። ፵፭ከሚጸልይበትም ተነ
ሥቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሄደ፤ ከኀዘንም የተ
ነሣ ተኝተው አገኛቸው። ፵፮“ስለ ምን ትተኛላ
ችሁ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሡና ጸልዩ”
አላቸው።

## በአይሁድ እጅ ስለ መግባቱ

(ማቴ. ፳፮፥፵፯-፶፮፤ ዮሐ. ፲፰፥፫-፲፩)

፵፯ይህንም ሲነግራቸው ሕዝቡ ደረሱ፤ ከዐ
ሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ አንዱ ይሁዳም
ይመራቸው ነበር፤ ወደ ጌታችን ኢየሱስም
ቀርቦ ሳመው፤ የሰጣቸውም ምልክት ይህ
ነበር፤ “የምስመው እርሱ ነውና እርሱን አጽ
ንታችሁ ያዙት”[፩] አላቸው። ፵፰ጌታችን ኢየሱ
ስም ይሁዳን፥ “በመሳም የሰውን ልጅ አሳል
ፈህ ትሰጠዋለህን?” አለው። ፵፱አብረውት የነ
በሩትም የሆነውን ባዩ ጊዜ፥ ጌታችን ኢየሱ
ስን፥ “አቤቱ፥ በሰይፍ ልንመታቸው ትፈቅዳ
ለህን?” አሉት። ፶ከእነርሱም አንዱ የሊቀ ካህ
ናቱን አገልጋይ መታው፤ ቀኝ ጆሮውንም ቈረ
ጠው። ፶፩ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ “ይህንስ
ተው” አለ፤ ወዲያውም ጆሮውን ዳስሶ አዳ
ነው። ፶፪ጌታችን ኢየሱስም ሊይዙት ወደ እርሱ
የመጡትን የካህናት አለቆችን፥ የቤተ መቅደስ
ሹሞችንና ሽማግሌዎችን እንዲህ አላቸው፥
“ሌባን እንደምትይዙ በሰይፍና በጎመድ ልት
ይዙኝ መጣችሁን? ፶፫ዘወትርም ከእናንተ ጋር
በቤተ መቅደስ ስኖር እጃችሁን እንኳ አልዘረ
ጋችሁብኝም፤ ነገር ግን ጊዜያችሁ ይህ ነው፤
የጨለማው አበጋዝም ሥልጣኑ ይህ ነው።”

## ስለ ጴጥሮስ ክሕደት

(ማቴ. ፳፮፥፶፯፡፶፰፤ ማር. ፲፬፥፶፫፡፶፬)

፶፬ይዘውም ወደ ሊቀ ካህናቱ ቤት ወሰዱት፤
ጴጥሮስም ከሩቅ ይከተለው ነበር። ፶፭በግቢውም
ውስጥ እሳት አንድደው ተቀመጡ፤ ጴጥሮስም
አብሮአቸው በመካከላቸው ተቀመጠ። ፶፮በእሳ
ቱም ብርሃን በኩል ተቀምጦ ሳለ አንዲት ብላ
ቴና አየችው፤ እርሱ መሆኑንም ለየችውና፥
“ይህም ከእርሱ ጋር ነበር” አለች። ፶፯እርሱ
ግን፥ “ሴትዮ! የምትዪውን አላውቅም” ብሎ
ካደ። ፶፰ከጥቂት ጊዜም በኋላ ሌላ ሰው አየ
ውና፥ “አንተም ከእነርሱ ወገን ነህ” አለው፤
ጴጥሮስ ግን፥ “አንተ ሰው! እኔ አይደለሁም”
አለው። ፶፱አንዲት ሰዓት ያህልም ቈይቶ አንድ
ሌላ ሰው፥ “ይህም በእውነት ከእርሱ ጋር
ነበረ፤ ሰውየውም የገሊላ ሰው ነው” ብሎ አስ
ጨነቀው። ፷ጴጥሮስ ግን፥ “አንተ ሰው! የምት
ለውን አላውቅም” አለው፤ እርሱም ይህን ሲና
ገር ያንጊዜ ዶሮ ጮኸ። ፷፩ጌታችን ኢየሱስም
ዘወር ብሎ ጴጥሮስን አየው፤ ጴጥሮስም፥ “ዛሬ
ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ” ያለውን
የጌታችንን ቃል ዐሰበ። ፷፪ጴጥሮስም ወደ ውጭ
ወጥቶ መራራ ልቅሶን አለቀሰ።

## አይሁድ በጌታችን በኢየሱስ ላይ ስለ መዘባበታቸው

፷፫ጌታችን ኢየሱስን ይዘውት የነበሩት ሰዎ
ችም ይዘባበቱበትና ይደበድቡት ነበር። ፷፬ሸፍ
ነውም ፊቱን በጥፊ ይመቱት ነበር፤ “ፊትህን
በጥፊ የመታህ ማነው? ንገረን” እያሉም ይጠ
ይቁት ነበር። ፷፭ሌላም ብዙ ነገር እየተሳደቡ
በእርሱ ላይ ይናገሩ ነበር።

## በአደባባይ ስለ መቆሙ

(ማቴ. ፳፮፥፶፱-፷፮፤ ዮሐ. ፲፰፥፲፱-፳፬)

፷፮በነጋም ጊዜ፥ የካህናት አለቆች፥ ጻፎችና የሕ
ዝቡ ሽማግሌዎች ተሰብስበው ወደ ሸንጎአቸው
ወሰዱት። ፷፯“አንተ ክርስቶስ እንደ ሆንህ በግ
ልጥ ንገረን” አሉት፤ እርሱም እንዲህ አላቸው፥
“ብነግራችሁም አታምኑኝም። ፷፰ብጠይቃችሁም
አትመልሱልኝም፤ ወይም አትተዉኝም። ፷፱ነገር
ግን ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር
ኀይል ቀኝ ይቀመጣል።” ፸ሁሉም፥ “እንግዲያስ
አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህን?” አሉት፤ እር
ሱም፥ “እኔ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንሁ
እናንተ ትላላችሁ” አላቸው። ፸፩እነርሱም፥ “ስለ
እርሱ ምን ምስክር እንሻለን? እኛ ራሳችን ሲና
ገር ሰምተናል” አሉ።

---

፩ “የምስመው እርሱ ነውና እርሱን አጽንታችሁ ያዙት” የሚለው በግሪኩና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።

፳፪፥፶፫ ሉቃ. ፲፱፥፵፯፤ ፳፩፥፴፯።

## ምዕራፍ ፳፫

### ጌታችን በጲላጦስ ፊት ስለ መቆሙ

(ማቴ. ፳፯፥፩-፪፤ ማር. ፲፭፥፩-፭)

፩ሁሉም በሙሉ ተነሥተው ወደ ጲላጦስ
ወሰዱት። ፪እንዲህም እያሉ ይከስሱት ጀመር፥
"ይህ ሰው ለቄሣር ግብር እንዳይሰጡ ሲከለክ
ልና ሕዝቡን ሲያሳምፅ፥ ራሱንም የእስራኤል
ንጉሥ ክርስቶስን ሲያደርግ አገኘነው።" ፫ጲላ
ጦስም፥ "አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን?" ብሎ
ጠየቀው፤ ጌታችን ኢየሱስም፥ "እኔ እንደ
ሆንሁ አንተ አልህ" አለው። ፬ጲላጦስም ለካህ
ናት አለቆችና ለሕዝቡ፥ "በዚህ ሰው ላይ ያገ
ኘሁት አንድስ እንኳ በደል የለም" አላቸው።
፭ሕዝቡም፥ "ከገሊላ ጀምሮ እስከዚህ ድረስ
በመላው ይሁዳ እያስተማረ ሕዝቡን ያውካል"
እያሉ አጽንተው ጮኹ።

### ጌታችን በሄሮድስ ፊት ስለ መቆሙ

፮ጲላጦስም "ገሊላ" ሲሉ ሰምቶ፤ ሰውየዉ
ገሊላዊ እንደ ሆነ የገሊላን ሰዎች ጠየቀ። ፯ከሄ
ሮድስ ግዛትም ውስጥ መሆኑን ዐውቆ ወደ
ሄሮድስ ላከው፤ ሄሮድስ በዚያ ወራት በኢየ
ሩሳሌም ነበርና። ፰ሄሮድስም ጌታችን ኢየሱ
ስን ባየው ጊዜ እጅግ ደስ አለው፤ ዜናውን
ስለሚሰማ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሊያየው ይሻ
ነበርና፤ የሚያደርገውንም ተአምራት ሊያይ
ይመኝ ነበርና። ፱በብዙ ነገርም መረመረው፤
እርሱ ግን አንድስ እንኳ አልመለሰለትም። ፲የካ
ህናት አለቆችና ጻፎችም ቆመው በብዙ ያሳ
ጡት ነበር። ፲፩ሄሮድስም ከሠራዊቱ ጋር አቃ
ለለው፤ አፌዘበትም፤ የሚያንፀባርቅ ልብስም
አልብሶ ወደ ጲላጦስ መልሶ ሰደደው። ፲፪በዚ
ያም ቀን ሄሮድስና ጲላጦስ ተስማሙ፤ ቀድሞ
ጥል ነበራቸውና።
፲፫ጲላጦስም የካህናት አለቆችንና መኳንን
ቱን፥ ሕዝቡንም ጠራቸው። ፲፬እንዲህም አላ
ቸው፥ "ይህን ሰው ሕዝብን ያሳምፃል ብላችሁ
ወደ እኔ አመጣችሁት፤ በፊታችሁም እነሆ፥
መረመርሁት፤ ግን እናንተ ካቀረባችሁት ክስ
በዚህ ሰው ላይ ያገኘሁት አንዳች በደል የለም።
፲፭ወደ ሄሮድስም ሰድጃችሁ ነበር፤ እርሱም
ምንም ስላላገኘበት ወደ እኛ መልሶታል፤ ለሞ
ትም የሚያበቃ ያደረገው ነገር የለም። ፲፮እነሆ፥
እኔም እንግዲህ ገርፌ ልተወው" አለ።

### በርባን ስለ መፈታቱና በጌታ ስለ መፈረዱ

፲፯በየበዓሉም ከእስረኞች አንድ ሊፈታላቸው
ልማድ ነበር። ፲፰ሁሉም በሙሉ፥ "ይህን አስ
ወግደው፥ ስቀለውም፥[፩] በርባንን ግን ፍታልን"
ብለው ጮሁ። ፲፱ያ በርባን ግን በከተማ ሁከት
ያደረገና ነፍስ በመግደል የታሰረ ነበር። ፳ጲላ
ጦስም ኢየሱስን ሊፈታው ወዶ፥ " ኢየሱ
ስን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁን?" ብሎ እንደ
ገና ተናገራቸው። ፳፩እነርሱ ግን፥ "ስቀለው!
ስቀለው!" እያሉ ይጮሁ ነበር። ፳፪ጲላጦስም
ለሦስተኛ ጊዜ፥ "ምን ክፉ ነገር አደረገ?
እነሆ፥ ለሞት የሚያበቃ ምክንያት አላገኘሁ
በትም፤ እንኪያስ ልግረፈውና ልተወው" አላ
ቸው። ፳፫እንዲሰቅሉትም ቃላቸውን ከፍ አድ
ርገው እየጮሁ ለመኑ፤ ጩኸታቸውና የካህ
ናት አለቆች ድምፅም በረታ። ፳፬ጲላጦስም የለ
መኑት ይሆንላቸው ዘንድ ፈረደበት። ፳፭ያን የለ
መኑትን፥ ነፍስ በመግደልና ሁከት በማድረግ
የታሰረውንም ሰው ፈታላቸው፤ ኢየሱስን ግን
ለፈቃዳቸው አሳልፎ ሰጣቸው።

### ወደ መስቀል ጉዞ

(ማቴ. ፳፯፥፴፪-፵፬፤ ዮሐ. ፲፱፥፲፯-፳፯)

፳፮በወሰዱትም ጊዜ የቀሬና ሰው ስምዖንን
ከዱር ሲመለስ ያዙት፤ ከጌታችን ከኢየሱስም
በስተኋላ መስቀሉን አሸከሙት። ፳፯ብዙ ሰዎ
ችም ተከተሉት፤ ሴቶችም "ዋይ ዋይ" እያሉ
ያዝኑለትና ያለቅሱለት ነበሩ። ፳፰ጌታችን ኢየ
ሱስም መለስ ብሎ እንዲህ አላቸው፥ "እና
ንተ የኢየሩሳሌም ልጆች ሆይ፥ ለራሳችሁና
ለልጆቻችሁ አልቅሱ እንጂ ለእኔስ አታልቅሱ
ልኝ። ፳፱መካኖች፥ ያልወለዱ ማኅፀኖችና ያላ
ጠቡ ጡቶችም የተመሰገኑ ናቸው የሚሉበት
ወራት ይመጣልና። ፴ያንጊዜም ተራሮችን 'በላ
ያችን ውደቁ፤ ኮረብቶችንም ሰውሩን' ይሉአቸ
ዋል። ፴፩በዚህ ርጥብ ዕንጨት እንዲህ ያደረጉ
በደረቁማ እንዴት ይሆን?"

### ከወንበዴዎች ጋር ስለ መሰቀሉ

፴፪ሌሎች ሁለት ወንበዴዎችንም ከእርሱ ጋር
ሊሰቅሉ ወሰዱ። ፴፫ቀራንዮ ወደሚባለው ቦታ

---

[፩] "ስቀለው" የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።

፳፫፥፴ ሆሴዕ ፲፥፰፤ ራእ. ፮፥፲፮።

በደረሱ ጊዜም፥ በዚያ ሰቀሉት፤ እነዚያንም
ሁለት ወንበዴዎች አንዱን በቀኙ አንዱንም
በግራው ሰቀሉ። ፴፬ጌታችን ኢየሱስም፥ “አባት
ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላ
ቸው” አለ፤ በልብሱም ላይ ዕጣ ተጣጣሉና
ተካፈሉ። ፴፭ሕዝቡም ቆመው ይመለከቱ ነበር፤
አለቆችም፥ “ሌሎችን አዳነ፤ በእግዚአብሔር
የተመረጠ ክርስቶስ ከሆነ ራሱን ያድን” እያሉ
ያፌዙበት ነበር። ፴፮ጭፍሮችም ይዘብቱበት
ነበር፤ ወደ እርሱም ቀርበው ሆምጣጤ አመጡ
ለት። ፴፯እንዲህም ይሉት ነበር፥ “አንተ የአይ
ሁድ ንጉሥ ከሆንህስ ራስህን አድን።” ፴፰በራ
ስጌውም ደብዳቤ ጻፉ፤ ጽሕፈቱም በሮማይ
ስጥ፥ በጽርዕና በዕብራይስጥ ሆኖ “የአይሁድ
ንጉሣቸው ይህ ነው” የሚል ነበር።

## ስለ ሁለቱ ወንበዴዎች

(ማቴ. ፳፯፡፴፰-፵፬፤ ማር. ፲፭፡፳፯-፴፪)

፴፱አብረው ተሰቅለው ከነበሩት አንዱ ወን
በዴ፥ “አንተስ ክርስቶስ ከሆንህ ራስህን
አድን፤ እኛንም አድነን” ብሎ ተሳደበ። ፵ኋደ
ኛውም መልሶ ገሥጸው፤ እንዲህም አለው፥
“አንተ በዚህ ፍርድ ውስጥ ሳለህ እግዚአብ
ሔር አምላክህን[፬] አትፈራውምን? ፵፩በእኛስ
በሚገባ ተፈርዶብናል፤ እንደ ሥራችንም ፍዳ
ችንን ተቀበልን፤ ይህ ግን ምንም የሠራው
ክፉ ሥራ የለም።” ፵፪ጌታችን ኢየሱስንም፥
“አቤቱ፥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ ዐስበኝ”
አለው። ፵፫ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ
አለው፥ “እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ በገነት ከእኔ
ጋር ትሆናለህ።”

## ጌታ ስለ መሞቱና ስለ ተአምራቱ

(ማቴ. ፳፯፡፵፭-፶፮፤ ማር. ፲፭፡፴፫-፵፩)

፵፬ቀትር በሆነ ጊዜም በስድስት ሰዓት ፀሐይ
ጨለመ፤ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስም ዓለም
ሁሉ[፭] ጨለማ ሆነ። ፵፭ፀሐዩም በጨለመ ጊዜ
የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች[፮] ከመ
ካከሉ ተቀደደ። ፵፮ያንጊዜም ጌታችን ኢየሱስ
ድምፁን ከፍ አድርጎ፥ “አባት ሆይ፥ ነፍሴን
በአንተ እጅ አደራ እሰጣለሁ” ብሎ ጮኸ፤
ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ። ፵፯የመቶ አለቃ
ውም የሆነውን ነገር አይቶ፥ “ይህ ሰው በእ
ውነት ጻድቅ ነበረ”ብሎ እግዚአብሔርን አመ
ሰገነው። ፵፰ይህንም ለማየት ተሰብስበው የነበ
ሩት ሕዝብ ሁሉ የሆነውን ባዩ ጊዜ፥ ደረታቸ
ውን እየመቱ ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ፵፱የሚ
ያውቁት ሁሉና ከገሊላ ጀምሮ የተከተሉትም
ሴቶች በሩቁ ቆመው ይህን ያዩ ነበር።

## ጌታ ስለ መቀበሩ

(ማቴ. ፳፯፡፶፯-፷፩፤ ዮሐ. ፲፱፡፴፰-፵፪)

፶እነሆ፥ በጎና ጻድቅ ሰው፥ የሸንጎ አማካሪም
የሆነ ዮሴፍ የሚባል ሰው መጣ። ፶፩እርሱም
በአይሁድ በምክራቸውና በሥራቸው አልተባበ
ረም ነበር፤ ሀገሩም የይሁዳ ዕጣ የሚሆን አር
ማትያስ ነበር፤ እርሱም የእግዚአብሔርን መን
ግሥት ተስፋ ያደርግ ነበር። ፶፪ወደ ጲላጦስም
ሄዶ የጌታችን የኢየሱስን ሥጋ ለመነ። ፶፫ሥጋ
ውንም አውርዶ በበፍታ ገነዘው፤ ማንም ባል
ተቀበረበት፥ ከድንጋይም በተፈለፈለ መቃብር
ቀበረው፤ ታላቅ ድንጋይም አንከባልሎ መቃብ
ሩን ገጥሞ ሄደ።[፯] ፶፬ያም ቀን የሰንበት መግቢያ
ዐርብ ነበር። ፶፭ከገሊላም ከእርሱ ጋር የመጡ
ሁለት[፰] ሴቶች ተከትለው፥ መቃብሩን፥ ሥጋ
ውንም እንዴት እንዳኖሩት አዩ። ተመልሰውም
ሽቱና ዘይት አዘጋጁ፤ ነገር ግን በሰንበት አል
ሄዱም፤ ሕጋቸው እንዲህ ነበርና።

## ምዕራፍ ፳፬

## ጌታ ስለ መነሣቱ

(ማቴ. ፳፰፡፩-፲፤ ዮሐ. ፳፡፩-፲)

፩ከሳምንቱም በመጀመሪያዪቱ ቀን ያዘጋጁ
ትን ሽቶ ይዘው እጅግ ማልደው ወደ መቃብሩ
ሄዱ፤ ሌሎች ሴቶችም አብረዋቸው ነበሩ።
፪ያቺንም ድንጋይ ከመቃብሩ ላይ ተንከባልላ
አገኙአት። ፫ገብተውም የጌታችን የኢየሱስን

---

[፬] “አምላክህን” የሚለው በግሪኩ የለም።

[፭] በግሪኩ “ምድር ሁሉ” ይላል።

[፮] “ከላይ እስከ ታች” የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።

[፯] “ታላቅ ድንጋይም አንከባልሎ መቃብሩን ገጥሞ ሄደ” የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።

[፰] በግሪኩ “ሁለት” አይልም።

፳፫፡፴፬ መዝ. ፳፩፡፲፰። ፳፫፡፴፭ መዝ. ፳፩፡፯። ፳፫፡፴፮ መዝ. ፷፰፡፳፩። ፳፫፡፵፭ ዘፀ. ፳፮፡፴፩-፴፫። ፳፫፡፵፮ መዝ. ፴፡፭። ፳፫፡፵፱ ሉቃ. ፰፡፪-፫። ፳፫፡፶፮ ዘፀ. ፳፡፲፣ ዘዳ. ፭፡፲፬።

ሥጋ አላገኙም። ፬ስለዚህም ነገር የሚሉትን
አጥተው ሲያደንቁ ሁለት ሰዎች ከፊታቸው
ቆመው ታዩአቸው፤ ልብሳቸውም ያብረቀርቅ
ነበር። ፭ፈርተውም ፊታቸውን ወደ ምድር አቀ
ረቀሩ። እነርሱም እንዲህ አሉአቸው፥ "ሕያ
ዉን ከሙታን ጋር ለምን ትሹታላችሁ? ፮በዚህ
የለም፤ ተነሥቶአል። በገሊላ ሳለ ለእናንተ እን
ዲህ ሲል የተናገረውን ዐስቡ፦ ፯የሰው ልጅ
በኀጢአተኞች ሰዎች እጅ ተላልፎ ይሰጥ ዘንድ
አለው፤ ይሰቅሉታል፤ ይገድሉታል፤ በሦስተኛ
ውም ቀን ይነሣል።" ፰ቃሉንም ዐሰቡ። ፱ከመ
ቃብርም ተመልሰው ለዐሥራ አንዱና ለቀሩት
ባልንጀሮቻቸው ሁሉ ይህን ነገር ነገሩአቸው።
፲እነዚያም መግደላዊት ማርያም፥ ዮሐና፥ የያዕ
ቆብ እናት ማርያም፥ አብረዋቸው የነበሩት ባል
ንጀሮቻቸውም ይህን ለሐዋርያት ነገሩአቸው።
፲፩ይህም ነገር በፊታቸው እንደ ተረት መሰላ
ቸውና አላመኑአቸውም። ፲፪ጴጥሮስም ተነሣ፤
ወደ መቃብርም ፈጥኖ ሄደ፤ ዝቅ ብሎም በተ
መለከተ ጊዜ በፍታውን ለብቻው ተቀምጦ
አየ፤ የሆነውንም እያደነቀ ተመለሰ።

### በኤማሁስ መንገድ ስላገኙት ሰዎች
(ማር. ፲፮፥፲፪-፲፫)

፲፫በዚያም ቀን ከመካከላቸው ሁለት ሰዎች
ከኢየሩሳሌም ስድሳ ምዕራፍ ያህል ወደምትር
ቀው ኤማሁስ ወደምትባለው መንደር ሄዱ።
፲፬እርስ በርሳቸውም ስለ ሆነው ነገር ሁሉ ይነጋ
ገሩ ነበር። ፲፭እነርሱም ይህን ሲነጋገሩና ሲመራ
መሩ ጌታችን ኢየሱስ ወደ እነርሱ ቀረበ፤ አብ
ሮአቸውም ሄደ። ፲፮እንዳያውቁትም ዐይናቸው
ተይዞ ነበር። ፲፯ጌታችንም፥ "በትካዜ እየሄዳ
ችሁ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩት ይህ ነገር
ምንድን ነው?" አላቸው። ፲፰ከእነርሱም ቀለዮጳ
የሚባለው አንዱ መልሶ፥ "አንተ ብቻ ለኢየ
ሩሳሌም እንግዳ ነህን? በእነዚህ ቀኖችስ በው
ስጥዋ የተደረገውን አታውቅምን?" አለው።
፲፱ጌታችን ኢየሱስም፥ "ይህ ምንድነው?" አላ
ቸው፤ እነርሱም እንዲህ አሉት፥ "በእግዚአብ
ሔር ፊትና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በቃሉና በሥ
ራው ብርቱ ነቢይና እውነተኛ ሰው ስለነበረው
ስለ ናዝሬቱ ስለ ኢየሱስ፥ ፳የካህናት አለቆ
ችና መኳንንቶቻችን አሳልፈው እንደ ሰጡት፥
ሞትም እንደ ፈረዱበትና እንደ ሰቀሉት ነው።
፳፩እኛ ግን እስራኤልን ያድናቸው ዘንድ ያለው
እርሱ እንደ ሆነ ተስፋ እናደርግ ነበር፤ ከዚ
ህም ሁሉ ጋር ይህ ነገር ከሆነ ዛሬ ሦስተኛ
ቀን ነው። ፳፪ደግሞም ሴቶች ከእኛ ዘንድ ወደ
መቃብር ገስግሠው ሄደው ነበርና አስደንቀው
ነገሩን። ፳፫ሥጋውንም በአላገኙ ጊዜ ተመል
ሰው፦ ተነሥቶአል ያሉአቸውን የመላእክትን
መልክ እንደ አዩ ነገሩን። ፳፬ከእኛም ዘንድ ወደ
መቃብር ሄደው እንዲሁ ሴቶች እንደ ተናገሩት
ሆኖ ያገኙት አሉ፤ እርሱን ግን አላዩትም።"
፳፭ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ "እና
ንተ ሰነፎች፥ ነቢያትም የተናገሩትን ነገር ሁሉ
ከማመን ልባችሁ የዘገየ፥ ፳፮ክርስቶስ እንዲህ
ይሞት ዘንድ ወደ ክብሩም ይመለስ ዘንድ
ያለው አይደለምን?" ፳፯እርሱም ከሙሴና ከነ
ቢያት፥ ከመጻሕፍትም ሁሉ ስለ እርሱ የተነገ
ረውን ይተረጕምላቸው ጀመር።

፳፰ሊሄዱባት ወደ ነበረችው መንደርም ተቃ
ረቡ፤ እርሱ ግን ይርቃቸው ጀመር። ፳፱እነ
ርሱም፥ "መሽቶአልና፥ ፀሐይም ተዘቅዝቆአ
ልና፥ ከእኛ ጋር እደር" ብለው ግድ አሉት፤
ከእነርሱም ጋር ሊያድር ገባ። ፴ከዚህም በኋላ
አብሮአቸው ለማዕድ ተቀምጦ ሳለ እንጀራውን
አንሥቶ ባረከ፤ ቈርሶም ሰጣቸው። ፴፩ዐይናቸ
ውም ተገለጠና ዐወቁት፤ ወዲያውኑም ከእ
ነርሱ ተሰወረ። ፴፪እርስ በርሳቸውም እንዲህ
አሉ፥ "በመንገድ ሲነግረን፥ መጻሕፍትንም
ሲተረጕምልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረ
ምን?"

### ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መመለሳቸው

፴፫በዚያችም ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩሳ
ሌም ተመለሱ፤ ዐሥራ አንዱን ደቀ መዛሙር
ትና አብረዋቸው የነበሩትንም ተሰብስበው አገ
ኙአቸው፤ ፴፬እንዲህ እያሉ፥ "ጌታችን በእው
ነት ተነሥቶአል፤ ለስምዖንም ታይቶታል።"
፴፭እነርሱም በመንገድ የሆነውንና እንጀራውን
ሲቈርስ ጌታችንን እንዴት እንዳወቁት ነገሩአ
ቸው።

### ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ስለ መገለጡ
(ማቴ. ፳፰፥፲፮-፳፤ ዮሐ. ፳፥፲፱-፳፫)

፴፮ይህንም ሲነጋገሩ ጌታችን ኢየሱስ በመካከ
ላቸው ቆመና፥ "ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አት
ፍሩ፤ እኔ ነኝ" አላቸው። ፴፯እነርሱ ግን ፈሩ፤
ደነገጡም፤ ምትሐትንም የሚያዩ መሰላቸው።

---

፳፬፥፮-፯ ማቴ. ፲፮፥፳፩፤ ፲፯፥፳፪-፳፫፤ ፳፥፲፰-፲፱፤ ማር. ፰፥፴፩፤ ፱፥፴፩፤ ፲፥፴፫፥፴፬፤ ሉቃ. ፱፥፳፪፤ ፲፰፥፴፩-፴፫።

፴፰እርሱም እንዲህ አላቸው፥ “ምን ያስደነግ
ጣችኋል? በልባችሁስ እንዲህ ያለ ዐሳብ ለምን
ይነሣሣል? ፴፱እጄንና እግሬን እዩ፤ ዳስሱኝም፤
እኔ እንደ ሆንሁም ዕወቁ፤ በእኔ እንደምታ
ዩት ለምትሐት አጥንትና ሥጋ የለውምና።”
፵ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው።
፵፩ከድንጋጤ የተነሣም ገና ሳያምኑ ደስ ብሎአ
ቸውም ሲያደንቁ ሳሉ፥ “በዚህ አንዳች የሚ
በላ አላችሁን?” አላቸው። ፵፪እነርሱም ከተጠ
በሰ ዓሣ አንድ ቁራጭ፤ ከማር ወለላም ጥቂት
ሰጡት። ፵፫ተቀብሎም በፊታቸው በላ፤ የተረ
ፈውንም አንሥቶ ሰጣቸው።፩

፵፬እርሱም፥ “በሙሴ ኦሪት፥ በነቢያትና
በመዝሙርም ስለ እኔ የተነገረው ይፈጸም
ዘንድ እንዳለው፥ ከእናንተ ጋር ሳለሁ የነገ
ርኋችሁ ነገሬ ይህ ነው” አላቸው። ፵፭ከዚ
ህም በኋላ መጻሕፍትን እንዲያስተውሉ አእ
ምሮአቸውን ከፈተላቸው። ፵፮እንዲህም አላ
ቸው፥ “ክርስቶስ እንዲሞት በሦስተኛውም
ቀን ከሙታን ተለይቶ እንዲነሣ፥ ፵፯ንስሓና
የኀጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአ
ሕዛብ ሁሉ እንዲሰበክ እንዲሁ ተጽፎአል።
፵፰እናንተም ለዚህ ነገር ምስክሮች ናችሁ።
፵፱እነሆ፥ እኔ የአባቴን ተስፋ ለእናንተ እል
ካለሁ፤ እናንተ ግን ከአርያም ኀይልን እስ
ክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ተቀ
መጡ።”

### ስለ ዕርገቱ

(ማር. ፲፮፥፲፱-፳፤ ሐ.ሥ. ፩፥፱-፲፩)

፶እስከ ቢታንያም ወደ ውጭ አወጣቸው፤
እጁንም አንሥቶ በላያቸውም ጭኖ ባረካቸው።
፶፩እየባረካቸውም ራቃቸው፤ ወደ ሰማይም
ዐረገ። ፶፪እነርሱም ሰገዱለትና በታላቅ ደስታ
ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። ፶፫በቤተ መቅደ
ስም ዘወትር እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያ
ገለገሉ ኖሩ።

ከሰባ ሁለቱ አርድእት አንዱ ወንጌላዊ ሉቃስ የጻፈው ወንጌል ተፈጸመ።

የጻፈውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ በዐረገ በሃያ አንድ ዓመት ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በዐሥራ አራት ዓመት በጽርዕ ቋንቋ ለመቄዶንያ ሰዎች ነው።

ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን። አሜን።

---

፩ “የተረፈውንም አንሥቶ ሰጣቸው” የሚለው በግሪኩ የለም።

፳፬፥፵፱ ሐ.ሥ. ፩፥፬።     ፳፬፥፶-፶፩ ሐ.ሥ. ፩፥፱-፲፩።